# መዝገበ፡ፊደል፡

## የግእዝና፡ያማርኛ፡ቋንቋ፡መክፈቻ።

፪ኛ፡ መጽሐፍ።

# መዝገበ፡ፊደል፡

## የግእዝና፡ያማርኛ፡ቋንቋ፡መክፈቻ።

፪ኛ፡ መጽሐፍ።

# አርእስተ፡ ክፍላት፡ ወገጻት።

| (አርእስቶች)፡ | (ክፍሎች)፡ | (ገጾች)፡ |
|---|---|---|
| ፩ኛ፡ ፊደል፡ ከነንዝዙ፡ | ፩፡ ክፍል፡ | ከ፯፡ እስከ፡ ፲፯ |
| ፪ኛ፡ ፊደል፡ ከነንዝዙ፡ | ፪፡ ክፍል፡ | ካ፲፰ — ፴፪ |
| የፊደላዋሪያ፡ ለውጥ፡ | ፫፡ ክፍል፡ | ከ፴፫ — ፴፱ |
| ፫ኛ፡ ባለዋየል፡ ፊደል፡ | ፬፡ ክፍል፡ | ካ፵ — ፵፰ |
| የቍጥር፡ ዐውድ፡ | ፭፡ ክፍል፡ | ››፵፰ — ፶፪ |
| የዘመን፡ ታሪክ፡ | ፮፡ ክፍል፡ | ››፶፫ — ፶፱ |
| ውዳሴ፡ አምላክ፡ | ፯፡ ክፍል፡ | ከ፷ — ፷፬ |

## ስእለት ፡ ወአስተብቍዖት = ልመናና ፡ ምልጃ ።

ይኸን ፡ ጨቅላ ፡ መጽሐፍ ፡ የምታዩ ፡ ኹሉ ፡
ዐደራ ፡ ስለኔ ፡ ማሪያም ፡ ማሪያም ፡ በሉ ፤
በሆዱ ፡ ያለውን ፡ የትምርት ፡ ሽል ፣
አለፍንቅ ፡ እንድወልድ ፡ እንድገላገል ፤
ከኻያ ፡ ስድስቱ ፡ ወንዶች ፡ ፊደላት ፡
አርግዠለኹና ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ።

ስንት ፡ እልፍ ፡ አበው ፡ ናቸው ፡ አርግዘው ፡ የሞቱ ፡ ?!
ቀኝ ፡ እጃቸው ፡ ፀጥሮ ፡ ጥፈት ፡ በማጣቱ ፤
እጇ ፡ እንዳባቶቼ ፡ እጅ ፡ ተምሮ ፡ ባይጥፍ ፡
ከሆዱ ፡ ባለጣም ፡ ይህ ፡ ጨቅላ ፡ መጽሐፍ ።

ለትምክሕት ፡ አይዶለም ፡ ይህን ፡ መናገሬ ፡
ለማስቀናት ፡ እንጂ ፡ ሰነፉን ፡ ገበሬ ፤
ሐዋርያም ፡ ሲጥፍ ፡ ወዳርድእቱ ፡ መንጋ ፡
ቅኑ ፡ አስቀኑ ፡ ይላል ፡ ለምትበልጥ ፡ ጸጋ ።

**እስመ ፡ ኦሪት ፡ በሙሴ ፡ ተውህበት ፤ ጸጋሰ ፡ ወጽድቅ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኮነ ፡ (ዮሐ፩ ፡ ፲፯) ።**

# መዝገበ ፡ ፊደላት ፡ ሴማውያት ።

## ወእማንቱ ፡ ፊደላተ ፡ ግእዝ ፡ ወዐምሐራ ፡

## እለ ፡ ምስለ ፡ ሱርስት ፡ ወዐረብ ፡ ወምስለ ፡ ዕብራይስጥ ፡ የኅብራ ።

«የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ ፊደል ፤ የመናዊ ፡ ወይም ፡ ከለዳዊ ፡ የሚባል» ።

እምኪዳን ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ ወልደ ፡ አባ ፡ ቶክሌ ፡

ተጽሕፈ ፡ ወተኀትመ ፡ ለውሉደ ፡ ጽባሕ ፡ ወሠርክ ፡

በቅዱስ ፡ አልዓዛር ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡

ድሬ ፡ ዳዋ ።

፲፱፻፳፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡

(1934)

ዳግመኛ ፡ በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታርሞ ፡ ታተመ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ (1961) ቀ ፡ 9712



ኅድጉ ፡ ሕፃናተ ፡ ይምጽኡ ፡ ኀቤየ ፡ ወኢትክልእዎሙ ።

ወደኔ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ ሕፃናትን ፡ ተዉ ፡ አትከልክሏቸው ፡ (ማር ፲ ፡ ፲፬) ።

በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ዘይሰመይ ፡ አልፋ ፡ ወሃቢ ፡ ፊደል ፡ ተስፋ ፡ ወጸጋዌ ፡ መምህር ፡ ሱታፋ ፤ ንዜኑ ፡ በጽሒፍ ፡ ወናየድዕ ፡ በአፍ ፡ ህላዌ ፡ ቀዳማይ ፡ አልፍ ፡ ወጠባይዐ ፡ ሆይ ፡ ትሩፍ ፡ ዘኀበእ ፡ እምሰብእ ፡ ወአዕዋፍ ፡ በላዕተ ፡ መጽሐፍ ። ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ለበነተረ ፡ ምእመናን ፡ ፊደላት ፤ እምአፈ ፡ ደቂቅ ፡ ወሕፃናት ፡ ጽሙኣነ ፡ ትምህርት ፤ በቃለ ፡ አሚን ፡ ወበትፍሥሕት ፤

አሜን ።

# መ ቅ ድ ም ።

ፊደል ፡ ማለት ፡ የነገር ፡ የቃል ፡ ምልክት ፡ አምሳል ፡ ወይም ፡ መግለጫ ፡ ማስታወቂያ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሥዕል ፡ እንደ ፡ ማለት ። ዐይነተኛ ፡ ፍችው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የቀረውን ፡ በግስ ፡ ይመለከቷል ። የፊደል ፡ ተራ ፡ የተፋለሰና ፡ አልፍ ፡ አ ፡ ከርስቱ ፡ ከቀዳማዊነት ፡ ተንቅሎ ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ሆይ ፡ ሀ ፡ መዠመሪያ ፡ ፊደል ፡ የኾነ ፡ ከጣቱ ፡ ብርሃን ፡ ከሚባለው ፡ ካንደኛው ፡ ስላሜ ፡ ከመዠመሪያው ፡ ጳጳስ ፡ ከፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ወዲህ ፡ ነው ። አበገደ ፡ የነበረውን ፡ ሀለሐመ ፡ ብለው ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ያፋለሱትም ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ የነበሩ ፡ ጽርአውያንና ፡ ቅብጣውያን ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ያፋለሱበትም ፡ ምክንያት ፡ የግእዝን ፡ ፊደል ፡ ከአኃዝነት ፡ አውጥቶ ፡ የርሳቸውን ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ ፊደል ፡ ላይ ፡ አኃዝ ፡ አድርጎ ፡ ለማግባት ፤ አልፋ ፡ ቤታ ፡ ጋማ ፡ የነበረውን ፡ (፩ ፡ ፪ ፡ ፫) ፡ አሐዱ ፡ ክልኤቱ ፡ ሠለስቱ ፡ እያሉ ፡ አላኢያውና ፡ አላምሳያው ፡ ለመጣፍና ፡ ለመፈደል ፡ ወይም ፡ ተሰብስቦ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ እንዳሚያድር ፡ እንደ ፡ ጥምቀትና ፡ እንደ ፡ ኀጠር ፡ ታቦት ፡ አንዱን ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ለመደረብና ፡ ለማዳበል ፡ እንዲመቻቸው ፡ ነው ። እነሆ ፡ ይህ ፡ ከአሐዱ ፡ እስከ ፡ እልፍ ፡ (፩—፼) ፡ ያለ ፡ አኃዝ ፡ ከስብዓ ፡ (፸) ፡ በቀር ፡ ኹሉም ፡ የጽርእና ፡ የቅብጥ ፡ ፊደል ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ዖ ፡ ዖ=ሚክሮን ፡ ከሚሉት ፡ ከታናሹ ፡ ዖ ፡ ስም ፡ የመጣ ፡ ነው ። ፻ና ፡ ፻፻ም ፡ የጽርእ ፡ ሮ ፡ ነው ፤ መልኩ ፡ የግእዝን ፡ የ ፡ ይመስላል ። ፯ና ፡ ፯ም ፡ የጽርእ ፡ ዜታ ፡ (ዜድ) ፡ ነው ፤ መልኩ ፡ የገን ፡ ኃምስና ፡ ግልስ ፡ ይመስላል ። ፱ና ፡ ፹ ፡ ፺ ፡ ተዛውረውና ፡ ተዘቅዝቀው ፡ አለቦታቸው ፡ አለመልካቸው ፡ ተጥፈዋል ፤ እኒሁም ፡ በጽርእና ፡ በቅብጥ ፡ ኒ ፡ ሚ ፡ ላምዳ ፤ በሮማይስጥ ፡ ኤን ፡ ኤም ፡ ኤል ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ። ፶ም ፡ የነሱው ፡ አኃዝ ፡ ነው ፤ መልኩ ፡ ተለውጦ ፡ እንደ ፡ ን ፡ ኾኗል ፤ በወዲያ ፡ ግን ፡ ራሱ ፡ ጣጥም ፡ ነው ፡ እግሩም ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ነው ። ጥንታዊውም ፡ የግእዝ ፡ አኃዝ ፡ እንደ ፡ ጽርእ ፡ እንደ ፡ ቅብጥ ፡ እንደ ፡ ዕብራይስጥ ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ፊደሉ ፡ እንጂ ፤ እንዳረብና ፡ እንደ ፡ ላቲን ፡ ሌላ ፡ ትርፍ ፡ አኃዝ ፡ አልነበረውም ። አጣጣፉም ፡ እንዳረብና ፡ እንደ ፡ ሱርስት ፡ እንደ ፡

ዕብራይስጥ ፡ ከቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ የነበረው ፡ ተዛውሮ ፡ እንደ ፡ ጽርእ ፡ እንደ ፡ ቅብጥ ፡ ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ የኾነ ፤ የግሱም ፡ አካሄድ ፡ ተለውጦ ፡ ሥሩ ፡ ጫፍ ፡ መጨረሻ ፤ ጫፉ ፡ ሥር ፡ መነሻ ፡ የኾነ ፡ በነሱው ፡ እጅ ፡ ነው ። ይህም ፡ ሐዲስ ፡ ሥራ ፡ የግእዝን ፡ ፊደል ፡ ከጥንታዊ ፡ ሕጉ ፡ ከሴም ፡ ቋንቋ ፡ ዐዋጅ ፡ አውጥቶ ፡ ጥርጊያ ፡ መንገዱን ፡ አጥፍቶ ፡ ቍጥሩን ፡ አሳስቶ ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ የቀረ ፡ አይዶለም ፤ ከዚህ ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፡ ያልፋ ፡ ወያን ፡ ምስጢር ፡ አፍርሷል ፡ (ራእ፩ ፡ ፰) ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አበገደ ፡ እየተረሳና ፡ እየጠፋ ፡ ሀለሐመ ፡ እየሰፋ ፡ ሂዷል ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ በኹሉ ፡ አገር ፡ ጠፍቶ ፡ በሺዋ ፡ በስሜን ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ እኩሉ ፡ የሺዎች ፡ ፊደል ፡ እኩሉ ፡ የስሜኖች ፡ ፊደል ፡ ይሉታል ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ከጥንት ፡ ከሰላማ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ አንቲካ ፡ ፊደል ፡ ነው ። አንቲካነቱም ፡ ሲታወቅ ፡ ባሡስም ፡ ሐውልት ፡ በየመን ፡ በሕምያር ፡ ጥፈት ፡ በየዋሻውና ፡ በየደንጊያው ፡ ተቀርጦ ፡ ይገኛል ፤ በሺዋም ፡ በያድባራቱ ፡ በየገዳማቱ ፡ ይልቁንም ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ በቡልጋ ፡ መማሪያቸው ፡ ማስተማሪያቸው ፡ ርሱ ፡ ነው ። ስሙንም ፡ ኹለተኛ ፡ ፊደል ፡ አቡጊዳ ፡ ፊደል ፡ ይሉታል ፤ ባላገሮችም ፡ እንደ ፡ ብርቅ ፡ ያዩታል ። (ተረት) ፤ አቡጊዳ ፡ የተማሪ ፡ ዕዳ ። ይህም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የፊደላችን ፡ ረድፍና ፡ ተራ ፡ አንቲካውና ፡ እውነተኛው ፡ አበገደሀ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ሀለሐመሠ ፡ እንዳይዶለ ፤ ዐረቦች ፡ ሳይቀሩ ፡ ሴማውያንም ፡ ያፌታውያንም ፡ በቃል ፡ በታሪክ ፡ ይመሰክራሉ ። ይልቁንም ፡ በምስር ፡ ያሉት ፡ የንግሊዝ ፡ ሊቃውንት ፡ ግእዝና ፡ ዕብራይስጥ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ታሪኩን ፡ ከነፊደሉ ፡ በጋዜጣ ፡ ጥፈው ፡ ለዓለም ፡ ኹሉ ፡ ይናኙታል ። እኛም ፡ ይህን ፡ ታሪክ ፡ አጥብቀን ፡ ይዘን ፡ ተመርኵዘን ፡ ያቡጊዳን ፡ አሠር ፡ ተከትለን ፤ ንግባእኬ ፡ ኀበ ፡ ጥንተ ፡ ነገር ፡ ብለን ፡ ሀለሐመን ፡ ጥለን ፡ ፊደላችንን ፡ ሐሰትና ፡ ስሕተት ፡ በሌለበት ፡ በዚያው ፡ በዱሮው ፡ መንገድ ፡ በዱሮው ፡ አካሄድ ፡ በጥንቱ ፡ ተራ ፡ አበገደ ፡ ብለን ፡ እንጥፋለን ። (ተረት) ፤ ጥጃ ፡ ቢሳሳት ፡ ከናቱ ፡ ነገር ፡ ቢሳሳት ፡ ከጥንቱ ፤ ሰይፍ ፡ ቢመለስ ፡ ካፎቱ ። በዚህም ፡ አካሄድ ፡ ሦስት ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ አለበት ፤ አንደኛው ፡ ከጥንቱ ፡ መንገድ ፡ ሰተት ፡ ብሎ ፡ መግባት ። ኹለተኛው ፡ ካለም ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ መስማማት ፤ ፊደሉን ፡ ከኛ ፡ በቀር ፡ በሀ ፡ የሚዠምር ፡ የለምና ። ሦስተኛው ፡ በፊደል ፡ ቍጥር ፡ አለመሳት ፡ አለመሳሳት ፡ ነው ።

የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ ትምርት ፡ ንባቡም ፡ ጥፈቱም ፡ በፊደሉ ፡ ላይ ፡ ይፈጸማል ፤ የፊደሉን ፡ መልክ ፡ ይልቁንም ፡ ይህን ፡ መዝገበ ፡ ፊደል ፡ ከሥር ፡ እስከ ፡ ጫፉ ፡ በቍጥር ፡ ባጠራር ፡ በጥፈት ፡ በንባብ ፡ ለይቶ ፡ ጠንቅቆ ፡ ካወቁት ፡ ሌላው ፡ አያቅትም ፤ መጽሐፍን ፡ ኹሉ ፡ አለችግር ፡ ማንበብና ፡ መጣፍ ፡ ይቻላል ። ፊደልንም ፡ መቍጠር ፡ ማስቈጠር ፤ መማር ፡ ማስተማር ፡ የሚገባ ፤ በቃል ፡ በጥፈት ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ዕውርና ፡ ሽባ ፡ ካልኾኑ ፡ በቀር ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ መማር ፡ አይበቃም ፤ መምሩንም ፡ ተማሪውንም ፡ ጐደሎ ፡ ያሰኛል ። ሠምና ፡ ፈትል ፡ ካልተዋሐዱ ፡ በየራሳቸው ፡ ብርሃን ፡ እንደሌላቸው ፤ ኹለተኛም ፡ መብል ፡ ያለ ፡ መጠጥ ፡ እንጀራ ፡ ያለወጥ ፡ ብቻ ፡ ብቻውን ፡ እንዳያጠግብና ፡ እንዳይጣፍጥ ፤ ትምርትም ፡ ጥፈት ፡ ከሌለበት ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። የግእዝም ፡ ቋንቋ ፡ ትምርቱና ፡ ኀይሉ ፡ የደከመበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ዐውቆታል ። (ተረት) ፤ አይጥፍ ፡ መምር ፡ ክንፍ ፡ የለው ፡ ንስር ፤ አይጥፍ ፡ ተማሪ ፡ ክንፍ ፡ የለው ፡ በራሪ ፤ አይጥፍ ፡ ደብተራ ፡ ክንፍ ፡ የለው ፡ አ

ይህ ፡ ፊደል ፡ ለተማሪና ፡ ለቈጣሪ ፡ እንዳሞር ፡ ባሕራሳብ ፡ በሹልክልኪት ፡ መንገድ ፡ ቶሎ ፡ እንዲገኝና ፡ እንዲታወቅ ፤ ትምርቱም ፡ ልጅ ፡ እንዳያስቅቅ ፡ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ ክፍል ፡ ተክፍሎ ፡ በስልት ፡ በስልቱ ፡ ተጥፏል ። አንዳንዲቱን ፡ ክፍል ፡ ይልቁንም ፡ ሥሩን ፡ መዠመሪያውን ፡ ክፍል ፡ ሳያበስሉና ፡ ሳያስተውሉ ፡ እጅ ፡ ሳያደርጉ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ማለፍ ፡ አይገባም ፤ አለዚያ ፡ ግን ፡ ትምርቱና ፡ የትምርቱ ፡ ሥራ ፡ ፈጽሞ ፡ ግብዝ ፡ ይኾናል ።

በፊደሉም ፡ ውስጥ ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ የፊደሉን ፡ ጠባይ ፡ የሚያስታውቅ ፤ መምር ፡ ለተማሮች ፡ የማያነበውና ፡ ኋላም ፡ ተማሮች ፡ የማያነቡት ፡ እንደ ፡ ዚቅና ፡ እንደ ፡ ስርዋጽ ፡ ኹኖ ፡ የገባ ፡ ዐማሞር ፡ ቍርጫኝ ፡ የቃል ፡ ተውሳክ ፡ ሐተታና ፡ ታሪክ ፡ አለ ። ዳግመኛም ፡ ፊደሉና ፡ የፊደሉ ፡ ንዝ ፡ ሲጨረስ ፡ በፊደላዋሪያ ፡ ፈንታ ፡ ሕፃናት ፡ ሲማሩት ፡ የሚገባ ፡ ንባብና ፡ ምስጢር ፡ የሚያስታውቅ ፤ ከሥነ ፡ ፍጥረት ፡ እስካሥርቱ ፡ ቃላት ፡ በታናናሽ ፡ ክፍል ፡ የተጣፈ ፡ ዐማሞር ፡ ቃል ፡ አለ ። ሦስተኛም ፡ ካሥርቱ ፡ ቃላት ፡ ቀጥሎ ፡ ለእጅ ፡ መኪና ፡ የሚኾን ፡ እንደ ፡ ጽርእና ፡ እንደ ፡ ላቲን ፡ በዋየል ፡ የሚሄድ ፡ ሦስተኛ ፡ ፊደል ፡ ከነመቅድሙና ፡ ከንጓዙ ፡ አለ ። አራተኛም ፡ ከርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ለሒሳብ ፡ ትምርት ፡ የሚጠቅሙ ፤ ኤውሮፖች ፡ ታብል ፡ የሚሏቸው ፡ አራቱ ፡ የቍጥር ፡ ዐውዶች ፡ ወይም ፡ መደቦችና ፡ ሰንጠረዦች ፡ በዚሁ ፡ በግእዙ ፡ አኃዝ ፡ ተጥፈዋል ። ዐምስተኛም ፡ በመጨረሻው ፡ ዐሞር ፡ ጒልቄ ፡ ዘመንና ፡ ውዳሴ ፡ እምላክ ፡ አለ ። መላው ፡ የክፍሎች ፡ ቍጥር ፡ ጌታን ፡ ይከተሉት ፡ በነበሩ ፡ በቅዱሳት ፡ አንስት ፡ ምሳሌ ፡ ፶፮ ፡ ነው ። ሥራውም ፡ ንባብንና ፡ ትርጓሜን ፡ ባንድ ፡ ዐይነት ፡ ፊደል ፡ መጣፍ ፤ ወይም ፡ አዛውሮ ፡ ትርጓሜን ፡ በጒልሕ ፤ ንባብን ፡ በረቂቅ ፡ ማተም ፡ ባዋቆችና ፡ በሠራተኞች ፡ ዘንድ ፡ ሥራን ፡ የሚያስነቅፍ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ፊደሉና ፡ የግእዙ ፡ ቃል ፡ ንባብ ፡ እንደ ፡ መኾን ፡ ስላባትነቱ ፡ በጒልሕ ፤ ያማርኛውም ፡ ቃል ፡ ትርጓሜ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ስለ ፡ ልጅነቱ ፡ በረቂቅ ፡ ፊደል ፡ ተሠርቷል ።

ይህም ፡ ፊደል ፡ የተጣፈበት ፡ ምክንያት ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የሚመጣ ፡ የግእዝን ፡ ቃላት ፡ በየፊደሉ ፡ ለይቶ ፡ ንባቡን ፡ በጥፈት ፡ የሚያሰናዳ ፤ ፍችውንም ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ ብዙ ፡ ምስክር ፡ ሰጥቶ ፡ በብዙ ፡ ዐማርኛ ፡ የሚያስረዳ ፤ ያማርኛንም ፡ ቃል ፡ ከግእዝ ፡ ቃላት ፡ የሚያዛምድና ፡ የሚያዋሕድ ፡ ሌላ ፡ ሐዲስ ፡ ታላቅ ፡ መጽሐፈ ፡ ግስ ፡ አለና ፤ ለዚያ ፡ ለመጪው ፡ መሪ ፡ ፊታውራሪ ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ እንዲኾን ፡ ነው ። መቅድሙም ፡ ከዚያኛው ፡ መቅድም ፡ ተለቅሞ ፡ ተቀሥሞ ፡ በክፍል ፡ የመጣ ፡ ነው ። ፊደልነቱም ፡ በመዠመሪያው ፡ ገጽ ፡ ለውሉደ ፡ ጽባሕ ፡ ወሠርክ ፡ እንደ ፡ ተባለ ፤ ለልጅም ፡ ላዋቂም ፡ ለኹሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለልጅ ፡ ብቻ ፡ አይዶለም ፤ እንዲያውም ፡ ስለ ፡ ብርታቱ ፡ ከልጆች ፡ ይልቅ ፡ ላዋቆች ፡ ይጠቅማል ። መብልዕስ ፡ ጽኑዕ ፡ ለልሂቅ ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ (ዕብ፭ ፡ ፲፬) ። ለልጅ ፡ ያሉትም ፡ ላዋቂ ፡ መትረፉ ፡ ከጥንት ፡ የቈየ ፡ ነው ። (ተረት) ፤ በልጅ ፡ አመካኝቶ ፡ ይበሏል ፡ ዐንጒቶ ።

| (፩) ፊደላት ፡ ግእዝ ፡ በበ ፡ አሐዱ ። አንዳንዱ ፡ ፊደል ፡ ግእዝ ፡ ግእዙ ፡ ብቻ ። | | (፪) በበ ፡ ክልኤቱ ። ኹለት ፡ ኹለቱ ። | ዲቃሎችና ፡ ዐማርኞች ፡ ካሥራንዱ ፡ የተወለዱ ። |
|---|---|---|---|
| አ | መ | አበ | ጐኈ |
| በ | ነ | ገደ | ኰቈ |
| ገ—ጐ | ሠ | ሀወ | ደጀ |
| ደ | ዐ | ዘሐ | ዘዠ |
| ሀ | ፈ | ኀጠ | ጠጨ |
| ወ | ጸ | የከ | ከኸ |
| ዘ | ፀ | ለመ | ነኘ |
| ሐ | ቀ—ቈ | ነሠ | ሰሸ |
| ኀ—ኈ | ረ | ዐፈ | ተቸ |
| ጠ | ሰ | ጸፀ | ጀዠ |
| የ | ተ | ቀረ | ጨ ኸ |
| ከ—ኰ | ጰ | ሰተ | ኘ(ኛ) |
| ለ | ፐ | ጰፐ | ሸቸ |

## (፫)

## አኃዝ ፡ አው ፡ ኍልቍ ።

ቍጥር ፡ ካንድ ፡ እስካሥር ፡ በሦስት ፡ ዐይነት ፡ ፊደል ።

(ግእዝና ፡ ጽርእ ፡ ህንድ) ።

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | በ | ገ | ደ | ሀ | ወ | ዘ | ሐ | ጠ | የ | ። |
| ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | ፯ | ፰ | ፱ | ፲ | ። |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | |

## (፬)

## ስመ ፡ ሰብዑ ፡ ፊደላት ፡ ወኍላቌሆን ።

የሰባቱ ፡ ፊደላት ፡ ስምና ፡ ቍጥር ፡ በግእዝና ፡ ባማርኛ ።

| | |
|---|---|
| አልፍ ፡ አ ። | ዐይን ፡ ዐ ። |
| አ—ግእዝ ፡ | ዐ—፩ኛ ። |
| ኡ—ካዕብ ፡ | ዑ—፪ኛ ። |
| ኢ—ሣልስ ፡ | ዒ—፫ኛ ። |
| ኣ—ራብዕ ፡ | ዓ—፬ኛ ። |
| ኤ—ኃምስ ፡ | ዔ—፭ኛ ። |
| እ—ሳድስ ፡ | ዕ—፮ኛ ። |
| ኦ—ሳብዕ ፡ | ዖ—፯ኛ ። |

ከአልፉ ፡ አ ፡ ድምጥ ፡ የዐይኑ ፡ ዐ ፡ ድምጥ ፡ ይበረታል ፤ አልፍ ፡ አ ፡ እንደ ፡ ሆይ ፡ ሀ ፡ ነው ፤ ዐይን ፡ ዐ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሐውት ፡ ሐ ፡ ይነገራል ፤ ኹሉም ፡ የጕረሮ ፡ ናቸው ፤ ጸታቸውን ፡ ባ፲፩ኛው ፡ ክፍል ፡ ተመልከት ። መዋረሳቸውም ፡ ባ፲ኛው ፡ ክፍል ፡ ተጥፏል ።

## (፫)

# ጠባይዐ ፡ ሰብዑ ፡ ፊደላት ።

### የሰባቱ ፡ ፊደላት ፡ ጠባይ ።

### (ታ ሪ ክ) ።

ከካዕብ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ያሉ ፡ ስድስት ፡ ስድስቱ ፡ ፊደሎች ፡ ጸና ፡ ፐም ፡ ሳይቀሩ ፡ ኋላ ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ በፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ መጻሕፍት ፡ ከጽርእ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ሲመለሱ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተጨምረዋል ። ከዚያ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ በመዠመሪያው ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ጣፍነው ፡ ግእዝ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ከግእዝ ፡ በቀር ፡ ነቍጣ ፡ ቅጥል ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ፊደል ፡ አልነበረም ፤ ቋንቋውም ፡ ስሙን ፡ ከፊደሉ ፡ ነሥቶ ፡ ግእዝ ፡ የተባለ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ይባላል ። ጸና ፡ ፐም ፡ ኹለቱ ፡ ስላንድ ፡ ናቸው ፤ ጰ ፡ ሲላላ ፡ ፐ ፤ ፐ ፡ ሲጠብቅ ፡ ደግሞ ፡ ጰ ፡ ይባል ፡ ነበረ ፡ ይሉናል ፤ የተጨመሩም ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ለመስማማት ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ሲታወቅ ፡ በጸና ፡ በፐ ፡ የሚጣፍ ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በጽርእና ፡ በቅብጥ ፡ በሮማይስጥ ፡ ፐ ፡ ኹኖ ፡ ይገኛል ። ጰ ፡ የሳባ ፡ ፊደል ፡ ይባላል ፤ ፐም ፡ የጽርእ ፡ ተ ፡ ነው ፤ ፐ ፡ መባሉ ፡ በግእዝ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ አይዶለም ። ፐ ፡ በዕብራይስጥም ፡ አለ ፤ የፈ ፡ ድርብ ፡ ነው ፤ አለነቍጣ ፡ ፈ ፡ የሚባለው ፡ ነቍጣ ፡ ሲኾንበት ፡ ፐ ፡ ይባላል ።

### ( ጠ ባ ይ ) ።

ግእዝና ፡ ሳድስ ፤ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፤ ሣልስና ፡ ኃምስ ፤ እሊህ ፡ ሦስቱ ፡ ጥንድ ፡ ፊደሎች ፡ ኹለት ፡ ኹለቱ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተወራራሾች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በሸማኔ ፡ ዝሓ ፡ ይመስላሉ ። ጥንዱ ፡ ዝሓ ፡ በኹለት ፡ ምሕን ፡ ተጠልፎ ፡ ካርቡ ፡ ጥርስ ፡ ካንዳንዲቱ ፡ ጕድጓድ ፡ ቀበሎ ፡ እየገባ ፡ ሲሠራ ፡ በመቂናጦና ፡ በመርገጫ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ እንዲል ፡ እነዚህም ፡ እንደዚያ ፡ ናቸው ፤ የድምጣቸው ፡ ስልት ፡ ድፋትና ፡ ቅናት ፡ ተብሎ ፡ በኹለት ፡ ስም ፡ ይጠራል ። የግእዝ ፡ የኃምስ ፡ የሳብዕ ፡ ስልት ፡ ቅናት ፤ የካዕብ ፡ የሣልስ ፡ የሳድስ ፡ ስልት ፡ ድፋት ፡ ይባላል ፤ በዚሁም ፡ ዐቢይና ፡ ንኡስ ፡ አለበት ። ራብዕ ፡ ግን ፡ አጣማጅ ፡ የሌለው ፡ ቀንጃ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የድምጡ ፡ ስልት ፡ እንዳራራይ ፡ ዜማ ፡ ለብቻው ፡ ነው ፤ በጣም ፡ አፍ ፡ ያበከፍታል ፤ ቃል ፡ ያገነታል ፤ በሴት ፡ አንቀጽ ፡ ላንድም ፡ ለብዙም ፡ ለሩቆች ፡ ብቻ ፡ ዝርዝር ፡ ይኾናል ። ግእዝ ፡ በጥቂቱ ፡ አፍ ፡ ያስከፍታል ፤ እንደ ፡ ራብዕ ፡ ቃል ፡ አያገነታም ፤ ሳድስም ፡ የግእዝ ፡ ወራሽ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ እንደ ፡ ትንፋሽ ፡ ነው ፤ ጕህና ፡ የለውም ። ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ እንደ ፡ ፉጨት ፡ ናቸው ፤ አፍን ፡ ማጥበብና ፡ ማሾል ፡ ማሞጥሞጥ ፡ ይስማማቸዋል ። ሣልስ ፡ እንደ ፡ ሣቅ ፡ ጥርስ ፡ ያስፈለቅቃል ፤ ኃምስ ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ አፍ ፡ ያስለቅቃል ። የቅጥላቸው ፡ ጠባይ ፡ ከየት ፡ መጣውና ፡ ሐተታው ፡ በሦስተኛው ፡ ፊደል ፡ ተጥፏል ።

---

(፯)

## ኵሎን ፡ ፊደላተ ፡ ግእዝ ፡ በበ ፡ ሰብዑ ።

መላው ፡ የግእዝ ፡ ፊደሎች ፡ ሰባት ፡ ሰባቱ ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

## (፯)

## ደ ቃ ል ው ።

### ዲ ቃ ሎ ች ።

ከነዚህ ፡ ከኻያ ፡ ስድስቱ ፡ ደግሞ ፡ አስቀድመን ፡ በመዠመሪያው ፡ ክፍል ፡ እንዳሳየነ ፤ መልካቸውንና ፡ ድምጣቸውን ፡ አካሄዳቸውን ፡ ለውጠው ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ትተው ፡ በሕጹጽነት ፡ የሚጣፉ ፡ ሕጹጻን ፡ ዲቃሎች ፡ ያሏቸው ፡ አራት ፡ ፊደሎች ፡ አሉ ። ፊደሎቹና ፡ ዲቃሎቹም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ጉንከቀና ፡ ጐኰኲቈ ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ገ) | ጐ | ጒ | ጓ | ጔ | ጕ |
| ኀ) | ኈ | ኊ | ኋ | ኌ | ኍ |
| ከ) | ኰ | ኲ | ኳ | ኴ | ኵ |
| ቀ) | ቈ | ቊ | ቋ | ቌ | ቍ |

ካዕብ ፡ መተዋቸው ፡ የካዕቡን ፡ ቃል ፡ ዐምስቱ ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ደረቡት ፡ ነው ፤ ባምስቱ ፡ ኹሉ ፡ የካዕብ ፡ ድምጥ ፡ አለ ፤ ይህነንም ፡ የቅጥላቸው ፡ መንታነት ፡ ያስረዳል ። ሳብዕ ፡ መተዋቸውም ፡ የሳብዑን ፡ ቃል ፡ ግእዛቸው ፡ ስለ ፡ ደረበው ፡ ነው ፤ በግእዛቸው ፡ ላይ ፡ በያንዳንዱ ፡ ኹሉ ፡ የካዕብና ፡ የሳብዕ ፡ ድምጥ ፡ አለ ፤ ይህነንም ፡ የቅጥሉ ፡ ቀለበትነት ፡ እንደነሆሎፎ ፡ እንደነሮቆቶ ፡ መኾኑ ፡ ያስረዳል ። ያምስቱ ፡ ኹሉ ፡ ቅጥላቸው ፡ መንታና ፡ ቀለበት ፡ መኾኑ ፡ የድምጣቸውን ፡ ቱሳሔና ፡ ጉሠት ፡ ቅልቅልነት ፡ ያሳያል ። ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ ሐተታ ፡ በሦስተኛው ፡ ፊደል ፡ ተመልከት ፤ ቦታው ፡ ከዚያ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በሰፊው ፡ ተጥፏል ።

ዳግመኛም ፡ በጓኋኳቋ ፡ አምሳል ፡ ካሥራ ፡ ኹለቱ ፡ የግእዝ ፡ ፊደሎች ፡ (በደዘጠለመነፈጸረሰተ) ፡ ከየራብዓቸው ፡ የተዴቀሉ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ራብዖች ፡ ብቻ ፡ ይገኛሉ ። ከነዚያውም ፡ አራቱ ፡ እንደነዚህ ፡ ለግእዝም ፡ ላማርኛም ፡ ቃል ፡ ይስማማሉ ። ስምንቱ ፡ ግን ፡ ዐማርኞች ፡ ናቸው ፤ ካማርኛውም ፡ ፊደሎች ፡ ከሰባቱ ፡ ራብዕ ፡ የተዴቀሉ ፡ ሰባት ፡ ራብዖች ፡ አሉና ፤ ኹሉም ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ኹነው ፡ ባሥረኛው ፡ ክፍል ፡ ከናገባባቸው ፡ ተጥፈዋል ።

## (፫)

### በበ ፡ አሐዱ ፡ ወበበ ፡ ክልኤቱ ።

ቀንጀና ፡ ቅንጁ ፡ እንደ ፡ መዝመሪያው ።

| | |
|---|---|
| አ ፡ ኡኢ ፡ ኣኤ ፡ እኦ ። | ለ ፡ ሉሊ ፡ ላሌ ፡ ልሎ ። |
| በ ፡ ቡቢ ፡ ባቤ ፡ ብቦ ። | መ ፡ ሙሚ ፡ ማሜ ፡ ምሞ ። |
| ገ ፡ ጉጊ ፡ ጋጌ ፡ ግጎ ። | ነ ፡ ኑኒ ፡ ናኔ ፡ ንኖ ። |
| ጐ ፡ ጒጓ ፡ ጔጕ ፡ — ። | ሠ ፡ ሡሢ ፡ ሣሤ ፡ ሥሦ ። |
| ደ ፡ ዱዲ ፡ ዳዴ ፡ ድዶ ። | ዐ ፡ ዑዒ ፡ ዓዔ ፡ ዕዖ ። |
| ሀ ፡ ሁሂ ፡ ሃሄ ፡ ህሆ ። | ፈ ፡ ፉፊ ፡ ፋፌ ፡ ፍፎ ። |
| ወ ፡ ዉዊ ፡ ዋዌ ፡ ውዎ ። | ጸ ፡ ጹጺ ፡ ጻጼ ፡ ጽጾ ። |
| ዘ ፡ ዙዚ ፡ ዛዜ ፡ ዝዞ ። | ፀ ፡ ፁፂ ፡ ፃፄ ፡ ፅፆ ። |
| ሐ ፡ ሑሒ ፡ ሓሔ ፡ ሕሖ ። | ቀ ፡ ቁቂ ፡ ቃቄ ፡ ቅቆ ። |
| ኀ ፡ ኁኂ ፡ ኃኄ ፡ ኅኆ ። | ቈ ፡ ቊቋ ፡ ቌቍ ፡ — ። |
| ኈ ፡ ኊኋ ፡ ኌኍ ፡ — ። | ረ ፡ ሩሪ ፡ ራሬ ፡ ርሮ ። |
| ጠ ፡ ጡጢ ፡ ጣጤ ፡ ጥጦ ። | ሰ ፡ ሱሲ ፡ ሳሴ ፡ ስሶ ። |
| የ ፡ ዩዪ ፡ ያዬ ፡ ይዮ ። | ተ ፡ ቱቲ ፡ ታቴ ፡ ትቶ ። |
| ከ ፡ ኩኪ ፡ ካኬ ፡ ክኮ ። | ጰ ፡ ጱጲ ፡ ጳጴ ፡ ጵጶ ። |
| ኰ ፡ ኲኳ ፡ ኴኵ ፡ — ። | ፐ ፡ ፑፒ ፡ ፓፔ ፡ ፕፖ ። |

## (፱)

### ያማርኛ፡ፊደል፡ከነጓዙ።

«ዐማርኛ፡ማለት፡ያማራ፡ቋንቋ፤ዐማራም፡ማለት፡(ዐም፡ሐራ)፡ነጻ፡ሕዝብ፡ጨዋ፡ሕዝብ፡ነጻነት፡ያለው፡ባላባት፡ጥሩ፡የሰው፡ልጅ፡ማለት፡ነው። ግዑዝ፡ አግዓዚ፡ ከማለት፡ጋራ፡ይስማማል፤ዐም፡የዕብራኒ፡የሶርያኒ፤ሐራ፡የኹሉ፡ነው። አንዳንድ፡ታሪክ፡ዐምሐራ፡ማለት፡ሕምያር፡ሐሜር፡ከማለት፡መጥቷል፡ይላል። ሕምያር፡ከየመን፡ፈልሶ፡ወዳፍሪቃ፡መሬት፡የመጣ፡ሴማዊ፡ሕዝብ፡ነው፤ሐሜርም፡የጡብና፡የሸክላ፡ጭቃ፡ነው፤የኹለቱም፡ፍች፡ቀይሕ፡ቀይሓዊ፡ማለት፡ነው፤ጎምራዊ፡እንደ፡ማለት። ሌላም፡ አፈታት፡ ይኖረዋል። አማራ፡ ተብሎ፡ በአልፍ፡ ሲጣፍ፡ ግን፤ ውብ፡ ዕውቅ፡ ዐዋቂ፡ ባለአእምሮ፡ ያሰኛል»። ምሉ፡ ዐማርኛ ፡ያላቸው፡ ፊደሎች፡ ሰባት፡ ብቻ፡ ናቸው፤ለቀሩት፡ፊደሎች፡ከራብዓቸው፡በቀር፡ያማርኛ፡ ቅጥል፡ የላቸውም። ሰባት፡ያልናቸውም፡ አስቀድመን፡በኹለተኛው፡ ክፍል፡የጣፍናቸው፡ ደዘጠ(ጸፀ)ከነሰተ፡ ናቸው።

| ሰባት፡ሰባቱ። | ቀንጀና፡ቅንጁ። |
| --- | --- |
| ጀ ጁ ጂ ጃ ጄ ጅ ጆ | ጀ፡ ጁጂ፡ ጃጄ፡ ጅጆ። |
| ዠ ዡ ዢ ዣ ዤ ዥ ዦ | ዠ፡ ዡዢ፡ ዣዤ፡ ዥዦ። |
| ጨ ጩ ጪ ጫ ጬ ጭ ጮ | ጨ፡ ጩጪ፡ ጫጬ፡ ጭጮ። |
| ኸ ኹ ኺ ኻ ኼ ኽ ኾ | ኸ፡ ኹኺ፡ ኻኼ፡ ኽኾ። |
| ኘ ኙ ኚ ኛ ኜ ኝ ኞ | ኘ፡ ኙኚ፡ ኛኜ፡ ኝኞ። |
| ሸ ሹ ሺ ሻ ሼ ሽ ሾ | ሸ፡ ሹሺ፡ ሻሼ፡ ሽሾ። |
| ቸ ቹ ቺ ቻ ቼ ች ቾ | ቸ፡ ቹቺ፡ ቻቼ፡ ችቾ። |

ጨ፡የወጣ፡ከጠና፡ከጸ(ፀ)፡ነው፤ከጠ፡ብቻ፡አይደለም፤በግእዝ፡ጸ—ፀ፡የሚባለው፡ባማርኛ፡ጠና፡ ጨ፡ ይኾናል። (ማስረጃ)፤ ጸመ፡ ጠመ፤ ጸልአ፡ጠላ። ጸልመ፡ጨለመ፤ጸፈነ፡ጨፈነ። ጸኈር፡ጠኈር፤ ጭገር፤ጼው፡ ጨው፤ጸርቅ፡ ጨርቅ። ፀመደ፡ ጠመደ፤ፀመረ፡ጨመረ፤ፀበጠ፡ጨበጠ፤የመሰለው፡ኹሉ።

## የዠና ፡ የጨ ፡ የኸ ፡ አጣጣፍ ።

የዠ ፡ አጣጣፍ ፡ ጥንቱ ፡ እንደዚህ ፡ ነበረ ፡ ዠ.ዠ ፤ ዛሬም ፡ በባላገር ፡ እንዲሁ ፡ ይጣፋል ፤ ፈረንጆችም ፡ በዥ ፡ ፈንታ ፡ ይህን ፡ ዠ ፡ እየጠፉ ፡ አለመልኩና ፡ አለስሙ ፡ ሳድስ ፡ ይሉታል ። ዐይናሞችና ፡ ልባሞች ፡ ግን ፡ ቅጥሉ ፡ በላይ ፡ በታች ፡ ሲኾን ፡ ሣልሱ ፡ ኃምሱ ፡ አይለይምና ፤ በላይ ፡ ብቻ ፡ ይኹን ፡ ብለው ፡ የታችኛውን ፡ አስቀርተውታል ። በዠ ፡ ፈንታ ፡ ጀን ፡ ጅብ ፡ ጀር ፡ ቈንጆ ፡ ጆግና ፡ ጀመረ ፡ እያሉ ፡ መጣፍ ፡ አይገባም ። በጂ ፡ ፈንታ ፡ ደግሞ ፡ ዠን ፡ ልዥ ፡ ውላዥ ፡ ቅናዥ ፡ ፍናዥ ፡ እያሉ ፡ የሚጥፉ ፡ አሉ ። የጨም ፡ አጣጣፍ ፡ ቅጥሉ ፡ በኹለት ፡ እግሮቹ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ በሦስተኛ ፡ እግሩ ፡ እንዳባቱ ፡ ነው ፤ ከካዕብና ፡ ከሣልስ ፡ ከኃምስ ፡ ምልክት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ቅጥል ፡ አይገባበትም ። በሦስተኛው ፡ እግሩ ፡ መቀጠልና ፡ ኃምሱን ፡ ጬ ፡ ማለት ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ፤ የቅጥሉ ፡ ገሮ ፡ ወይም ፡ ቀለበት ፡ እንደ ፡ ጕኈኰቈ ፡ ግእዝ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ሎ ፡ ሳብዕ ፡ ቢያሰኘው ፡ እንጂ ፡ ኃምስ ፡ አያሰኘውም ። የኸም ፡ አጣጣፍ ፡ በጕንደሮች ፡ ዐዋጅ ፡ ከካዕብ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ኹ ኺ—ኾ ፡ የሀ(ሐን) ፡ ቤት ፡ ነውና ፤ ለከ ፡ ከግእዙ ፡ በቀር ፡ ምሉ ፡ ዐማርኛ ፡ የለውም ፡ ይባላል ፤ ስሙንም ፡ ቀንጃ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ድሆ ፡ (ኸ) ፡ ይሉታል ። ዐዋጁም ፡ ስሙም ፡ እምነበ ፡ አልቦ ፡ የመጣና ፡ ባለማስተዋል ፡ የወጣ ፡ ነው ፤ የጸሐፍቱ ፡ ልብ ፡ ያማርኛን ፡ ጠባይ ፡ መንገዱንና ፡ አካሄዱን ፡ መሣሪያ ፡ እንደሌለው ፡ እንደ ፡ ተርታ ፡ ሐኪም ፡ አጥብቆ ፡ አጥልቆ ፡ አልመረመረውም ። ማስረጃውን ፡ ኋላ ፡ በቦታው ፡ እናመጣዋለን ፡ (ገጽ ፡ ፲፯) ።

---

(፩)

ብኋኋቋ ፡ እንጸር ፡ ከግእዙም ፡ ካማርኛውም ፡ የሚገኙ ፡ አንዳንድ ፡ ዲቃሎች ፡ ራብዖች ፡ ብቻ ።

ከ ግ እ ዙ ።

ባ ዳ ዛ ጣ ላ ማ ና ፋ ጻፃ ራ ሳ ታ ።

ቧ ዷ ዟ ጧ ሏ ሟ ኗ ፏ ጿ ሯ ሷ ቷ ።

ካ ማ ር ኛ ው ።

ጃ ዣ ጫ ኻ ኛ ሻ ቻ ።

ጇ ዧ ጯ ዃ ኟ ሿ ቿ ።

እነዚሁም ፡ በሩቅ ፡ ሴት ፡ ዝርዝርና ፡ በስም ፡ በግብር ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ ይገባሉ ።

| (ስም) ፡ | | (ዝርዝር) ፡ | | (ግብር) ፡ |
|---|---|---|---|---|
| ልብ ፡ | — | ልቧ ፡ | — | ዐስቧል ። |
| ሆድ ፡ | — | ሆዷ ፡ | — | ወዷል ። |
| ወዝ ፡ | — | ወዟ ፡ | — | ተንብዟል ። |
| ወጥ ፡ | — | ወጧ ፡ | — | ጣፍጧል ። |
| ባል ፡ | — | ባሏ ፡ | — | ታድሏል ። |
| ስም ፡ | — | ስሟ ፡ | — | ተሰይሟል ። |
| ጐን ፡ | — | ጐኗ ፡ | — | ተጠግኗል ። |
| አፍ ፡ | — | አፏ ፡ | — | ለፍልፏል ። |
| ገጽ ፡ | — | ገጿ ፡ | — | ደንግጿ(ፃ)ል ። |
| ወር ፡ | — | ወሯ ፡ | — | ተዝምሯል ። |
| ራስ ፡ | — | ራሷ ፡ | — | ርሷል ። |
| ፊት ፡ | — | ፊቷ ፡ | — | በርቷል ። |
| ወዳጅ ፡ | — | ወዳጇን ፡ | — | ይዋጇል ። |
| ዐጋዥ ፡ | — | ዐጋዧን ፡ | — | ይቤዧል ። |
| አገጭ ፡ | — | አገጯን ፡ | — | ይገጯል ። |
| አኳኋን፡ | — | አኳኋኗ ፡ | — | ትኳናም ። |
| ዐዳኝ ፡ | — | ዐዳኟን ፡ | — | ይዳኟል ። |
| ከሳሽ ፡ | — | ከሳሿን ፡ | — | ይሸሿል ። |
| ዐማች ፡ | — | ዐማቿን ፡ | — | ያስመቿል ። |

## የሯና ፡ የሯ ፡ አጣጣፍ ።

ርያ ፡ ሪያ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሯ ፡ ወይም ፡ ሯ ፡ (መኰሯ ፡ ሯ ፤ መዝመሯ ፡ ሯ) ፡ ማለት ፡ መልኩም ፡ ድምጡም ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ፤ ለረ ፡ ከራብዑ ፡ በቀር ፡ ምሉ ፡ ያማርኛ ፡ ቅጥይ ፡ የለውም ፤ አለመኖሩም ፡ ከቧ ፡ እስከ ፡ ቷ ፡ ባሉት ፡ ባሥራንድ ፡ ወንድሞቹ ፡ ይታወቃል ፤ ራብዑም ፡ ሯ ፡ በዝርዝር ፡ ሲጣፍ ፡ ሩዋ ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፡ ርያ ፡ አያሰኝም ። ስላልተለመደ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሻና ፡ ሧ ፡ ጿና ፡ ሯ ፡ እንደነኝ ፡ ከግእዝ ፡ ቃላት ፡ ሊገቡ ፡ ይቻላል ። (ምሳሌ ፤ ተሻቅሐ ፡ አስተሻቅሐ ፤ ምሧዕ ፡ መሧዕት ፤ ምጿት ፡ ምሯጽ ፡ ስሯጽ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ከቧ ፡ እስከ ፡ ቷ ፡ ያሉ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ራብዖች ፡ ፊደልነታቸው ፡ እንደ ፡ ጓኳኳቋ ፡ ለግእዝና ፡ ላማርኛ ፡ ለኹለቱም ፡ ሲኾን ፡ ከነዚህ ፡ ካራቱ ፡ (ሻሧጿሯ) ፡ በቀር ፡ ለስምንቱ ፡ ግእዛዊ ፡ ቃል ፡ አይገኝምና ፤ ቢገኝም ፡ ጥቂት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ወዳማርኛ ፡ ተቈጥረዋል ።

ላማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ለፊደሉና ፡ ለቃሉ ፡ አባቱና ፡ እናቱ ፡ ስፌዱ ፡ ወንፊቱ ፡ ግእዝ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ትምርቱ ፡ ብቻውን ፡ ሊነገር ፡ አይገባም ፤ ቢነገርም ፡ ጥፈቱና ፡ ቋንቋው ፡ አይጠራም ፤ ጸያፉ ፡ አይከተትም ፤ ትምርቱና ፡ ስልቱ ፡ ፍጹም ፡ ዐልማ ፡ ይኾናል ።

ያማርኛም ፡ ስልት ፡ እንደ ፡ ሕዝቡ ፡ አራት ፡ ክፍል ፡ ነው ፤ አንደኛው ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፤ ኹለተኛው ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሦስተኛው ፡ የነጋዴ ፤ አራተኛው ፡ የባላገር ። የቤተ ፡ ክህነት ፡ ዐማርኛ ፡ በሰዋስው ፡ ተመሥርቶ ፡ ባገባብ ፡ የታነጠ ፡ በትርጓሜ ፡ የተቀረጠ ፡ በግእዝ ፡ አበባ ፡ የተጌጠ ፡ ነው ፤ ከግእዝ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ባዕድ ፡ ቋንቋ ፡ አይገባበትም ። የቤተ ፡ መንግሥትም ፡ ዐማርኛ ፡ የግእዝ ፡ ትምርት ፡ ስላለበትና ፡ ሠራተኞቹ ፡ የካህናት ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ እጅግ ፡ ስብቅል ፡ ነው ፤ ቃላትን ፡ ኹሉ ፡ እግዜር ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ በማሳጠርና ፡ በማሳመር ፡ በማከናወን ፡ ይነገራል ። ዛሬ ፡ ግን ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ ጌቶች ፡ በማለት ፡ ጸያፍ ፡ ገብቶበታል ፤ ያንቱታ ፡ ቃል ፡ ካንቀጽ ፡ በቀር ፡ አካል ፡ አያበዛም ፤ ይህም ፡ ጌታ ፡ በሉ ፡ ጠጡ ፤ ጌታ ፡ መጡ ፡ ሄዱ ፡ ማለቱን ፡ ጌቶች ፡ አለማሰኘቱን ፡ ያሳያል ። አንዱን ፡ ሰውዬ ፡ ጌቶች ፡ ካሉት ፡ በዚሁ ፡ አንጻር ፡ ንጉሦች ፡ ራሶች ፡ ደጃዝማቾች ፡ ሊሉት ፡ ይገባል ። የነጋዶችና ፡ የቀራጮች ፡ የመዝገብ ፡ ጣፎች ፡ ዐማርኛ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ንፍሮና ፡ እንደ ፡ ልመና ፡ እኽል ፡ ቅይጥ ፡ ውጥንቅጥ ፡ ነው ፤ ሥራቸውና ፡ መዋሪያቸው ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በሽቀጡና ፡ በንግዱ ፡ ዕቃ ፡ መጠን ፡ በየጊዜው ፡ ሌላ ፡ ባዕድ ፡ ቋንቋ ፡ እየጨመረ ፤ ሳይቸግረውም ፡ እየተበደረ ፤ ያኑም ፡ እያዘናጐለ ፡ ብርዑን ፡ ብዕር ፡ እያለ ፡ በድብልቅልቅነት ፡ ሲጣፍና ፡ ሲነገር ፡ ይኖራል ፤ ዛሬ ፡ እንደምናየው ፡ እንደምንሰማው ፡ ኹሉ ። የባላገሮች ፡ ዐማርኛ ፡ ሥረ ፡ ወጥ ፡ ነው ፤ ጥፈትና ፡ ትምርት ፡ ስላጣ ፡ መታደስ ፡ መለወጥ ፡ መሰብቀል ፡ መሻሻል ፡ የለውም ፤ በዚያው ፡ በዱሮው ፡ በጥንተ ፡ ተፈጥሮው ፡ ይነገራል ። ዐማርኛ ፡ ምንም ፡ እንደ ፡ ገብስ ፡ ስሙና ፡ ጣዕሙ ፡ አንድ ፡ ቢኾን ፡ የሕዝቡ ፡ ክፍል ፡ አራት ፡ ጾታ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ እንዲህ ፡ ባራት ፡ ስልት ፡ ይከፈላል ፤ ይህም ፡ ያንኑ ፡ አንዱን ፡ ገብስ ፡ በሶ ፡ ጥረሾ ፡ ብቅል ፡ ዐሻሮ ፤ ወይም ፡ እንቀት ፡ ገንፎ ፡ ጥሕኒ ፡ ጥሕሎ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ አራቱ ፡ ደግሞ ፡ ታጥፎ ፡ ተደርቦ ፡ ከተምኛ ፡ ባላገርኛ ፡ ይባላል ፤ ያኸውም ፡ መልካም ፡ መናኛ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

(ማስረጃ) ፤ በማርኛና ፡ ትግሬ ፡ ትግሬኛ ፡ ካባታቸው ፡ ከግእዝ ፡ ጕያ ፡ ሳይወጡ ፡ ጀሸኸ ፡
በማለት ፡ ከዐረብና ፡ ከዕብራይስጥ ፤ ዠኘቸ ፡ በማለት ፡ ከሮማይስጥና ፡ ከልጆቹ ፡ ይሰማማሉ ፤
ጨ ፡ በማለት ፡ ግን ፡ ከማንም ፡ ከማን ፡ የማይገጥሙ ፡ ብቸኞች ፡ ናቸው ። ሸን ፡ ከጥንታዊ ፡
ግእዝ ፡ ወርሰውታል ። ጀ ፡ የዐረቦች ፡ ገ ፡ ነው ፤ ያማርኛም ፡ ፈደል ፡ በጀ ፡ ምክንያት ፡ ዐረቢ ፡
ይባላል ፤ ዐረብ ፡ ገ ፡ ሲል ፡ ጂም ፡ ጀመል ፡ ይላል ። ባማርኛም ፡ ገና ፡ ጀ ፡ ይወራረሳሉ ፤ እንጊ
(ጂ)ራ ፤ ግራ ፡ ነገረ ። ግ ፡ ጊ ፡ (ጅ ፡ ጂ) ራፍ ፤ ገረፈ ። አረገ ፡ (ጀ) ። ኸ ፡ የሚባለውም ፡ በዐረብ
ና ፡ በጥንታዊ ፡ ግእዝ ፡ ኀርም ፡ ኀ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ካፍ ፡ አይዶለም ፤ ኄ(ኼ)ር ፡ በማለት ፡ ፈ
ንታ ፡ እልኸይር ፡ እንዲል ፡ (ማር ፡ ይሥ ፡ መቅድም) ። ከን ፡ ኸ ፡ ማለት ፡ የዕብራይስጥና ፡
ያማርኛ ፡ የትግሬኛም ፡ ነው ። የኀና ፡ የኸ ፡ ድምጥ ፡ ምንም ፡ አንድ ፡ ቢኾን ፡ ምስጢራቸው ፡
እንደ ፡ መልካቸው ፡ ልዩ ፡ ነው ፤ ከ ፡ በግእዝ ፡ ላራቱ ፡ ሰራዊት ፡ ለቅርቦች ፡ ብቻ ፡ ዝርዝር ፡ ም
እላድ ፡ እንዲኾን ፡ ኸ ፡ ደግሞ ፡ ባማርኛ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፤ ላንዲቱ ፡ ሴት ፡ ብቻ ፡ ኪ ፡ ተለውጦ ፡
ሽ ፡ ይኾናል ። (ያቀከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን) ፤ ሀወቀኸ ፡ ቀሽ ፡ ቃችኹ ። (አቡከ ፡ ኪ) ፤ አባትኸ ፡
ትሽ ። ባይዘረዝርም ፡ የግእዙን ፡ አሠር ፡ ተከትሎ ፡ (ክልኤት ፤ ሠሉ ፤ እክል) ፤ ኹለት ፡ ሦ-ኹሉ ፤
እኽል ። (ኮነ ፡ ይከውን ፡ ይኩን ፡ ክዊን ፡ ክዋኔ) ፤ ኾነ ፡ ይኾናል ፡ ይኹን ፡ መኾን ፡ አኺ
ኺን ። (ዝ ፡ ዝኬ) ፤ ይህ ፡ ይኸ ፡ እያሰኘ ፡ በዚያው ፡ በገንዘቡ ፡ በኸ ፡ ይጣፋል ። ኸን ፡ ለሀሑን ፡ ለው
ጦ ፡ አባትህ ፡ አወቀህ ፤ ሆን ፡ ሁኔታ ፡ ሑለት ፡ ሁሉ ፡ እህል ፡ እያሉ ፡ መጣፍ ፡ ልማድና ፡ ልብ ፡
ወለድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የቋንቋው ፡ መንገድ ፡ አይዶለም ፤ ነበረ ፤ ደነባ ፤ ገነባ ፡ ብሎ ፡ ወምበር ፡
ደምብ ፡ ግምብ ፡ እምቢ ፡ አምባ ፡ ሳምባ ፡ ላምባ ፡ ግምባር ፡ ማለት ፡ ፍጹም ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤
ነን ፡ በ ፡ ሲከተለው ፡ ወትሮ ፡ እንዲህ ፡ ያሳስታል ። ሌላ ፡ ፊደል ፡ ሲከተለው ፡ ግን ፡ ስንት ፡
አንድ ፡ አንተ ፡ ቺ ፡ ዐንገት ፡ እንደበት ፡ አንጋፋ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ኤን ፡ ሳይንካና ፡
ሳይጕረድ ፡ ጨርሶም ፡ ሳይዋጥ ፡ እያለ ፡ እንደሌለ ፡ ኹኖ ፡ ይነገራል ። እና ፡ ሆም ፡ ሲወራረ
ሱ ፡ አልፍ ፡ አ ፡ ሆይ ፡ ሀን ፡ ብቻ ፤ ዐይን ፡ ዐ ፡ ሐውትንና ፡ ኀርምን ፡ ኹለቱን ፡ ይወርሳል ።
ይህም ፡ ሀለወ ፡ አለ ፤ ሆከ ፡ አወከ ፤ ሀገር ፡ አገር ፤ ሐከመ ፡ ሐገመ ፡ ዐከመ ፡ ዐገመ ፤ ሐረረ ፡
ዐረረ ፤ ኀብረ ፡ ዐበረ ፤ ኀደረ ፡ ዐደረ ፤ ኀጥአ ፡ ዐጣ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። የቋንቋ
ና ፡ የጥፈት ፡ ትምርት ፡ ፍሬውና ፡ ጣዕሙ ፡ የፊደል ፡ አገባብ ፡ ማወቅ ፡ ነው ፤ አጣጣሉን ፡
ብቻ ፡ ማሳመርና ፡ ማከናወን ፡ አያስመሰግንም ። ባለሕጉን ፡ ቋንቋ ፡ ዘእንበለ ፡ ሕግ ፡ እየጣፉ ፡
ማንበብ ፡ ምንም ፡ ለጣፊው ፡ ሕጉ ፡ ቢኾን ፡ በሕግ ፡ ዐዋቆች ፡ ዘንድ ፡ መነቀፉና ፡ ማስነቀፉ ፡
አይቀርም ፤ በግድ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ያሰኛል ። የቋንቋችንም ፡ ሕግ ፡ ሲማዊ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዓለም ፡
ኹሉ ፡ ዐውቆታል ። ይህነንም ፡ ቃል ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ያዩ ፡ ሰዎች ፤ ይልቁንም ፡ ወጣ
ቶችና ፡ ብር ፡ ነቀሎች ፡ ቶሎ ፡ ይረዱት ፡ ይመስለኛል ። ሸ ፡ የሚባለውም ፡ ንጉሡ ፡ ሠ ፡ እንጂ ፡
ሳቱ ፡ ሰ ፡ አልነበረም ፤ ሠውት ፡ ሠና ፡ ሳት ፡ ሰ ፡ በቦታና ፡ በድምጥ ፡ ተዛውረው ፡ ተፋልሰው ፡
አለቦታቸው ፡ ተጥፈዋል ። መፋለሳቸውም ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ፤ ነጋሢ ፡ ነጋሽ ፤ ሢመት ፡

ሹመት ፤ ሦካ ፡ ሾኽ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። በጽርእ ፡ ቋንቋ ፡ ሸ ፡ የሚሉ ፡ ፊደል ፡ ሸ ፡ የሚያሰኝ ፡ ቃል ፡ ስለሌለ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ መጻሕፍትን ፡ ከጽርእ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ሲመልስ ፡ ሸን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አውጥቶት ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በግእዝ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ መጣፋና ፡ መነገሩ ፡ ቀርቷል ። ብርቱ ፡ የነበረው ፡ የፀና ፡ የሐም ፡ ድምጥ ፡ የደከመና ፡ የሰለተ ፡ ጥንቃቄውና ፡ ልዩነቱ ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ አና ፡ እንደ ፡ ሀ ፡ የኾነ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፤ በትግሬና ፡ በትግሪኛ ፡ ግን ፡ እንደዚያው ፡ እንደ ፡ ጥንት ፡ ድምጡ ፡ ይነገራል ።

«ከትግሪኛ ፡ ይልቅ ፡ ትግሬ ፡ ጥሩ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ፤ ለግእዝ ፡ በጣም ፡ ይቀርባል ። ሕዝቡ ፡ ብቻውን ፡ ነዋሪ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በውስጡ ፡ ከሴም ፡ ቋንቋ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ጭማሪ ፡ የለበትም ፤ ግእዝን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ከዐረብና ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ከሱርስት ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ። በግእዝ ፡ መጻሕፍት ፡ የሌሉ ፡ ብዙ ፡ ቃላት ፡ ይገኙበታል ፤ ካማርኛም ፡ ጋራ ፡ የሚገጥም ፡ ብዙ ፡ ቃል ፡ አለበት ። ትግሪኛ ፡ ግን ፡ ባማርኛና ፡ በትግሬ ፡ መካከል ፡ የቆመ ፡ ማእከላዊ ፡ ነው ፤ ፊደሉም ፡ ከትግሬና ፡ ከግእዝ ፡ ይልቅ ፡ ወዳማርኛ ፡ ያደላል ። የንባቡ ፡ መልክ ፡ ተዞሮና ፡ አጣጥሞ ፡ ሲያዩት ፡ ሲሰሙት ፡ የተበላሸ ፡ ግእዝና ፡ ያልተከናወነ ፡ ዐማርኛ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ፤ ግእዝ ፡ የማያውቅ ፡ ዐማራ ፡ ጣዕሙን ፡ ሊቀምሰው ፡ አይችልም ፤ አነጋገሩ ፡ እጅግ ፡ ያስቸግራል» ።

ከካዕብ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ያሉ ፡ ቅጥሎች ፡ ምኖችና ፡ የምን ፡ ምሳሌዎች ፡ እንደ ፡ ኹኑ ፤ የግእዝና ፡ ያማርኛም ፡ ጠባይ ፡ ዐመሉ ፡ ዋየሉ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በሠላሳኛው ፡ ክፍል ፡ በሦስተኛው ፡ ፊደል ፡ በመቅድሙ ፡ ውስጥ ፡ ተመልከት ።

(፲፩)

ፍኖተ ፡ ፊደል ፡ ካልእ ፡ ኅዉሠ ፡ ዘርዕ ፡ ወቱሱሐ ፡ መልከእ ፡ በበ ፡ ስብዕ ፤ ዘያንቅሆሙ ፡ ለውሉድ ፡ እምንዋመ ፡ እበድ ፤ እስመ ፡ ስምዑ ፡ ለአቡጊዳ ፡ እሙን ፡ መጥበቤ ፡ ሕፃናት ፡ አብዳን ፤ በከመ ፡ ጽሑፍ ። ወሑረቱኒ ፡ ስያፍ ፡ አምሳለ ፡ ፍርዝ ፡ (ሰንጠረዥኛ) ።

ኹለተኛ ፡ የፊደል ፡ መንገድ ፡ በስያፍ ፡ አካሄድ ።

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ቡ | ጊ | ዳ | ሄ | ው | ዞ | ነ | ሡ | ዒ | ፋ | ጼ | ቅ | ሮ |
| በ | ጉ | ዲ | ሃ | ዌ | ዝ | ሖ | ሠ | ዑ | ፊ | ጻ | ቄ | ር | ሶ |
| ገ | ዱ | ሂ | ዋ | ዜ | ሕ | ጦ | ዐ | ፉ | ጺ | ቃ | ሬ | ስ | ቶ |
| ደ | ሁ | ዊ | ዛ | ሔ | ጥ | ዮ | ፈ | ጹ | ቂ | ራ | ሴ | ት | ኆ |
| ሀ | ዉ | ዚ | ሓ | ጤ | ይ | ኮ | ጸ | ቁ | ሪ | ሳ | ቴ | ኅ | ፆ |
| ወ | ዙ | ሒ | ጣ | ዬ | ክ | ሎ | ቀ | ሩ | ሲ | ታ | ኄ | ፅ | ጶ |
| ዘ | ሑ | ጢ | ያ | ኬ | ል | ሞ | ረ | ሱ | ቲ | ኃ | ፄ | ጵ | ፖ |
| ሐ | ጡ | ዪ | ካ | ሌ | ም | ኖ | ሰ | ቱ | ኂ | ፃ | ጴ | ፕ | ኦ |
| ጠ | ዩ | ኪ | ላ | ሜ | ን | ሦ | ተ | ኁ | ፂ | ጳ | ፔ | እ | ቦ |
| የ | ኩ | ሊ | ማ | ኔ | ሥ | ዖ | ኀ | ፁ | ጲ | ፓ | ኤ | ብ | ጎ |
| ከ | ሉ | ሚ | ና | ሤ | ዕ | ፎ | ፀ | ጱ | ፒ | ኣ | ቤ | ግ | ዶ |
| ለ | ሙ | ኒ | ሣ | ዔ | ፍ | ጾ | ጰ | ፑ | ኢ | ባ | ጌ | ድ | ሆ |
| መ | ኑ | ሢ | ዓ | ፌ | ጽ | ቆ | ፐ | ኡ | ቢ | ጋ | ዴ | ህ | ዎ |

(፲፪)

## በበ ፡ ሠለስቱ ፡ ወበበ ፡ አሐዱ ።

የሦስትና ፡ ያንድ ፡ ፊደል ፡ ንባብ ፤ እንደርሻ ፡ አካሄድ ።

| | |
|---|---|
| አቡጊ ፡ ዳ ፡ ሄውዞ ። | ነሡዒ ፡ ፋ ፡ ጼቅሮ ። |
| በጉዲ ፡ ሃ ፡ ዌዝሖ ። | ሠዑፊ ፡ ጻ ፡ ቄርሶ ። |
| ገዱሂ ፡ ዋ ፡ ዜሕጦ ። | ዐፉጺ ፡ ቃ ፡ ሬስቶ ። |
| ደሁዊ ፡ ዛ ፡ ሔጥዮ ። | ፈጹቂ ፡ ራ ፡ ሴትኆ ። |
| ሀዉዚ ፡ ሓ ፡ ጤይኮ ። | ጸቁሪ ፡ ሳ ፡ ቴኅፆ ። |
| ወዙሒ ፡ ጣ ፡ ዬክሎ ። | ቀሩሲ ፡ ታ ፡ ኄፅጾ ። |
| ዘሑጢ ፡ ያ ፡ ኬልሞ ። | ረሱቲ ፡ ኃ ፡ ፄጽፖ ። |
| ሐጡዪ ፡ ካ ፡ ሌምኖ ። | ሰቱኂ ፡ ፃ ፡ ጴፕኦ ። |
| ጠዩኪ ፡ ላ ፡ ሜንሦ ። | ተኍፂ ፡ ጳ ፡ ፔእቦ ። |
| የኩሊ ፡ ማ ፡ ኔሥዖ ። | ኀፁጺ ፡ ፓ ፡ ኤብጎ ። |
| ከሉሚ ፡ ና ፡ ሤዕፎ ። | ፀጹፒ ፡ አ ፡ ቤግዶ ። |
| ለሙኒ ፡ ሣ ፡ ዔፍጾ ። | ጸፑኢ ፡ ባ ፡ ጌድሆ ። |
| መኑሢ ፡ ዓ ፡ ፌጽቆ ። | ፐኡቢ ፡ ጋ ፡ ዴሀዎ ። |

ግእዝ ፤ ካዕብ ፤ ሣልስ ። ራብዕ ፤ ኃምስ ፤ ሳድስ ። ሳብዕ ፤ ሳምን ፤ ታስዕ ። ዓሥር ፤ ዓሥራዊ ፡ ዓሥራይ ፤ ዐሥረኛ ።

## (፲፫)

ስመ ፡ ፊደል ፡ ወትርጓሜሁ — የፊደል ፡ ስም ፡ ከነትርጓሜው ።

በሥጋዊ ፡ ትርጓሜና ፡ አፈታት ፡ ኹሉም ፡ የፍጥረት ፡ ስሞች ፡ ናቸው ፤ በመንፈሳዊ ፡ አፈታት ፡ ግን ፡ የፈጣሪ ፡ ስሞች ፡ ወይም ፡ የስሙ ፡ ቅጥሎች ፡ ይኾናሉ ።

አ ፡ አልፍ ፤ ቀንድ ፡ የቀንድ ፡ ከብት ፤ (አብ) ።
በ ፡ ቤት ፤ በቁሙ ፡ ቤት ፤ (ባዕል) ።
ገ ፡ ገምል ፤ ግመል ፡ ገመል ፤ (ግሩም) ።
ደ ፡ ድ(ን)ልት ፤ መዝጊያ ፡ (ዘላለም) ፡ (ድልው) ።
ሀ ፡ ሆይ(ሀውይ) ፤ ኗሪ ፡ ኺኝ ፤ (ሀልው) ።
ወ ፡ ዋዌ(ዋው) ፤ ወገል ፡ ዘለበት ፤ (ዋሕድ) ።
ዘ ፡ ዛይ(ዛይን) ፤ ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ (ዝኩር) ።
ሐ ፡ ሐው(ይ)ት ፤ ሕያው ፤ ሕይወት ።
ኀ ፡ ኀርም ፤ ልዩ ፡ ብቸኛ ፤ (ኄር) ።
ጠ ፡ ጠይት ፤ ሠናይት ፤ ሥን ፤ (ጠቢብ) ።
የ ፡ የማን ፤ ቀኝ ፡ እጅ ።
ከ ፡ ካፍ ፤ ውስጥ ፡ እጅና ፡ እግር ፤ (ከሃሊ) ።
ለ ፡ ላዊ ፡ ላውይ ፤ ጠማማ ፤ ጥምጥም ፤ (ልዑል) ።
መ ፡ ማይ ፡ ሜም ፤ ውሃ ፤ ፈሳሽ ፤ (ምዑዝ) ።
ነ ፡ ነሐስ ፡ ናስ ፤ ሽቦ ፡ እባብ ፤ (ንጉሥ) ።
ሠ ፡ ሠውት ፤ ሠዊት ፤ ሰብል ፤ (ሠዓሊ) ።
ዐ ፡ ዐይን ፤ በቁሙ ፤ ምንጭ ፤ (ዐቢይ) ።
ፈ ፡ ፈፍ ፡ (ፌ) ፤ አፍ ፤ አፉፍ ፤ ፈፉ ፤ (ፍቁር) ።
ጸ ፡ ጸደይ ፤ የዘር ፡ ወራት ፤ (ጻድቅ) ።
ፀ ፡ ፀጸ(ፀጺ) ፤ ፀሐያዊ ፤ እሳታዊ) ።
ቀ ፡ ቆፍ ፤ ዝንጀሮ ፤ (ቅዱስ) ።
ረ ፡ ርእስ ፤ ራስ ፤ ርስ ፡ ቅል ።
ሰ ፡ ሳት ፡ (ሰዓት) ፤ ክረምት ፡ (በቁሙ) ፤ (ስቡሕ) ።
ተ ፡ ታው(ታዊ) ፤ ትእምርተ ፡ መስቀል ፤ (ትጉህ) ።
ጰ ፡ ጰይት ፡ (ጴት) ፤ በይት ፡ (ቤት) ፡ በ ።
ፐ ፡ ፒ ፡ (ፔ) ፤ ፈ ፡ (ፌ) ፈ ።

ያ፳፬ና ፡ ያ፳፭ ፡ የ፳፮ ፡ የ፳፯ ፡ ፊደል ፡ ንባብ ።

አበገደ ፡ ሀወዘሐ ፤ ኀጠየከ ። ለመነሠ ፡ ዐፈጸፀ ፤ ቀረሰተ ። ጰፐጰፐ ።

ጰራልያ ፤ ፐፒረለይ ። ጰራቅሊጦስ ፤ ፓንዋማንጦስ ፡ (ፐኔፍማቶስ) ።

## (፲፬)

ኍልቈ ፡ ፊደላት ፡ ወጸዋትዊሆን ፡ ምስለ ፡ ክፍላቲሆን ፡ እስከ ፡ ታው ፡ እምአልፍ ፡ ዘይትገሰስ ፡ ወዘይትለከፍ ፡ በኈምስቱ ፡ ሕዋሳተ ፡ አፍ ፤ እስመ ፡ ፀ ፡ እምኔሆን ፡ ቀጣን ፡ ወገዛፍ ።

### የፊደላት ፡ ኹሉ ፡ ቍጥራቸውና ፡ ስልታቸው ፡ ከነክፍላቸው ።

መላው ፡ የግእዝ ፡ ፊደላት ፡ በየራሳቸው ፡ ነጥሎ ፡ ተርትሮ ፡ በትኖ ፡ ዘርዝሮ ፡ ሲቈጥሯቸው ፡ (ከወ=፳፮) ፡ ኻያ ፡ ስድስት ፡ ዘር ፡ ይኾናሉ ፤ ኀን ፡ ከሐ ፡ ፀን ፡ ከጸ ፤ ጸን ፡ ከበ ፡ ፐን ፡ ከፈ ፡ ደርቦ ፡ በአሌፋት ፡ መንገድ ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ፍቅድ ፡ ሲቈጥሯቸው ፡ ግን ፡ መደበኞቹና ፡ ዋንኞቹ ፡ ከአልፍ ፡ እስከ ፡ ታው ፡ (ከበ=፳፪) ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ብቻ ፡ ይኾናሉ ። «በሀ ፡ የሚነገር ፡ ሴማዊ ፡ ቃል ፡ እጅግ ፡ አለልክ ፡ ስለ ፡ በዛ ፡ የሀ ፡ ድምጥና ፡ መልክ ፡ ፫ ፡ ዐይነት ፡ ኹኖ ፡ ፪ቱ ፡ መደብ ፡ ፫ኛው ፡ ድርብ ፡ ይባላል ። ፫ኛ ፡ ኀ ፡ በግእዝ ፡ እንዳለ ፡ በዐረብም ፡ አለ ፤ በዕብራይስጥም ፡ የካፍ ፡ ድርብ ፡ ኹኖ ፡ ይነገራል ፤ ካፍ ፡ ነቍጣ ፡ ሲኾንበት ፡ ከ ፡ ሲቀርበት ፡ ኸ ፡ ይባላል ። ፐ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ ከፈ ፡ ተደርቦ ፡ ይነገራል ። ፪ኛ ፡ ፀም ፡ በዐረብና ፡ በዕብራይስጥ ፡ አለ» ። እሊህም ፡ ኻያ ፡ ኹለቱ ፡ ፊደላት ፡ አራቱ ፡ ድርቦች ፡ (ኀፀጰፐ) ፡ ሳይቀሩ ፡ ከግእዛቸው ፡ እስከ ፡ ሳብዓቸው ፡ እንደ ፡ ክራር ፡ እንደ ፡ ብገና ፡ አውታር ፡ ተሰድረው ፡ እየብቻቸው ፡ ተይዘው ፡ ሲነዘሩና ፡ ሲቃኙ ፡ ድምጥ ፡ የሚሰጡ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፤ የድምጣቸውን ፡ ስልት ፡ ልዩ ፡ ልዩነቱን ፡ ለማስታወቅ ፡ እንዳምስት ፡ ጣት ፡ ባምስት ፡ ጾታ ፡ ተከፍለው ፡ ባምስቱ ፡ ሕዋሳተ ፡ አፍ ፡ በጕረሮና ፡ በትናጋ ፡ በምላስና ፡ በከንፈር ፡ በጥርስ ፡ ይነገራሉ ።

### ጾታቸውና ፡ ክፍላቸውም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ተጣፈው ፡ ነው ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፩ ፤ በጕረሮ ፡ | የሚነገሩ ፡ | ፭ ፤ | — | አ ፡ ዐ ፡ ሀ ፡ ሐ ፡ ኀ ። |
| ፪ ፤ በትናጋ ፡ | የሚነገሩ ፡ | ፬ ፤ | — | ገ ፡ የ ፡ ከ ፡ ቀ ። |
| ፫ ፤ በምላስ ፡ | የሚነገሩ ፡ | ፮ ፤ | — | ደ ፡ ጠ ፡ ለ ፡ ነ ፡ ተ ። |
| ፬ ፤ በከንፈር ፡ | የሚነገሩ ፡ | ፯ ፤ | — | በ ፡ ወ ፡ መ ፡ ፈ ፡ ጰ ፡ ፐ ። |
| ፭ ፤ በጥርስ ፡ | የሚነገሩ ፡ | ፯ ፤ | — | ዘ ፡ ሠ ፡ ሰ ፡ ጸ ፡ ፀ ፡ ረ ። |

## (፲፭)

### መቅድመ ፡ አኃዝ = የአኃዝ ፡ መቅድምና ፡ መግቢያ ።

ፊደላችንና ፡ የፊደል ፡ ቍጥራችን ፡ በሀለሐ ፡ አካሄድ ፡ ተፋልሶ ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ መሳሳቱን ፡ ከጥቂት ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ ኹሉ ፡ ሳያውቀው ፡ ይኖር ፡ ነበር ። የፊደሉም ፡ ቍጥር ፡ በዚ

ያው ፡ በስሕተቱ ፡ ከሀ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ ፳፪ ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ ባቡጊዳ ፡ አካሄድ ፡ ፫ ፡ ፊደላት ፡ ጐቈእ ፡ ተጨምረውለት ፡ (፻) ፡ እልፍ ፡ መልቷል ፤ እስከ ፡ እልፍም ፡ በፊደል ፡ መቍጠር ፡ የጥንት ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያኹን ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ አይዶለም ፤ የሲም ፡ ፊደል ፡ ኹሉ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፤ በፊደል ፡ እስከ ፡ እልፍ ፡ ይቈጠራል ። ጐ ፡ ስለ ፡ ቀለበቱ ፡ የ፱፻ ፡ አኀዝ ፡ መኾኑ ፤ ኀርም ፡ ኀ ፡ የሐ ፡ ተወራጅ ፡ ነውና ፡ በተራ ፡ ቍጥር ፡ ዘጠነኛነት ፡ ስላለው ፡ ነው ። ቈም ፡ ስለ ፡ ቀለበቱ ፡ ያ፲፻ ፡ አኀዝ ፡ መባሉ ፤ ቆፍ ፡ ፻ ፡ ነውና ፤ የርሱን ፡ ያባቱን ፡ አሥር ፡ ተከትሎ ፡ ነው ። እ ፡ ደግሞ ፡ እልፍ ፡ መባሉ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተቀዳጀት ፡ ስላንዲቱ ፡ ቅንጣት ፡ ነቍጣ ፡ ነው ፤ የእልፍ ፡ እ ፡ ጠባይ ፡ በዕብራይስጥም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፤ ብቻውን ፡ አሐዱ ፡ ይባል ፡ የነበረው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነቍጣ ፡ ሲኾንበት ፡ አንድ ፡ እልፍ ፡ ይባላል ። ዕብራውያን ፡ ግን ፡ እልፍ ፡ የሚሉት ፡ እንዳረቦች ፡ ዐሥሩን ፡ መቶ ፡ ነው ፤ የግእዝም ፡ እልፍ ፡ ጥንታዊው ፡ እንደዚህ ፡ ነበረ ፤ ይኸውም ፡ በአኃዙ ፡ አካሄድ ፡ ይታወቃል ፤ ፲ ፡ ብሎ ፡ ፻ ፡ በማለቱ ። ዐሥሩን ፡ መቶ ፡ ወይም ፡ እንዱን ፡ ሺሕ ፡ እምእት ፡ ብሎ ፡ ዐሥሩን ፡ ሺሕ ፡ አንድ ፡ እልፍ ፡ ማለት ፤ ከጽርእና ፡ ከቅብጥ ፡ የመጣ ፡ የሐዲስ ፡ ግእዝ ፡ ልማድ ፡ ነው ።

---

## (፲፩)

### ኍልቍ ፡ ወስመ ፡ ኍልቍ ፡ በአኃዝ ፡ ወበፊደል ።

ቍጥርና ፡ የቍጥር ፡ ስም ፡ በአኃዝና ፡ በፊደል ፡ ካንድ ፡ እስከ ፡ ምእልፊት ።

| | | |
|---|---|---|
| አ — ፩ ፡ | አሐድ ፡ አሐዱ ፤ | አንድ ፡ አንዱ ፤ አንደኛው ። |
| በ — ፪ ፡ | ክልኤት ፡ ክልኤቱ ፤ | ኹለት ፡ ኹለቱ ፤ ኹለተኛው ። |
| ገ — ፫ ፡ | ሠለስት ፡ ቱ ፤ | ሦ(ሠወ)ስት ፡ ቱ ፤ ሦስተኛው ። |
| ደ — ፬ ፡ | አርባዕት ፡ ቱ ፤ | አራት ፡ ቱ ፤ አራተኛው ። |
| ሀ — ፭ ፡ | ኀምስት ፡ ቱ ፤ | ዐምስት ፡ ቱ ፤ ዐምስተኛው ። |
| ወ — ፮ ፡ | ስድስት ፡ ቱ ፤ | በቁሙ ፤ ስድስተኛው ። |
| ዘ — ፯ ፡ | ሰብዐት ፡ ቱ ፤ | ሰባት ፡ ቱ ፤ ሰባተኛው ። |
| ሐ — ፰ ፡ | ሰመንት ፡ ቱ ፤ | ስምንት ፡ ቱ ፤ ስምንተኛው ። |
| ጠ — ፱ ፡ | ተስዐት ፡ ቱ ፤ | ዘጠኝ ፡ ኙ ፤ ዘጠነኛው ። |
| የ — ፲ ፡ | ዐሠርት ፡ ቱ ፤ | ዐሥር ፡ ሩ ፤ ዐሥረኛው ። |
| ከ — ፳ ፡ | ዕሥራ ፡ (ሁ) ፤ | ካያ=ኻያ ፤ ኹለት ፡ ዐሥር ። |
| ለ — ፴ ፡ | ሠላሳ ፡ (ሁ) ፤ | በቁሙ ፤ ሦስት ፡ ዐሥር ። |

መ — ፵ ፡ አርብዓ ፤ አርባ ፤ አራት ፡ ዐሥር ።

ነ — ፶ ፡ ኀምሳ ፤ ዐምሳ ፤ ዐምስት ፡ ዐሥር ።

ሠ — ፷ ፡ ስሳ ፤ ስድሳ ፤ በቁሙ ፤ ፮፲ ። ወይም ፡ ሥልሳ ፤ ፷ ።

ዐ — ፸ ፡ ሰብዓ ፤ ሰባ ፤ ሰባት ፡ ዐሥር ።

ፈ — ፹ ፡ ሰማንያ ፤ ሰማኒያ ፤ ስምንት ፡ ዐሥር ።

ጸ — ፺ ፡ ተስዓ ፤ ዘጠና ፤ ዘጠኝ ፡ ዐሥር ።

ቀ — ፻ ፡ ምእት ፡ (ቱ) ፤ መቶ ፤ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ።

ረ — ፪፻ ፡ ክልኤ ፡ ቱ ፡ ምእት ፤ ኹለት ፡ መቶ ፤ ኻያ ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ።

ሰ — ፫፻ ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፤ ሦስት ፡ መቶ ፤ ሠላሳ ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ።

ተ — ፬፻ ፡ አርባዕቱ ፡ ምእት ፤ አራት ፡ መቶ ፤ አርባ ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ።

ኀ — ፭፻ ፡ ኀምስቱ ፡ ምእት ፤ ዐምስት ፡ መቶ ፤ ዐምሳ ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ።

ፀ — ፮፻ ፡ ስድስቱ ፡ ምእት ፤ ስድስት ፡ መቶ ፤ ስሳ ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ።

ጸ — ፯፻ ፡ ሰብዐቱ ፡ ምእት ፤ ሰባት ፡ መቶ ፤ ሰባ ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ።

ፐ — ፰፻ ፡ ሰመንቱ ፡ ምእት ፤ ስምንት ፡ መቶ ፤ ሰማኒያ ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ።

ኆ — ፱፻ ፡ ተስዐቱ ፡ ምእት ፤ ዘጠኝ ፡ መቶ ፤ ዘጠና ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ።

ቈ — ፲፻ ፡ ዐሠርቱ ፡ ምእት ፤ ዐሥር ፡ መቶ ፤ ፻ ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ፤ ፩ ፡ ሺሕ ።

እ — ፼ ፡ እልፍ ፤ ምእት ፡ በበ ፡ ፻ ፤ በቁሙ ፡ ፻ ፡ ጊዜ ፡ ፻ ፤ ዐሥር ፡ ሺሕ ።

---

የእ — ፲፼ ፡ አእላፍ ፤ ዐሥር ፡ እልፍ ፡ ወይም ፡ መቶ ፡ ሺሕ ።

ቀእ — ፻፼ ፡ አእላፋት ፤ ፻፼ ፤ ወይም ፡ ሺሕ ፡ ጊዜ ፡ ሺሕ ፡ (፩ ፡ ሚልዮን) ።

ቈእ — ፲፻፼ ፡ ትእልፊት ፤ ሺሕ ፡ ፼ ፤ ወይም ፡ እልፍ ፡ ጊዜ ፡ ሺሕ ፤ (፲ ፡ ሚ) ።

እእ — ፼፼ ፡ ትእልፊታት ፤ ፼ ፡ ጊዜ ፡ ፼ ፤ ወይም ፡ ፻፼ ፡ ጊዜ ፡ ሺሕ ፤ (፻ ፡ ሚ) ።

ቈእእ — ፲፻፼፼ ፡ ምእልፊት ፤ ሺሕ ፡ እልፍ ፡ ጊዜ ፡ እልፍ ፤ (ሺሕ ፡ ሚ) ።

እእእ — ፼፼፼ ፡ ምእልፊታት ፤ { እልፍ ፡ እልፍ ፡ ጊዜ ፡ እልፍ ፤ እልፉን ፡ እልፍ ፡<br>አንድ ፡ እያሉ ፡ እስከ ፡ እልፍ ፡ (፼ ፡ ሚሊዮን) ።

(፲፯)

## ሥርዐተ ፡ ነጥብ=የነጥብ ፡ አገባብ ።

ቃልን ፡ ከቃል ፡ በየጎርመቱና ፡ በየስልቱ ፡ ለያይተው ፡ ከፋፍለው ፡ የሚያሳዩ ፡ የጥፈትና ፡ የቃል ፡ ምልክቶች ፡ ፭ ፡ ናቸው ፤ ኹለቱ ፡ ስላንድ ፡ ይቈጠራሉ ። መልካቸውና ፡ ስማቸውም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ተጣፈው ፡ ነው ።

| መልካቸው ። | | ስማቸው ። |
|---|---|---|
| ፡ | — | ነቍጥ ፡ ወይም ፡ ነጥብ ። |
| ፥ ፥ | — | ንኡስ ፡ ሠረዝ ፡ ወይም ፡ ነጠላ ። |
| ፤ | — | ዐቢይ ፡ ሠረዝ ፡ ወይም ፡ ድርብ ። |
| ። | — | ነጥብ ፡ ወይም ፡ ነቍጥ ። |

### አ ገ ባ ባ ቸ ው ።

ነቍጥ ፡ የቃል (፡) መለያ ፡ ነው ፤ በያንዳንዱ ፡ ቃል ፡ በጎርመት ፡ ኹሉ ፡ ይገባል ። የጥንቱ ፡ ነቍጥ ፡ እንደ ፡ ዜማ ፡ ይዘት ፡ አንድ ፡ ቅንጣት ፡ ብቻ ፡ (.) ነበረ ፡ ይባላል ፤ ፪ኛም ፡ ባንዱ ፡ ነቍጥ ፡ ፈንታ ፡ እንዳ፲ቱ ፡ ያለ ፡ (፡) ዘንግ ፡ ነበረ ፤ ፫ኛ ፡ ግን ፡ በዘንት ፡ ፈንታ ፡ ፪ ፡ ነቍጥ ፡ ኹኗል ። ነቍጥ ፡ የዐረቢ ፡ ነጥብ ፡ የግእዝ ፡ ቃል ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ አንዳንዱ ፡ ጠብታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኹለቱና ፡ አራቱ ፡ አይዶለም ። ሲበዛ ፡ ነቍጣት ፡ ነጥባት ፡ ወይም ፡ ነጠብጣብ ፡ ያሰኛልና ፤ ኹለቱን ፡ አራቱን ፡ ነቍጥ ፡ ነጥብ ፡ ማለት ፡ በዚያው ፡ ባንዱ ፡ ነቍጣ ፡ በጥንታዊው ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በበዋስው ፡ ሕግ ፡ አይዶለም ። ባማርኛ ፡ ፪ ፡ ነጥብ ፡ ፬ ፡ ነጥብ ፡ ተብሎ ፡ ከቅጽል ፡ ጋራ ፡ ይነገራል ፤ ጣፎችና ፡ ባለመጣፎች ፡ ግን ፡ ነቍጥን ፡ ለኹለቱ ፡ ብቻ ፤ ነጥብን ፡ ላራቱ ፡ ብቻ ፡ ሰጥተው ፡ አለቅጽል ፡ ፪ቱን ፡ ነቍጥ ፡ ፬ቱን ፡ ነጥብ ፡ ብለው ፡ በተለየ ፡ ስም ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ አድርገው ፡ ይጠሩታል ። ባለቅኔዎችም ፤ ቃልከ ፡ ነቍጥ ፡ እንዘ ፡ ክልኤቲ ፡ ልሳንከ ፡ አሐቲ ፡ ይእቲ ። ፍቅደ ፡ ነጥብ ፡ በዓላተ ፡ ወልድ ፡ ተስዐቱ ፡ ውእቱ ፡ እያሉ ፡ በውስጠ ፡ ብዙነት ፡ ያገቡታል ። ነጥብን ፡ ተስዐቱ ፡ ማለት ፡ ፭ ፡ ቀይ ፡ ሲጨመርበት ፡ ነው ። ነጠላ ፡ ሠረዝ ፡ (፥) ጠባዩ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ መልኩ ፡ ፪ ፡ ነው ፤ ልዩ ፡ ልዩነት ፡ ባለው ፡ ባማዋርና ፡ በማይማፈር ፡ ቃል ፡ ይገባል ። አነ ፡ ዘጳውሎስ ፤ ወአነ ፡ ዘአጵሎስ ፤ ወአነ ፡ ዘኬፋ ፤ ወአነ ፡ ዘክርስቶ

ስ ፡ ነቢያት ፡ ቀደሙ ፡ አእምሮ ፡ ወሐዋርያት ፡ ተለዉ ፡ አሥሮ ። ሚካኤል ፡ አርመመ ፡ ወገብር ኤል ፡ ተደመ ። አው ፡ በነልዮ ፡ አው ፡ በነቢብ ፤ አው ፡ በገቢር ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ድር ብ ፡ ሠረዝ (፤) በፍጹም ፡ ቃል ፡ ማኽል ፡ እየራሱ ፡ በሚታሰርና ፡ በሚነገር ፤ ባስረጅና ፡ ባፍራ ሽ ፡ ይገባል ። ወምድርሰ ፡ ኢታስተርኢ ፤ ወኢኮነት ፡ ድሉተ ፤ ወጽልመት ፡ መልዕልተ፡ ቀላይ ፤ ወመንፈሰ ፡ እግዚ ፡ ይጺልል ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ። ወይቤ ፡ እግዚ ፤ ለይኩን ፡ ብርሃን ፤ ወኮነ ፡ ብርሃን ። ንበር ፡ ማእከሌነ ፡ ወንግረነ ፤ እስመ ፡ ኪያከ ፡ እልሀቀ ፡ እግዚ ። ፈርሀ ፡ ወደንገፀ ፤ ባ ሕቱ ፡ ኢጐየ ፡ ወኢገገጸ ። ነጥብ ፡ (።) ንኡስ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው ፤ አንባቢን ፡ እንደ ፡ ልጓም ፡ ኹኖ ፡ ይገታል ፤ እንዲሁ ፡ ፍጹም ፡ ቃል ፡ ዐጭርም ፡ ረዥምም ፡ ቢኾን ፡ ተሳቢው ፡ ተከቶ ፡ ነገ ሩ ፡ ሲጨረስ ፡ እንደ ፡ ጕልላት ፡ በጫፍ ፡ በመጨረሻ ፡ ይገባል ። ረዥም ፡ ቃል ፡ ወምድርሰ ፡ እንዳልነው ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ዐጭር ፡ ቃል ፡ በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ እግዚ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ። የመሰለ ው ፡ ኹሉ ። ያማርኛውም ፡ እንደ ፡ ግእዙ ፡ ነው ፤ ለብቻው ፡ የተለየ ፡ ዐዋጅ ፡ የለውም ። በትግ ሬኛም ፡ ወንጌል ፡ ሠረዞች ፡ እንደሚገባቸው ፡ ተጥፈዋል ፡ አልተሳሳቱም ።

በነዚህ ፡ ባ፳ቱ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ሀይነት ፡ ምልክት ፡ ከኤውሮፓ ፡ መጣፍ ፡ ማም ጣትና ፡ መጨመር ፡ ያሻናል ። ስለሚያሹንም ፡ ምልክቶች ፡ ባ፲፱፻፶፱ ፡ ዓመት ፡ የታተመ ፡ የከ ረን ፡ ሰዋስው ፡ በመጨረሻው ፡ ገጽ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። «ወስከ ፡ ጥበብ ። ኤሮፓውያን ፡ በመ ጣፎቻቸው ፡ የሚያደርጓቸው ፡ ምልክቶች ፡ የተጣፈውን ፡ የመጣፉን ፡ ምስጢር ፡ አለችግር ፡ በ ገር ፡ ያሳውቃሉና ፤ በሌላ ፡ መጣብብ ፡ ትተን ፡ እነሱኑ ፡ በጥፈታችን ፡ ውስጥ ፡ እንዳሉ ፡ ማግ ባት ፡ እጅግ ፡ የሚያሻና ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ።

ምልክቶቹም ፡ እኒህ ፡ ናቸው ።

ትእምርተ ፡ ደጊመ ፡ ቃል ፡ »
ትእምርተ ፡ ቃለ ፡ ሐተታ ፡ ?
» » አንክሮ ፡ ! በዘየንብብ ፡ ከልኤሆሙ ፡ ?!
» » ሥላቅ ፡ ¡

አንባቢ ፡ በገር ፡ ያውቀዋል ፡ ተብሎ ፡ ሊጻፍ ፡ በማያሻ ፡ ነገር ፡ የሚደረግ ፡ ምልክት ፡ ይህ ፡ . . . ነው ።

ከተነገሩቱ ፡ ፍጹማን ፡ ቃላት ፡ ባሳሳብ ፡ የማይተባበር ፡ ፍጹም ፡ ቃልን ፡ ከቃል ፡ የሚለይ ፡ ምልክት ፡ ይህ ፡ ( ) ነው ።

ያንዱን ፡ ደራሽ ፡ ጥቅስ ፡ ወይም ፡ ስፖጽ ፡ ቃልን ፡ ለመለየት ፡ ከመገዥመርያው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ የሚደረግ ፡ የስፖጽ ፡ ምልክት ፡ ይህ ፡ « » ነው» ።

ትእምርተ ፡ ቃለ ፡ ሐተታ ፡ ካለው ፡ በቀር ፡ ኹሉም ፡ በግድ ፡ የሚፈለጉ ፡ ናቸው ፤ የጥያቄ ው ፡ ቃል ፡ ምልክት ፡ ግን ፡ ሳይቸገሩ ፡ እንደ ፡ መበደር ፡ ነው ፤ ለግእዙም ፡ ላማርኛውም ፡ የታ

ወቀና ፡ የተለየ ፡ የጥያቄ ፡ አገባብ ፡ (ሁ—ኑ ። ን-ወይ) አላቸውና ፡ ጥፈታቸውና ፡ ንባባቸው ፡ ሌላ ፡ ምልክት ፡ ሳይሻ ፡ ያው ፡ ይበቃው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ባማርኛ ፡ ያልሠለጠኑ ፡ ያማርኛውን ፡ አገባብ ፡ በጥፈትና ፡ ባነጋገር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይተዉታልና ፤ አንባቢና ፡ ጣፊ ፡ ለይቶ ፡ እንዲያውቀው ፡ ላማርኛው ፡ ብቻ ፡ ቢገባ ፡ አይከፋም ። የአንክሮና ፡ የሥላቅ ፡ ምልክት ፡ ከአና ፡ ከሆይ ፡ ከኹለቱ ፡ ጋራ ፡ ሊጣፍ ፡ ይገባዋል ። ነጠብጣብ ፡ ስለ ፡ ቀሪው ፡ ፈደል ፡ ነውና ፤ ቍጥሩ ፡ በዚያው ፡ በቀሪው ፡ ልክ ፡ ይገባል ። ጎግ ፡ ማ . . ። ዳዊት ፡ መዝሙረ ፡ . . . ። አምላክ ፡ ወልደ ፡ . . . . ፡ እንደ ፡ ማለት ። ይኸም ፡ ኹለቱ ፡ ዐይነት ፡ ቀርናዊ ፡ ( ) « » ምልክት ፡ ነጠብጣብም ፡ . . . ሳይቀር ፡ እየተረሳ ፡ ቀርቶ ፡ እንጂ ፡ በዱሮ ፡ መጻሕፍት ፡ ይገኛል ፤ ሌላም ፡ ብዙ ፡ ምልክት ፡ ቀርቶብናል ፤ ይልቁንም ፡ በወንጌል ፡ አጣጣፍ ። ዳግመኛም ፡ የተጣፈውን ፡ ቃል ፡ መልሶ ፡ በመጣፍ ፡ ፈንታ ፡ የሚደረግ ፡ ይህ ፡ — ነው ። ሥጋ ፡ ሰብእ ፤ — ፡ አምላክ ፤ — ፡ ላሕም ። ፪ ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ ዥላሊት ፡ በኹነ ፡ በ፪ ፡ ቃል ፡ ማኸል ፡ እየገባ ፡ ትክክልነትን ፡ ያሳያል ። ለምጽ=ለምጥ ፤ ቡኽ=ሊጥ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። የሚጠብቀውም ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ዜማ ፡ ይዘት ፡ አንዳንዲት ፡ ነቍጣ ፡ ይፈልጋል ፤ ነደ ፡ ነድ ፤ ቈረ ፡ ቍር ፤ ተነ ፡ ተን ።

በዘመናችን ፡ ግን ፡ ስንኳን ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሊጨመር ፡ ያው ፡ ከጥንት ፡ የቈየው ፡ ፈደልና ፡ ንባብ ፡ የጥፈቱ ፡ ሥርዐት ፡ የፊደሉ ፡ አገባብ ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፡ አልተጠበቀም ፤ አልተጠነቀቀም ። ጥፈቱም ፡ አለመምርና ፡ አለትምርት ፡ በመላ ፡ በግምት ፡ በልማድ ፡ በድፍረት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ሥርዐቱ ፡ ኹሉ ፡ ፊደሉም ፡ ሳይቀር ፡ መጐደልና ፡ ማነስ ፤ መናድና ፡ መፍረስ ፤ መጥፋት ፡ መበላሸት ፡ ዠምሯል ።    በወዲያኛው ፡ ባስመራ ፡ ማኅተም ፡ በስዌድን ፡ ማኅበር ፡ ከትግሬና ፡ ከትግሪኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ሦስቱ ፡ ፊደላት ፡ (ሠ ፡ ኀ ፡ ፀ) ፡ እንደ ፡ ወጡ ፤ በወዲህም ፡ ካማርኛው ፡ መጽሐፍ ፡ በነዚህ ፡ በሦስቱ ፡ ላይ ፡ ኹለት ፡ ፊደላት ፡ (ዐ ፡ ሐ) ፡ ተጨምረው ፡ ፭ቱ ፡ እንዲወጡ ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ ሐሳብና ፡ ምኞት ፡ ተነሥቶ ፡ እንደ ፡ ደጀ ፡ ጠኒ ፡ ይጐላላል ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እየፈላና ፡ እየገነፈለ ፡ በግልጥ ፡ ይነገራል ፤ ሥራውንም ፡ እንኳ ፡ የዠመሩት ፡ ሰዎች ፡ ይኖራሉ ፤ ወሰው ፡ ያለላቸው ፡ የለም ፡ እንጂ ።

የማሕዙም ፡ መጽሐፍ ፡ ከንትርጓሜው ፤ ግእዝ ፡ የሌለውም ፡ ያማርኛው ፡ መጽሐፍ ፡ አለንቀ፝ፍና ፡ አለሠረዝ ፡ ስድ ፡ እየታተመ ፡ መልኩ ፡ ጠፍቶ ፡ ደፍራችኹና ፡ ተዥራችኹ ፡ አትዩኝ ፡ አታንቡኝ ፡ ይላል ። አንዳንድ ፡ ሰሦተ ፡ ግን ፡ ዐዲስ ፡ ሥልጣኔ ፡ ይሉታል ። (በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ንኡስ ፡ ሠረዞች ፡ ስለ ፡ ታጡ ፡ በርሳቸው ፡ ፈንታ ፡ ድርብ ፡ ሠረዝ ፡ ገብቷል) ።

# (፲፰)

## ግጥም ፡ ተማሪና ፡ መምር ፡ ስለ ፡ ፊደላት ፡ ስምና ፡ ግብር ።

### ተ ማ ሪ ።

ልጆች ፡ የምሥራች ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፡
እንደ ፡ መልአክ ፡ ኹኜ ፡ በማበሥራችሁ ፤
የማበሥራችኹም ፡ ኹለት ፡ ፍሬ ፡ ቃል ፡
መዐዛው ፡ የአራት ፡ ጣዕሙ ፡ የወንጌል ።

ባማርኛ ፡ ደብተር ፡ በግእዝ ፡ መዝገብ ፡
ተጥፎ ፡ እንዳይታይ ፡ እንዳይነበብ ፡
ተደብቆ ፡ ሲኖር ፡ የፊደላት ፡ ወሬ ፡
ከስማቸው ፡ ጋራ ፡ ተገለጠ ፡ ዛሬ ፤
ቁፍሮ ፡ ባወጣው ፡ የትምርት ፡ ወዳጅ ፡
በመዝገበ ፡ ፊደል ፡ ኹሉም ፡ ተገኘ ፡ እንጅ ።

ዐማራና ፡ ትግሬ ፡ የግእዝ ፡ ልጆች ፡
እግዜር ፡ ያነጣችኹ ፡ የቀለም ፡ ቀንዶች ፡
ከመዝገበ ፡ ፊደል ፡ ጥበብ ፡ እንድትዘግቡ ፡
ወዳቡጊዳ ፡ ቤት ፡ ግቡ ፡ ተሰብሰቡ ።
ባቡጊዳችንም ፡ እንዳያሻሟጥጥ ፡
ሀለሐመን ፡ ተዉት ፡ ወዲያ ፡ ይቀመጥ ።
በቍጥር ፡ በተራ ፡ በኹለት ፡ ባህል ፡
ልዩ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከዓለም ፡ ፊደል ፡
የግእዝ ፡ ሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ አድርገው ፡
ምንም ፡ ባያወግዙት ፡ እንደ ፡ ውጉዝ ፡ ነው ።

ስንሻው ፡ የነበር ፡ ስንመኘው ፡ ቀድሞ ፡
በግእዝ ፡ ቋንቋችን ፡ ተጥፎ ፡ ታትሞ ፡
ወሬያቸው ፡ ስማቸው ፡ ከተገለጠማ ፡
ኑ ፡ እናወድሳቸው ፡ በቅኔ ፡ በዜማ ።
ቅኔውም ፡ ዜማውም ፡ የዱሮ ፡ ግእዝ ፡
ከበሮውም ፡ እኛ ፡ መዝሙሩም ፡ ሐዋዝ ።

እንደ ፡ ኤርምያስም ፡ ሳንንሰቀሰቅ ፡
እንዳዊ ፡ ዳዊትም ፡ እንብብ ፡ ሳናፈልቅ ፡
አንዱንም ፡ አንዱንም ፡ በስሙ ፡ ጠርተን ፡
የአሌፋት ፡ መዝሙር ፡ እንዘምራለን ።

አልፍ ፡ ቤት ፡ ገምል ፡ ድልት ፡ ሆይ ፡ ዋዌ ፡
ዛይ ፡ ሐውት ፡
አዕማደ ፡ ምስጢር ፡ የምትባሉት ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ ቁመን ፡ ስናዋቅር ፡ ጣራ ፡
እንዳንወድቅባችኹ ፡ ደግፉን ፡ ዐደራ ።

ኀርምና ፡ ጠይት ፡ የማን ፡ ካፍ ፡ ላውይ ፡
ማይ ፡ ሚም ፡
ነሐስ ፡ ሠውት ፡ ዐይን ፡ ፈፍ ፡ ጸደይ ፡ ፀጰ ፡ ፀም ፡
እርድእት ፡ ለማድረግ ፡ ሕዝብ ፡ አሕዛቡን ፡
እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ አላችኹ ፡ ሥልጣን ።

ቆፍና ፡ ርእስ ፡ ሳት ፡ ታው ፡ መጨረሻው ፡
ጸና ፡ ፐም ፡ ኹለቱ ፡ ከታው ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡
ከአልፍ ፡ እስከ ፡ ጰፐ ፡ ኻያ ፡ ስድስታችኹ ፡
በልባችን ፡ ሸንጎ ፡ ጉባኤ ፡ አድርጋችኹ ፡
እንድትወስኑልን ፡ ግእዝ ፡ ካማርኛ ፡
አማጥኑናችኋል ፡ በትምርት ፡ ዳኛ ።
የትምርቱም ፡ ዳኛ ፡ አቅንቶ ፡ ፈራጅ ፡
ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ነው ፡ የሰሎሞን ፡ ልጅ ።

ልጆቻችኹንም ፡ ስንቈጥራቸው ፡
እንደ ፡ አዳም ፡ ልጆች ፡ ሠላሳ ፡ ናቸው ፤
ሰባቱ ፡ ዐማርኛ ፡ አራቱ ፡ ግእዝ ፡
ዐሥራ ፡ ዘጠኙ ፡ ግን ፡ ያማርኛ ፡ ጓዝ ።

መዝሙሩ ፡ ይቈየን ፡ እንስማ ፡ ስብከት ፡
የሚሰበከውን ፡ ስለ ፡ ፊደላት ፤
የፊደልን ፡ ትውልድ ፡ ታሪክና ፡ ዜና ፡
ሊሰብክ ፡ ሊያስተምር ፡ መምህር ፡ ቈሟልና ።

---

## መ ምር ።

አጽምዑ ፡ ሕፃናት ፡ ሕዝብየ ፡ ሕገ ፡ ስብከትየ ፤ ወጽልዉ ፡ እዝንክሙ ፡ ኀበ ፡ ቃለ ፡ አፉየ ፤ እስመ ፡ ናሁ ፡ እከሥት ፡ ለክሙ ፡ በምላሌ ፡ አፉየ ፤ ወእነግር ፡ ኵሎ ፡ አምሳለ ፡ ዘእምትካት ፡ በእንተ ፡ አሌፋት ፡ ወፊደላት ።

የተላከ ፡ ከግስ ፡ ከመዝገበ ፡ ቃል ፡
ትርጓሜና ፡ አፈታት ፡ ሐተታ ፡ ፊደል ፤
ይድረስ ፡ ከወዳጄ ፡ ከሕፃናት ፡ ልብ ፡
ከግእዝ ፡ ሰራዊት ፡ ካማርኛ ፡ ሕዝብ ፤
ከናቴም ፡ ከጦቢያው ፡ ካፍሪቃ ፡ ባላል፡ጋ ፡
እጆቿን ፡ ወደግዜር ፡ ከምትዘረጋ ።

ሰላምታ ፡ አቀርብለኹ ፡ ለፊደል ፡ ጸሐፍት ፡
ላታሞችም ፡ ሳይቀር ፡ እጅ ፡ በመንሣት ።

እጅ ፡ መንሻዬም ፡ የማር ፡ ወለላ ፡ ፊደል ፡
መስፈሪያው ፡ ዕብራይስጥ ፡ ጕንዶ ፡ የሚባል ።

ያቡጊዳን ፡ ሥራ ፡ የምታማርሩ ፡
እንዲጣፍጣችኹ ፡ ቅመሱ ፡ ተማሩ ።

ስለ ፡ ተጠማችኹ ፡ የፊደልን ፡ ዜና ፡
ከሥሩ ፡ ከምንጩ ፡ ላመጣው ፡ ነውና ፤
ምናልባት ፡ ስትቀምሱት ፡ ስታጣጥሙት ፡
ጠላ ፡ ነው ፡ ብላችኹ ፡ ስም ፡ እንዳትሰጡት ።

ጥሩውን ፡ ቃል ፡ ውሃ ፡ ጠላ ፡ ነው ፡ ብትሉ ።
ይታዘብችኋል ፡ የሚቀምሰው ፡ ኹሉ ።

የስብከት ፡ መዐዛ ፡ የሰባኪው ፡ ጣዕም ፡
ለይቶ ፡ ማስታወቅ ፡ ከፉና ፡ መልካም ።

በልበ ፡ ሕፃናት ፡ በአፈ ፡ ደቂቅ ፡
ፊደል ፡ ሥር ፡ እንዲሰድ ፡ ታሪኩ ፡ እንዲጸድቅ ፤
ልጆች ፡ እየጠቀሰኩ ፡ ከምድር ፡ ከሰማይ ፡
እስኪ ፡ ልናገረው ፡ የልጅን ፡ ጠባይ ።

ያባትንም ፡ ሥራ ፡ በልጆቹ ፡ ላይ ፡
እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ገልጬ ፡ ላሳይ ።

ሰውና ፡ መላእክት ፡ ያንድ ፡ አባት ፡ ልጆች ፡
ታናሽና ፡ ታላቅ ፡ ወንድማማቾች ፤
ታላቁ ፡ ሸፍቶ ፡ ካባቱ ፡ ቢዋጋ ፡
ብኵርናው ፡ ተሰጠ ፡ ለታናሹ ፡ ሥጋ ።

ታናሹም ፡ ቢሸፍት ፡ አልሄደም ፡ ብኵርና ፤
ቃል ፡ ወረሰው ፡ እንጂ ፡ በሕገ ፡ ሰብእና ።

ለሰው ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ የቃል ፡ በኵርነቱ ፤
ለመላእክትም ፡ ነው ፡ በሰማይ ፡ ላሉቱ ።

በዲያብሎስ ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ አዳም ፡
ወልድ ፡ ነው ፡ በኵራቸው ፡ ለመላእክትም ።

ዲያብሎስ ፡ ቢገፋው ፡ ወድቆ ፡ ከመሬት ፡
ተበላሽቶ ፡ ነበር ፡ ይኽ ፡ በኵርነት ።
ከሥጋው ፡ ቃል ፡ በቀር ፡ ለርሱ ፡ የሚመች ፡
አልተገኘምና ፡ ከላይም ፡ ከታች ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ እስኪባል ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡
ሰሙ ፡ እንጂ ፡ መልአክ ፡ ነው ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፤
ትንቢትና ፡ ራእይ ፡ ለአበው ፡ ሲሰብክ ፡
አርአያው ፡ የመልአክ ፡ ቃሉ ፡ የአምላክ ፤
ከሔኖክ ፡ ዝምሮ ፡ ነቢያት ፡ ይጠሩ ፤
የርሱን ፡ መልአክነት ፡ እንዲመሰክሩ ።

በሃይማኖት ፡ ገመድ ፡ በልጅነት ፡ ሐብል ፡
እንደ ፡ ከነዓን ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡
መንግሥት ፡ ሰማይን ፡ ዐብረው ፡ ለሚወርሱ ፡
ለሰው ፡ ለመላእክት ፡ በኵር ፡ የለም ፡ አለርሱ ።

በእሳት ፡ ጉባኤ ፡ በመሬት ፡ ማኅበር ፡
ለካህናተ ፡ ሰማይ ፡ ለካህናተ ፡ ምድር ፡
የፊደል ፡ የጥፈት ፡ የቋንቋ ፡ መምር ፡
ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ።

ፊት ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ኋላም ፡ በሐዲስ ፡
አፍ ፡ እየስከፈተ ፡ መጣፍ ፡ የሚያጕርሥ ፤

እውነተኛው ፡ መምር ፡ የትምርቱ ፡ አባት ፡
አንድ ፡ እግዚር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በላይ ፡ በታች ፡ ቤት ።

እግዚር ፡ መምር ፡ ኹና ፡ ያዳምን ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡
በመንፈሱ ፡ ሲቃኝ ፡ ሲያስተምር ፡ በቃሉ ፡
ያቆመለትን ፡ ሕግ ፡ በተፈጥሮ ፡ ዕውቀት ፡
ፈታዊ ፡ ልቡናው ፡ ቢዘነጋበት ፡
ፊደልን ፡ ጥፈትን ፡ ባርኮ ፡ የሰጠው ፡
በሦስተኛው ፡ ትውልድ ፡ በሄኖስ ፡ ጊት ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ ታሪክ ፡ እንዳንለው ፡ አሉ ፡
እንሆ ፡ ምስክር ፡ መጽሐፈ ፡ ኩፋሌ ፤
ሔኖክም ፡ ይነግራል ፡ ገልጦ ፡ እያሳመረ ፡
ፊደል ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ነበረ ።

ኋላም ፡ ባለቤቱ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ወርዶ ፡
ሃይማኖት ፡ ለማሞቅ ፡ እሳቱን ፡ አንድዶ ፤
ጽላትና ፡ ታቦት ፡ ቀርጦ ፡ እያስቀረጠ ፡
ዐሠርቱ ፡ ቃላትን ፡ በጇ ፡ ጥፎ ፡ ሰጠ ።

ለባለጁ ፡ ሙሴም ፡ ሲሰጠው ፡ እጅ ፡ በጅ ፡
ስማ ፡ ስማ ፡ ብሎ ፡ እስነገረ ፡ ዐዋጅ ።
በቃሉ ፡ ነጐድጓድ ፡ በመንፈሱ ፡ ድምጥ ፡
ዓለም ፡ ኹሉ ፡ እስኪርድ ፡ እስኪንቀጠቀጥ ።

የሙሴ ፡ እጀችና ፡ የጀቹ ፡ ጣቶች ፡
የጽላት ፡ የቃላት ፡ አምሳል ፡ መርገፎች ።

ሙሴ ፡ ፵ ፡ ቀን ፡ ምሉ ፡ አሪትን ፡ ሲማር ፡
ፈጣሪው ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ይነግረው ፡ ነበር ።

በጣም ፡ ስለ ፡ ገባው ፡ ጥፈቱ ፡ ትምርቱ ፡
የብርሃን ፡ ቀለም ፡ ቀንድ ፡ ተሣለ ፡ በፊቱ ፡
ተገልበብ ፡ እያሉ ፡ ውሉደ ፡ ጽልመት ፡
በክርስቶስ ፡ አምሳል ፡ እስኪሸፍኑት ።

የተማረውንም ፡ ጽላቱን ፡ ቢገድፍ ፡
ወዲያው ፡ ቶሎ ፡ ሰጠው ፡ ዘኢያገድፍ ፤
ዘኢያገድፉም ፡ የወርቅ ፡ ታቦት ፡
ኹለቱ ፡ ኪሩቤል ፡ የተሣሉበት ።

ጽላትና ፡ ታቦት ፡ አርኣያና ፡ አምሳል ፡
ብተለየ ፡ አካሉ ፡ ሰው ፡ ለኾነው ፡ ቃል ።

ሰው ፡ ከመኾን ፡ በፊት ፡ ሰውን ፡ ሊባርክ ፡
ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ እንዲወርድ ፡ አምላክ ፡
አስቀድሞ ፡ ሰብኳል ፡ ነቢዩ ፡ ሔኖክ ፡
ለንማቱሳላ ፡ ለኖኅ ፡ ለላሜክ ።

ስንኳን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በዝንጋዔው ፡ ቦታ ፡
በሰማይም ፡ አለ ፡ የጥፈት ፡ ገበታ ፤
ፊደልና ፡ ጥፈት ፡ በሰማይ ፡ እንዳሉ ፡
ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ ይመሰክራሉ ።

አንድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ያለሙ ፡ መምር ፡
የሰማዩ ፡ ሥርዐት ፡ ተሠርቷል ፡ በምድር ።

ከአጽምዑ ፡ አንሥቶ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡
የስብከቱ ፡ መግቢያ ፡ መቅድምና ፡ ራስ ።

---

በሴምና ፡ በካም ፡ በያፌት ፡ ነገድ ፡
ከሦስት ፡ ተከፍሎ ፡ የፊደል ፡ ትውልድ ፡
በዛፍ ፡ ይመሰላል ፡ ዐጽቁ ፡ ስለ ፡ በዛ ፡
ከርሱ ፡ ፍሬ ፡ በልተን ፡ አእምሮ ፡ እንድንገዛ ።

ከማዕደንም ፡ ጋራ ፡ ሲያመዛዝኑት ፡
ላቂያና ፡ ብልጫ ፡ አለው ፡ ከስድስቱ ፡ ዐይነት ።

ወርቅ ፡ ነው ፡ ወርቅ ፡ ነው ፡ የግእዝ ፡ ፊደል ፡
ሰባት ፡ እጅ ፡ የጠራ ፡ ከሰባት ፡ ዛሕል ፤
ልኩና ፡ ሚዛኑ ፡ በፍጥረት ፡ ቍጥር ፡
ከአሌፍ ፡ እስከ ፡ ታው ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ልጥር ፤
፩ዱ ፡ ልጥር ፡ ፊደል ፡ ፩ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡
እንደ ፡ ሙሴ ፡ ተቅዋም ፡ ባለሰባት ፡ ዐጽቅ ።

በዕለታት ፡ አምሳል ፡ ከሰባት ፡ ተከፍሎ ፡
ሰባት ፡ ቤት ፡ ይባላል ፡ ፊደላትን ፡ ወሎ ።

የትውልዱም ፡ ሐረግ ፡ የሚሳብበት ፡
ሰባቱ ፡ ሰማያት ፡ ሰባቱ ፡ ሀብታት ።

ሰባት ፡ ቤት ፡ መባሉም ፡ ስሙ ፡ ፩ ፡ ሲኾን ፡
ፈጽሞ ፡ ያስረዳል ፡ ፍጹምነቱን ፤
ፍጹም ፡ እንደ ፡ ኾነም ፡ ይህ ፡ ሰባት ፡ ቍጥር ፡
አምላክ ፡ ነቢያት ፡ ርሱ ፡ ይመሰክር ።

የፊደል ፡ ዘይቤ ፡ ባጭር ፡ ቃል ፡ ሲፈታ ፡
የቋንቋ ፡ ድብኝት ፡ የቃል ፡ ኹሉ ፡ ጐታ ፤
የመጻሕፍት ፡ ምንጭ ፡ የምስጢራት ፡ ነቅ ፡
ቢቀዳ ፡ ቢቀዳ ፡ ውሃው ፡ የማያልቅ ።

ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ምስጢረ ፡ ሥጋዌ ፡
ኅቡኡ ፡ ረቂቁ ፡ የአምላክ ፡ ህላዌ ፤
በፊደል ፡ መንጽር ፡ ይታየናል ፡ ገዝፎ ፡
አልፋና ፡ ዖሜጋን ፡ ለብሶ ፡ ተጐናጽፎ ።
አልፋ ፡ የአካላት ፡ ዖ ፡ የመለኮት ፤
ትርጓሜው ፡ ቀድምና ፡ ጥንት ፡ ወተፍጻሜት ።

የሀም ፡ ሦስትነት ፡ እንደ ፡ ሦስት ፡ ቅዳሴ ፡
ወይም ፡ እንደ ፡ አዳም ፡ አርአያ ፡ ሥላሴ ፤
ያዳም ፡ አርአያነት ፡ እሙን ፡ የታመነ ፡
ለባዊ ፡ ነባቢ ፡ ሕያው ፡ ስለ ፡ ኾነ ።

በአልፋ ፡ ዠምሮ ፡ በዖ ፡ መጨረስ ፡
የጽርአውያን ፡ ሕግ ፡ የሰብአ ፡ ጢሮስ ።

እኛም ፡ በሴም ፡ ቋንቋ ፡ እንደ ፡ ባህላችን ፡
ጽርሑን ፡ ከግእዙ ፡ እያስማማን ፡
ሥሩንና ፡ ጫፉን ፡ ገጥመን ፡ ስንፈታው ፡
አልፋ ፡ ወዖ ፡ ማለት ፡ አሌፍ ፡ ወታው ፡ ነው ።

---

አንድ ፡ አ ፡ እንዳይበቃው ፡ ለትግሬ ፡ ላማራ ፡
አልፋ ፡ ወዖ ፡ ብሎ ፡ ኹለቱንም ፡ ጠራ ።

ሠወስቱ ፡ ሀ(ሐኀ)ደግሞ ፡ ሠወስት ፡ ምስክር ፡
ለብሉይ ፡ ለሐዲስ ፡ ለቋንቋ ፡ ምስጢር ።
ባንዱ ፡ የሚጣፈው ፡ በሌላው ፡ ሲጣፍ ፡
ቋንቋው ፡ ተበላሽቶ ፡ ይኾናል ፡ ጲያፍ ።

የጸሐፊ ፡ ደዌ ፡ ያታሚ ፡ መከራ ፡
ጠንቅቆ ፡ አለማወቅ ፡ የፊደልን ፡ ሥራ ።
እንዳገኙ ፡ መጣፍ ፡ በድፍረት ፡ በመላ ፡
የቋንቋ ፡ ደረመን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቢስ ፡ ገላ ።
ንባብ ፡ የሚያሳክክ ፡ ምስጢር ፡ የሚቈምጥ ፡
መልክአ ፡ ትርጓሜ ፡ የሚለዋውጥ ።

አለነጥብም ፡ መጣፍ ፡ የንባብ ፡ ቂጥኝ ፡
ጣፊዉን ፡ መጣፉን ፡ ቢያክ ፡ ቢያክ ፡ የሚያሰኝ ።

ሠና ፡ ሰ ፡ ጸና ፡ ፀም ፡ አራቱ ፡ ቀለም ፡
አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ሔዋንና ፡ አዳም ፤
ማንም ፡ ሰው ፡ ተነሥቶ ፡ እንዳይለያቸው ፡
እግዜር ፡ በጥበቡ ፡ ያጣመራቸው ።

ከበገና ፡ አውታሮች ፡ ካሥሩ ፡ ዥማት ፡
ኹለቱ ፡ ሊቃውንት ፡ ኹለቱ ፡ አማሪት ፤
ምንም ፡ አንድ ፡ ቢኾን ፡ የድምጣቸው ፡ ስልት ፡
በውስጥ ፡ አለውና ፡ ልዩ ፡ ልዩነት ፤
ኹሉም ፡ ካልተገኙ ፡ በኹለትነት ፡
አንዳንዱ ፡ እንዳይበቁ ፡ ለበገናነት ፡
ፊደልም ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ በቋንቋ ፡ ሥርዐት ፡
ከሄኖስ ፡ ዠምሮ ፡ ከሰብአ ፡ ትካት ።

ካሠርቱ ፡ ቃላትም ፡ አንዱ ፡ ቃል ፡ ቢጐድል ፡
ትምርቱና ፡ ሕጉ ፡ ሕጹጽ ፡ ይባላል ።

እነምን ፡ አለበት ፡ እንኹሉ ፡ ቀኙ ፡
በትግሪኛ ፡ መንፈስ ፡ ፊደልን ፡ ሲቃኙ ፡
ከግእዝ ፡ ለይተን ፡ ፀማርኛን ፡ ኹሉ ፡
ባ፩ ፡ አ ፡ ባ፩ ፡ ሀ ፡ (ሰ ፡ ጸ) እንጣፍ ፡ የሚሉ ፡
አላወቁም ፡ ይኸን ፡ ቋንቋ ፡ እንዲበላሽ ፡
ንባቡም ፡ ምስጢሩም ፡ እንዲኾን ፡ ፈራሽ ።

እንደነሰምሶን ፡ ዐይኑ ፡ ካወጣማ ፡
ጥፈቱም ፡ ቋንቋውም ፡ ይኾናል ፡ ጨለማ ።

ፀወቀች ፡ ፀወቀች ፡ ፀወቀች ፡ ቢሏት ፡
መጣፏን ፡ ፀጠበች ፡ የሚሉት ፡ ተረት ፡
ላየው ፡ ላስተዋለው ፡ ላይናማ ፡ ደብተራ ፡
ሠምና ፡ ወርቅ ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ ምኞት ፡ ጋራ ።

የፊደልን ፡ ገላ ፡ ደፍሮ ፡ ለመቍረጥ ፡
ሐኪም ፡ መኾን ፡ ያሻል ፡ በአፍአ ፡ በውስጥ ፤
አፍአው ፡ ፀማርኛ ፡ ውስጡም ፡ ግእዝ ፡ ነው ፡
ትምርቱ ፡ እንደ ፡ ገደል ፡ ያልተደፈረው ።

ለቋንቋ ፡ በሽታ ፡ ለጥፈት ፡ ሕማም ፡
ከትምርት ፡ በቀር ፡ መድኀኒት ፡ የለም ።

እንደ ፡ ምን ፡ ይቻላል ፡ በቀንጃ ፡ ፊደል ፡
የቋንቋውን ፡ ምክሼ ፡ ማወቅ ፡ መነጠል ።
ጥንቱን ፡ ፊደላችን ፡ ሲማዊው ፡ በገና ፡
ኹለት ፡ ኹለት ፡ ኹኖ ፡ ለምን ፡ ተሠራና ።

ዐማርኛችንስ ፡ በጥፈት ፡ ጕዳና ፡
ካባቱ ፡ ከግእዝ ፡ መቼ ፡ ይለይና ።

የትምርቱስ ፡ ችጋር ፡ የውቀቱ ፡ ቀጠና ፡
ፊደል ፡ በማሳነስ ፡ መቼ ፡ ይለቅና ።

በሴማውያን ፡ ዘንድ ፡ በያፌት ፡ ልጆች ፡
ይህ ፡ ነገር ፡ ቢሰማ ፡ ያሰኛል ፡ ሞኞች ።

---

ብርሃንና ፡ ሰላም ፡ የወሬ ፡ ማሲንቆ ፡
የፊደልን ፡ እውታር ፡ ብዛቱን ፡ ጠይቆ ፡
የተገባ ፡ ምላሽ ፡ የሚሰጠው ፡ ቢያጣ ፡
ፊደል ፡ እናሳንስ ፡ ማለት ፡ ስላመጣ ፡

የተማሪ ፡ ቤቱን ፡ ከማስፋት ፡ በቀር ፡
ሌላ ፡ ምክር ፡ አያሻም ፡ የፊደል ፡ ነገር ።

በዚያው፡ሥራ፡መሥራት፡ቀኙ ፡ እያለልን ፡
ለምን ፡ እንሄዳለን ፡ ግራ ፡ ግራውን ።

ምክርስ ፡ የሚያስፈልግ፡ በሙሉው፡ፊደል፡
የትምርቱን፡ መጽሐፍ፡ ማውጣት፡ በየክፍል፤
ለተማሪ ፡ ቤቱም ፡ ደረጃ ፡ መሥራት ፡
በፊደሉ ፡ ቍጥር ፡ ካንድ ፡ እስከ ፡ ሰባት ፤
የትምርቱንም ፡ ሕግ ፡ ማደስ ፡ መለወጥ ፡
ከፊደል ፡ ዠምሮ ፡ ትምርቱ ፡ እንዲሰለጥ ፤
የቋንቋውን ፡ ቅንጣት ፡ ቃልና ፡ ንባብ ፡
በፊደሉ ፡ ተራ ፡ መልቀም ፡ መሰብሰብ ፤
የፊደሉም ፡ ተራ ፡ ሥሩ ፡ መነሻው ፡
መቼ ፡ እንደ፡ ቅኔያችን፡ ማፉ ፡ መድረሻው ።

ዐዲስ ፡ መንገድ ፡ ይውጣ ፡ ባዲሱ ፡ ንጉሥ፡
ሰው ፡ ከደረሰበት ፡ ቶሎ ፡ እንድንደርስ ።

ዙሪያ ፡ ጥምጥም፡ ኹኖ፡የዱሮው፡መንገድ፡
ዕውቀት ፡ ዐጥሮብናል ፡ በርሱ ፡ እንዳንሄድ ።

ከፊደል ፡ ላይ ፡ ዘሎ ፡ በሐዲስ ፡ ላይ ፡ ፊጥ ፡
ጥርስ ፡ ሳያወጡ ፡ ዳቦ ፡ እንደ ፡ መግመጥ ።

ቃል ፡ ትምርቱም ፡ ይኹን፡ስዋስው፡ርባታ፡
በመልካ ፡ መልኩና ፡ በውዳሴው ፡ ፈንታ ።

ቋንቋውን፡ ሳያውቁ፡ መጮኽ ፡ መለፍለፍ፡
ገደል ፡ ያስመስላል ፡ ወይም ፡ ፎኖግራፍ ።

ልጅነት ፡ የያዘው ፡ ምላሳችን ፡ መንካ ፡
ከቋንቋችን ፡ በፊት ፡ ሌላ ፡ ቋንቋ ፡ አይንካ ።
ግእዝ ፡ ካማርኛ ፡ አስተባብሮ ፡ ሲያውቅ ፡
ከውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይንጠቅ ፤
ትምርቱንም ፡ ይንዳው ፡ እንደ ፡ ምርኮ ፡ ከብት ፡
ባማርኛው ፡ መንገድ ፡ በግእዙ ፡ ስልት ፤
የጥበቡን ፡ መጽሐፍ ፡ ሥራ ፡ መሥሪያውን ፡
እንብቦ ፡ ተርጕሞ ፡ ቶሎ ፡ እንዲያሰማን ።

---

የትምርቱ ፡ አካሄድ ፡ እንዲህ ፡ ቢሻሻል ፡
የሦስቱ፡ዓመት፡ሥራ፡ በሦስት፡ ወር፡ ያልቃል።

በጌታችን ፡ አምሳል ፡ በሐዋርያት ፡
በተከታዮቹም ፡ በሰብዓ ፡ አርድእት ፡
ሦስት፡ዓመት፡ከሦስት፡ ወር፡ ተግቶ፡ የሚሠራ፡
ሳያገኝ ፡ አይቀርም ፡ የሚበቃ ፡ አዝመራ ።

ዕንቍላሉ ፡ ምኞት ፡ እሳቱ ፡ ፈሊጥ ፡
ከተዳፈነበት ፡ ከልባችን ፡ ውስጥ ፡
በኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ይፍረጥ ፡ ይገለጥ ፤
የረጋውም ፡ ወተት ፡ ይገፋ ፡ ይናጥ ፡
የትምርቱን ፡ ቅቤ ፡ ሕፃኑ ፡ እንዲውጥ ፤
ጕበዙም ፡ ተቀብቶ ፡ እንዲቅለጠለጥ ።

ከሴማዊው ፡ እሳት ፡ ከግእዝ ፡ ሬዲል ፡
ተማሪው ፡ ተጋፍጦ ፡ እስኪቀጣጠል ፤
እየቈለቈሉት ፡ መምህራን ፡ በቃል ፡
ትምርቱ፡እስኪጋጋም፡ዕውቀቱ ፡እስኪበስል፡
ፍሕሙ ፡ እስኪመርትና ፡ እስኪዛቅ ፡ በገል ፡
ከመጤስ፡ ከመንደድ ፡ ማነው ፡ ዝም ፡ የሚል ።

መልኩንስ፡ በሰው፡መልክ፡ማነው፡የማያይ፤
የሰው ፡ መስታዮቱ ፡ ሰው ፡ አይዶለሞይ ።

የብድሩ ፡ ቋንቋ ፡ የልቀው ፡ ትምርት ፡
አይበቃንምና ፡ ለንግ ፡ ለሣልስት ፤
ያማርኛው ፡ ጕድጓድ ፡ የግእዙ ፡ ዐዘቅት ፡
አፈ ፡ መምር ፡ ኹሉ ፡ ይስፋ ፡ ይከፈት ፤
በየውስጡ ፡ ያለው ፡ ጥሩ ፡ ሐሳብ ፡ ምንጭ ፡
ይፈልፍል ፡ ይገንፍል ፡ ይውጣ፡ ወደ፡ ውጭ ።

ትምርታችን ፡ ይጕረፍ ፡ ቋንቋችን ፡ ይፍሰስ ፤
ጕርፉ ፡ ማዕበሉ ፡ አፍሪቃን ፡ ያልብስ ፤
ኤውሮፓንም ፡ ያርካ ፡ እስያን ፡ ያርስ ፤
ወዳሜሪካንም ፡ ይጋልብ ፡ ይገሥግሥ ፤
እኛንም ፡ ያጥምቀን ፡ እንደ ፡ ዮርዳኖስ ፤
ቀድሞ ፡ የተጣፈው ፡ በጥቍር ፡ ክርታስ ፡
መጽሐፈ ፡ ዕዳችን ፡ እንዲደመሰስ ፡
በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
(አሐዱ ፡ አምላክ ፤ አሜን) ።

## (፲፱)

## ሀየንተ ፡ ፊደለ ፡ ሐዋርያ ።

የፊደላዋሪያ ፡ ለውጥ ፡ ወይም ፡ ምትክ ። (ተረት) ፤ ምትክ ፡ ራሱን ፡ አያክ ።

ዕለታተ ፡ ሰንበት = የሳምንት ፡ ቀኖች ።

እሑድ ። ሰኑይ ። ሠሉስ ። ረቡዕ ። ኀሙስ ። ዐርብ ። ቀዳም ።
» ። ሰኞ ። ማግሰኞ ። ሮብ ። ዐሙስ ። » ። ቅዳሜ ።



ዘከመ ፡ ፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለመ ፡ ወኵሎ ፡ ዘውስቴቱ ፡ በስዱስ ፡ ዕለት ።
እግዜር ፡ ዓለምንና ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ በስድስት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ፈጠረ ።

ግጥም ፡ ስለ ፡ ፈጣሪና ፡ ስለ ፡ ፍጥረት ፡ (ስላሥርቱና ፡ ስለ ፡ ስድስቱም ፡ ቃላት) ፤ ራስ ፡ ጕበና ፡ ቤት ፡ የነበሩ ፡ ኦርቶዶክሳዊው ፡ ሊቅ ፡ አለቃ ፡ ዕንቍ ፡ ባሕርይ ፡ የገጠሙት ።

አራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ሰባቱ ፡ ሰማያት ፡
ሕያዋን ፡ መላእክት ፡ ብርሃንና ፡ ጽልመት ፤
እንዚህ ፡ ሰምንቱ ፡ ተፈጥረዋል ፡ እሑድ ፡
በረቂቁ ፡ ባሕርይ ፡ በሥላሴ ፡ ፈቃድ ።

ውሃን ፡ ከ፫ ፡ ከፍለው ፡ ፩ዱን ፡ እጅ ፡ አጽንተው ፡
በነፋስ ፡ ተራዳ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ዘርግተው ፡
በዕለተ ፡ ሰኑይ ፡ ፈጠሩ ፡ ሥላሴ ፡
በአሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ እንደ ፡ ጣፈው ፡ ሙሴ ።

አዝርዕቱም ፡ አትክልቱም ፡ ከዕፀዋት ፡ ጋራ ፡
ማግሰኞ ፡ ተገኙ ፡ በመለኮት ፡ ሥራ ።

ፀሓይን ፡ ጨረቃን ፡ ከከብን ፡ ጨምሮ ፡
ረቡዕ ፡ ፈጠረ ፡ በቃሉ ፡ ተናግሮ ።

ኀሙስ ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ የፈጠራቸው ፡
እንስሳት ፡ አራዊት ፡ አዕዋፍ ፡ ናቸው ።

የኀሙስን ፡ ፍጥረት ፡ በመልክ ፡ የሚመስሉ ፡
ዐርብም ፡ ከየብስ ፡ ላይ ፡ ፈጠረ ፡ በቃሉ ።

ደግሞ ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ በሦስተኛው ፡ ሰዓት ፡
አዳምን ፡ ፈጠረው ፡ ሊያኖረው ፡ በገነት ።

ቀዳሚት ፡ ዐረፈ ፡ ሥራውን ፡ ቢጨርስ ፡
ድካም ፡ የሌለበት ፡ የዘላለም ፡ ንጉሥ ።

ፈጥሮ ፡ ለሚገዛን ፡ ለሚመግበን ፡
ክብርና ፡ ምስጋና ፡ ኀይልና ፡ ሥልጣን ፤
ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ፡ ወአሜን ።

(፳)

## ክፍላተ ፡ ዘመን ፡ ወጊዜ ፤ አው ፡ መስፈርታት ፡ ወአምጣናት ።

የዘመንና ፡ የጊዜ ፡ ክፍሎች ፤ ወይም ፡ መስፈሪያዎችና ፡ ልኮች ።

**ቀመር ። ዓመት ። ወርኀ ። ሰንበት ። ዕለት ። ሰዓት ። ደቂቃ ። ካልኢት ።**

(ቀመር) ፡ ባመት ፡ የሚቈጠር ። (ዓመት) ፡ ፫፻፷፭ ፡ ቀን ፡ ከሩብ ። (ወርኀ) ፡ ፴ ፡ ቀን ። (ሰንበት) ፡ ፯ ፡ ቀን ። (ዕለት) ፡ ፳፬ ፡ ሰዓት ። (ሰዓት) ፡ ፷ ፡ ደቂቃ ። (ደቂቃ) ፡ ፷ ፡ ካልኢት ። (ካልኢት) ፡ ፮ ፡ ቅጽበት ።

(፳፩)

## ክፍላተ ፡ ዓመት ፡ ወከዋክብቲሆሙ = ያመት ፡ ክፍሎችና ፡ ኮከቦቻቸው ።

**መፀው ። ሐጋይ ። ጸደይ ። ክረምት ።**
**ምልክኤል ። ሕልመልሜሌክ ። ሚላኤል ። ናርኤል ፡ (ሔኖክ) ።**
**ወዕለታቲሆሙ ፡ በበ ፡ ተስዓ ፡ ወእሐዱ ፡ ዕለት ፡ ወራብዕት ።**

ቀኖቻቸውም ፡ (ጸአ ፡ ጸአ) ፡ ፺፩ ፡ ፺፩ ፡ ቀን ፡ ተሩብ ፡ ናቸው ።

መፀው ፡ እምአመ ፡ ዕሥራ ፡ ወሰዱሱ ፡ ለመስከረም ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ዕሥራ ፡ ወሰዱሱ ፡ ለታኅሣሥ ፤ ወእምድኅሬሁ ፡ ሐጋይ ። ዝኒ ፡ በክፍለ ፡ አፍ

ራቅያ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወእኮ ፡ በክፍለ ፡ ኤውሮፓ ፡ ወእስያ ።

መፀው ፡ ከመስከረም ፡ ፳፮ ፡ እስከ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፮ ፡ ነው ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በጋ ። ይህም ፡ ኢት ዮጵያ ፡ ባለችበት ፡ በአፍሪቃ ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በኤውሮፓና ፡ በእስያ ፡ ክፍል ፡ አይደለም ።

---

(፳፯)

ሰመንቱ ፡ ማእዝናት ፡ ዐቢያን ፡ ወንኡሳን ፡ = ፰ቱ ፡ ማዝኖች ።

ዐቢያን = ታላላቆች ።

ምሥራቅ ። ምዕራብ ። ሰሜን ። ደቡብ ።

ንኡሳን = ታናናሾች ።

መስዕ ። አዜብ ። ባሕር ። ሊባ ።

---

(፳፰)

ኀምስቱ ፡ ክፍላተ ፡ ዓለም = ፭ቱ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ።

አፍሪቃ ። እስያ ። ኤውሮፓ ። ዖሲያንያ ። አመሪቃ ፡ ካ ።

---

(፳፱)

ስመ ፡ ኀምስ ፡ ሕዋስ ፡ ወግብራቲሆን = ያ፭ቱ ፡ ሕዋሳት ፡ ስምና ፡ ግብር ።

| (ስም) ፡ | | (ግብር) ፡ | | (ሥራ) ፡ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ዐይን ፡ | — | ርእይ ፡ | — | ማየት ፡ | — | ያይን ። |
| እዝን ፡ | — | ሰሚዕ ፡ | — | መስማት ፡ | — | የጆሮ ። |
| አንፍ ፡ | — | አጼንዎ ፡ | — | ማሽተት ፡ | — | ያፍንጫ ። |
| አፍ ፡ | — | ጥዒም ፡ | — | መቅመስ ፡ | — | ያፍ ። |
| እድ ፡ | — | ገሢስ ፡ | — | መዳሰስ ፡ | — | የጅ ። |

በነዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ እግርና ፡ አባለ ፡ ዘር ፡ ሲጨመሩ ፡ ፯ ፡ ይኾናሉ ።

---

(፷፭)

አስማተ፡ ሰብዐቱ፡ ከዋክብት፡ ዐበይት፡ እለ፡ ይነሥኡ፡ ብርሃነ፡ እምፀሐይ።

ከፀሐይ፡ ብርሃን፡ የሚቀበሉ፡ የ፯ቱ፡ ታላላቅ፡ ከዋክብት፡ ስሞች።

ዐጣርድ። ዝሁራ። መሪኅ። መሽተሪ። ዙሐል። ኡራኑስ። ነይጡን።

እንደ፡ ፈላስፎች፡ ቍጥር፡ ግን፡ በነዚህ፡ ላይ፡ ምድር፡ ስትጨመር፡ ፰፡ ይኾናሉ።

---

(፷፮)

አስማተ፡ ዐሠርቱ፡ ወክልኤቱ፡ አውራኅ፡ ወከዋክብቲሆሙ።

ያ፲፪ቱ፡ ወር፡ ስምና፡ ኮከብ።

| | | (ወር)፡ | (ኮከብ)፡ | (ፍች)፡ |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | — | መስከረም፡ | ሚዛን፡ | በቍሙ። |
| ፪ | — | ጥቅምት፡ | ዐቅራብ፡ | ጊንጥ። |
| ፫ | — | ኅዳር፡ | ቀውስ፡ | ቀስተኛ። |
| ፬ | — | ታኅሣሥ፡ | ጀደይ፡ | የፍየል፡ ጠቦት። |
| ፭ | — | ጥር፡ | ደለው፡ | ማሕየብ፡ (መቅጃ)። |
| ፮ | — | የካቲት፡ | ሑት፡ | ዓሣ። |
| ፯ | — | መጋቢት፡ | ሐመል፡ | አውራ፡ በግ። |
| ፰ | — | ሚያዝያ፡ | ተውር፡ | (ሶር)፡ በሬ)። |
| ፱ | — | ግንቦት፡ | ጀውዛ፡ | ጥንድ። |
| ፲ | — | ሠኔ፡ | ሸርጣን፡ | ጕርምጥ። |
| ፲፩ | — | ሐምሌ፡ | አሰድ፡ | አንበሳ። |
| ፲፪ | — | ነሐሴ፡ (ጳጕሜ)፡ | ሰንቡላ፡ | ሽቷም፡ ባለሽቱ። |

(፳፯)

ሩቅና ፡ ቅርብ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አንድና ፡ ብዙ ፡ ተለይተው ፡ የሚታወቁበት ፡ ፲ ፡ የርባታ ፡ መደብ ፤ ወይም ፡ መራ ፡ ሰራዊት ። የብዙዎቹ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ በማርኛቸው ፡ አንድ ፡ ነው፤ እንደ ፡ ግእዙ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ። (ቀዳማይና ፡ ትንቢት ፡ ዘንድና ፡ ትእዛዝ ፡ እንቀጽ) ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ያንድ ፤ — | አነ ፡ | እኔ ፡ | ጸሐፍኩ ፤ | ጣፍኩ ። (ያለፈ) |
| » | አንተ ፡ | አንተ ፡ | ጸሐፍከ ፤ | ጣፍክ ። |
| » | አንቲ ፡ | አንቺ ፡ | ጸሐፍኪ ፤ | ጣፍሽ ። |
| » | ውእቱ ፡ | (ያ) ፡ ርሱ ፡ | ጸሐፈ ፤ | ጣፈ ። |
| » | ይእቲ ፡ | (ያች) ፡ ርሷ ፡ | ጸሐፈት ፤ | ጣፈች ። |
| የብዙ ፤ — | ንሕነ ፡ | እኛ ፡ | ጸሐፍነ ፤ | ጣፍነ ፡ ን ። |
| » | አንትሙ ፡ | እናንተ ፡ | ጸሐፍክሙ ፤ | ጣፋችኹ ። |
| » | አንትን ፡ | » | ጸሐፍክን ፤ | » |
| » | እሙንቱ ፡ | እነሱ ፡ | ጸሐፉ ፤ | ጣፉ ። |
| » | እማንቱ ፡ | » | ጸሐፋ ፤ | » |

የጥሬ ፡ ዝርዝር ፤ ወይም ፡ ርባታ ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| | (መጽሐፍ) ፡ | (መጣፍ) ፡ | |
| ያንድ ፤ — | መጽሐፍየ ፡ ............... | መጣፌ ። | |
| » | መጽሐፍከ ፡ ............... | መጣፍኽ ። | |
| « | መጽሐፍኪ ፡ ............... | መጣፍሽ ። | |
| » | መጽሐፉ ፡ ............... | መጣፉ ። | |
| » | መጽሐፋ ፡ ............... | መጣፏ ። | |
| የብዙ ፤ — | መጽሐፍነ ፡ ............... | መጣፋችን ። | |
| » | መጽሐፍክሙ ፡ ............ | መጣፋችኹ ። | |
| » | መጽሐፍክን ፡ ............ | » | |
| » | መጽሐፎሙ ፡ ............ | መጣፋቸው ። | |
| » | መጽሐፎን ፡ ............... | » | |

ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ እንቀጽና ፡ ጥሬ ።
እንዲህ ፡ እያልኽ ፡ አርባ ።

እጽሕፍ ፡ እጥፋለኹ ። እጽሐፍ ፡ እጥፍ ፡ ዘንድ ፤ እንድጥፍ ፤ ልጥፍ ። እጽሐፍ ፡ ልጣፍ ። ጽሒፍ ፤ ፎት ፤ መጣፍ ። ጸሓፊ ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት) ፤ የሚጥፍ ፤ ጣፊ ።

(፳፫)

ርእሰ ፡ ዐሠርቱ ፡ ቃላት ＝ ያሠርቱ ፡ ቃላት ፡ ራስ ።

አፍቅሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ በኵሉ ፡ ልብከ ፡ ወበኵሉ ፡ ነፍስከ ፡ ወበኵሉ ፡ ኀይልከ ＝ ፈጣሪኽ ፡ እግዜርን ፡ በፍጹም ፡ ልብኽና ፡ በፍጹም ፡ ሰውነቱኽ ፡ በፍጹም ፡ ኀይልኽ ፡ ውደደው ፡ (ዘዳ፮ ፡ ፭ ። ፲ ፡ ፲፪) ።



ዘከመ ፡ ወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ ጽላተ ፡ ሕግ ፡ ወትእዛዝ ፡ ጽሑፋተ ፡ እንተ ፡ ክልኤ ፡ ፍና ፡ በደብረ ፡ ሲና ።

እግዜር ፡ ለሙሴ ፡ የሕግና ፡ የትእዛዝ ፡ ጽላት ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ (ዘፀ፴፩ ፡ ፲፰ ። ፴፪ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮) ።

«ሕግ ፡ አታድርግ ፡ አታድርግ ፤ ትእዛዝ ፡ አድርግ ፡ አድርግ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ።»

ዐሠርቱ ፡ ቃላተ ፡ኦሪት ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፫ ፡ ፯ ፡ ፰ ፡ ፲፪—፲፯ ። ዘሌ፲፱ ፡ ፲፰) ።

(፩) አነ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፤ ኢታምልክ ፡ ባዕደ ፡ አምላክ ፡ ዘእንበሌየ ＝ ፈጣሪኽ ፡ እግዜር ፡ እኔ ፡ ነኝና ፤ ከኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አታምልክ ። (፪) ኢትምሐል ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪከ ፡ በሐሰት ＝ ባለት ፡ የፈጣሪኽን ፡ የግዜርን ፡ ስም ፡ ጠርተኽ ፡ አትማል ። (፫) ተዘከር ፡ ዕለተ ፡ ሰንበት ።

**ወበዓላት**=የሰንበትንና ፡ የበዓሎችን ፡ ቀን ፡ ዐስበኸ ፡ አክብር ፡ (ዘሌ ፳፫ ፡ ፫—፰) ። (፩) **አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ**=አባትና ፡ እናትኸን ፡ አክብር ። (፩) **ኢትቅትል**=ነፍስ ፡ አትግደል ። (፮) **ኢትዘሙ**=አትሴስን ፤ አታመንዝር ። (፯) **ኢትስርቅ**=አትስረቅ ፤ አትቀማ ። (፰) **ኢትኩን ፡ ስምዐ ፡ በሐሰት**=ባሰት ፡ አትመስክር ። (፱) **ኢትፍቱ ፡ ቤተ ፡ ካልእከ ፤ ወኢትፍቱ ፡ ብእሲተ ፡ ካልእከ ፤ ወኢገብሮ ፡ ወአመቶ ፤ ወላሕሞ ፡ ወአድጎ ፤ ወኵሎ ፡ ዘካልእከ**=የባልንጀራኸን ፡ ቤት ፡ ሚስቱን ፡ ሎሌውን ፡ ገረዱን ፡ ላሙን ፡ አህያውን ፡ የርሱን ፡ ገንዘብ ፡ ኹሉ ፡ አትመኝ ፤ አትውደድ ። (፲) **አፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ከመ ፡ ነፍስከ**=ባልንጀራኸን ፡ እንደ ፡ ነፍስኸ ፡ ውደድ ።

ከኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አታምልክ ፤ ባሰት ፡ አትማል ፤ ሰንበት ፡ በዓላትን ፡ አክብር ፡ ያላቸው ፡ እኒህ ፡ ሦስቱ ፡ እግዜርን ፡ በፍጹም ፡ ልቡና ፡ በመውደድ ፡ ይፈጸማሉ ። የቀሩት ፡ ስድስቱ ፡ ባልንጀራን ፡ በፍጹም ፡ ልቡና ፡ በመውደድ ፡ ይፈጸማሉ ፡ (ማቴ ፳፪ ፡ ፴፯—፵) ።

---

## (፳፱)

ያለቃ ፡ ዕንቈ ፡ ባሕርይ ፡ ግጥም ፡ ስላ፲ቱና ፡ ስለ ፡ ፮ቱ ፡ ቃላት ፤ ስለ ፡ መርገፎቹም ።

ከዐሠርቱ ፡ ቃላት ፡ መዠመሪያው ፡ አንዱ ፡ በፍጹም ፡ ልቡና ፡ እግዜርን ፡ ውደዱ ።

ከመጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ወጥቶ ፡ በሰንበት ፡ የሠራ ፡ ዕረፍት ፡ አያገኝም ፡ ከሰማይ ፡ መከራ ።

አባትና ፡ እናቱን ፡ በምግብ ፡ የማይረዳ ፡ ተበድሮ ፡ በልቶ ፡ አልከፈለም ፡ ዕዳ ።

አልታገሥ ፡ ብሎ ፡ የሰው ፡ ነፍስ ፡ ገዳይ ፡ በምድር ፡ ርስት ፡ ያጣል ፡ ስንኳን ፡ በሰማይ ።

ገዘሙት ፡ የወደደ ፡ ሞቱን ፡ ማሰብ ፡ ትቶ ፡ እንስሳ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ ከቶ ።

የሰው ፡ ገንዘብ ፡ ሲሰርቅ ፡ ልቡ ፡ የማይሠጋ ፡ ሲገረፍ ፡ ይኖራል ፡ በእሳት ፡ ዐለንጋ ።

ባሐሰት ፡ መስክሮ ፡ በሐሰት ፡ የማለ ፡ ክብርሃን ፡ ጨለማ ፡ ይሻለኛል ፡ አለ ።

ከሰው ፡ ሚስት ፡ የሚሄድ ፡ ጠላት ፡ ነው ፡ ለራሱ ፡ ወዲህም ፡ በሥጋው ፡ ወዲህም ፡ በነፍሱ ።

የሰውን ፡ ክብት ፡ አይቶ ፡ መውደድ ፡ መመኘት ፡ ከሞነኔ ፡ በቀር ፡ አያስጥም ፡ ሀብት ።

መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አትገኝም ፡ ነፍሱ ፡ ሰውን ፡ ካልወደዱ ፡ እንደ ፡ ራስ ፡ አድርጎ ።

---

### ስለ ፡ ፮ቱ ፡ ቃላት ።

«ማቴ ፭ ፡ ፳፪ ፡ ፳፰ ፡ ፴፪ ፡ ፴፬ ፡ ፴፱ ፡ ፵፬» ።

ስድስቱ ፡ ቃላትን ፡ ጽፎልናል ፡ ክፍሎ ፡ ወንድም ፡ ከማሳዘን ፡ ተጠበቁ ፡ ብሎ ።

ለኔ ፡ ትኹን ፡ ብሎ ፡ ሴትን ፡ መመልከት ፡ እጅግ ፡ ፍጹም ፡ በደል ፡ ታላቅ ፡ ኀጢአት ።

ሳትመንዝርበት ፡ ሚስቱን ፡ የሚፈታ ፡ ይፈረድበታል ፡ በላይኛው ፡ ቦታ ።

በውነት ፡ እንኳ ፡ ቢኾን ፡ መሐላ ፡ ይቅር ፤ ይሻለናልና ፡ የላይኛው ፡ ክብር ።

ክፉ ፡ ለሠራ ፡ ሰው ፡ በጎ ፡ የመለሰ ፡ ዘላለም ፡ ይኖራል ፡ ጸጋ ፡ እንደ ፡ ለበሰ ።

ጠላትን ፡ ቢወዱ ፡ ይወዳል ፡ ፈጣሪ ፡ ርሱ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የኹሉ ፡ አሳዳሪ ።

---

### የ፮ቱ ፡ ቃላት ፡ መርገፍ ።

ሌሎቹም ፡ መጻሕፍት ፡ ብለውናል ፡ ሲያዙ ፡
የምድሩን ፡ ትታችኹ ፡ የሰማዩን ፡ ያዙ ።

አኹን ፡ ምን ፡ አለና ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ደንቄሮ ፡
ለምድር ፡ የሚለውጥ ፡ የሰማዩን ፡ ኑሮ ።

ኹሉን ፡ ያታልላል ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ተድላ ፡
ጥቂት ፡ ላይሰነብት ፡ ላይገኝ ፡ ለኋላ ።

የሥጋ ፡ መከራ ፡ ይፈጸማል ፡ በድሜ ፤
ለነፍስ ፡ መከራ ፡ የለውም ፡ ፍጻሜ ።

ገሃነም ፡ ከገቡ ፡ አይገኝም ፡ ተስፋ ፤
ለትሉ ፡ እንቅልፍ ፡ የለው ፡ እሳቱም ፡ አይጠፋ ።

የኋላ ፡ መከራ ፡ አይወርድም ፡ ከራስ ፤
ይህን ፡ እያሰበ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ያልቅስ ።

---

ያለቃ ፡ ዕንቊ ፡ ባሕርይ ፡ ግጥም ፡ ይህ ፡ የጣፍነው ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ስላምስቱ ፡ አዕማድ ፡ የገጠሙት ፡ ፲ ፡ ዕንቍ ፡ ግጥም ፡ አላቸው ፤ እኛ ፡ ግን ፡ አዕማዱን ፡ ስላልጣፍናቸው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ትተነዋል ። ግጥማቸውንም ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ያውቀዋል ።



«ምስጢረ ፡ ምጽአት ፡ ወመንግሥተ ፡ ሰማይ» ። አነ ፡ ውእቱ ፡ አልፋ ፡ ወዖ ፤ ቀዳማዊ ፡ ወደኃራዊ ፤ ርእስ ፡ ወማኅለቅት ። ወናሁ ፡ እመጽእ ፡ ፍጡነ ፤ ወዕሴትየኒ ፡ ምስሌየ ፤ ከመ ፡ እፍድዮ ፡ ለኵሉ ፡ በከመ ፡ ምግባሩ ፡ (ራእ፳፪ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ። ፳ ፡ ፩—፯ ። ፩ተሰ ፡ ፬ ፡ ፲፭—፲፰ ። ፭ ፡ ፩ ፡ ፪) ።

## መቅድመ ፡ ፊደል ፡ ሣልስ ።

ዓዲ ፡ ናቁርብ ፡ ወንሜልስ ፡ ለከ ፡ ዘንተ ፡ ፊደለ ፡ እምኃ ፡ ጥበብ ፡ ወጋዳ ፤ አ ፡ እንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፤ ወዕጓለ ፡ ዳዊት ፡ አንበሳ ፡ መዋኤ ፡ አራዊት ፡ ወእንስሳ ፤ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሥ ፡ ነዊኀ ፡ መንፈስ ፡ ወመምህረ ፡ ሕግ ፡ ሐዲስ ፤ ዘየሐውር ፡ እምኀይል ፡ ውስተ ፡ ኀይል ፡ እንዘ ፡ ይመርሖ ፡ ልዑል ፤ እስመ ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ በኵረ ፡ ስም ፡ ዐቢይ ፡ ወዘርዐ ፡ መንግሥት ፡ ሠናይ ፤ ዘወድቀ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ሠናይት ፡ እግዝእተ ፡ ዐሠርቱ ፡ ምእት ፡ ወኀጠተ ፡ ሥርናይ ፡ ቡሩክ ፡ ሥጋሁ ፡ ለወልደ ፡ አምላክ ፤ እሳታዊ ፡ መብልዕ ፡ ርሱን ፡ ወመስቴ ፡ መኰንን ።

### የ፫ኛ ፡ ፊደል ፡ መቅድም ።

ባገራችንና ፡ በክፍላችን ፡ በመሬታችን ፡ ውስጥ ፡ የታወቀና ፡ ያልታወቀ ፡ የተገኘና ፡ ያልተገኘ ፤ ገና ፡ ሊፈለግ ፡ የሚገባው ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ገንዘብ ፡ ዐላባና ፡ ድልብ ፡ እንዳለበት ፤ በቋንቋችንም ፡ ውስጥ ፡ ጉባኤው ፡ ሰፍቶ ፡ ተማሪው ፡ ተንጋግቶ ፡ በጥፈትና ፡ በጥያቄ ፡ እየቈፈረ ፡ እየመረመረ ፡ ይፍረጥ ፡ ይገለጥ ፡ የሚለው ፡ ስላጣ ፤ እንደንቍላል ፡ ድፍን ፡ እንደ ፡ ባር ፡ ማሽላ ፡ ሽፍን ፡ ኹኖ ፡ ባለመታወቅ ፡ እንደሳት ፡ ተዳፍኖ ፡ የሚኖር ፡ ብዙ ፡ ትምርት ፡ አለ ። ኹሉን ፡ ቈፍሮ ፡ ለማውጣት ፡ ብዙ ፡ ሠራተኛ ፡ ዐጋዥ ፡ ረዳት ፡ ታላላቅ ፡ መሣሪያ ፡ የተማሪ ፡ ቤት ፡ ስለሌለ ፤ ከምሉ ፡ በከፍሉ ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ያየነውን ፡ የሰማነውን ፡ ኀሊናችን ፡ በውቀት ፡ እጃችን ፡ በጥፈት ፡ የደረሰበትን ፡ መርምረንና ፡ ተመራምረን ፡ ዘግነን ፡ ቈንጥረን ፡ የፊደልን ፡ ጠባይ ፡ የድምጡንና ፡ የቅጥሉን ፡ ነገር ፡ እንጥፋለን ፤ እኵሉንም ፡ ካኹን ፡ አስቀድሞ ፡ ባለፉት ፡ ክፍሎች ፡ በታችኞቹ ፡ ጥፈንዋል ፤ የቀረውም ፡ ዐዲስ ፡ መንገድና ፡ እንግዳ ፡ ልማድ ፡ በታላቁ ፡ ግስ ፡ ተጥፎል ።   የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ የሌላውም ፡ የሴም ፡ ቋንቋ ፡ ዐመሎች ፡ ወይም ፡ ዋየሎች ፡ ፬ ፡ ናቸው ፤ ወና ፡ የ ፡ አ(ዐ) ና ፡ ሀ(ሐኀ) ፤ እነዚህ ፡ አራቱ ፡ ያሉበት ፡ ግስ ፡ ቤቱን ፡ ሳይለቅ ፡ ድምጥና ፡ አካሄድ ፡ ይለውጣል ። ከአ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ ባሉ ፡ በፊደላት ፡ ኹሉ ፡ በካዕብ ፡ በሳብዕ ፡ ወ ፤ በሣልስ ፡ በኃምስ ፡ የ ፤ በራብዕ ፡ በሳድስ ፡ እና ፡ ሀ ፡ አሉ ። ይህ ፡ ከካዕብ ፡ እስከ ፡

ሳብዕ ፡ ያለ ፡ ቅጥል ፡ ኹሉ ፡ ሰባርነትና ፡ ዐንካስነት ፡ ሳይቀር ፡ በነዚህ ፡ ፈንታ ፡ የገባ ፡ ነው ። ለድጓና ፡ ለቅዳሴ ፡ ዜማ ፡ ለምልክቱ ፡ ሥረይ ፡ እንዳለው ፤ ለፊደልም ፡ ድምጥ ፡ ለጠባዩና ፡ ለቅጥዩ ፡ ሥረዮቹ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ቅጥል ፡ ኹሉ ፡ ምልክት ፡ ኹኖ ፡ የነዚህን ፡ ያራቱን ፡ ጠባይ ፡ ያሳያል ፤ ጠባያቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ። የወ ፡ ጠባይ ፡ ራሱን ፡ እየጐረደ ፡ ሳድስና ፡ ግእዝ ፡ ይኾን፡ የነበረውን ፡ በኋላው ፡ ያለውን ፡ ፊደል ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። (ማስረጃ) ፤ ፈነወ ፡ ብሎ ፡ ይፌንው ፡ ይፈንው ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ይፌኑ ፡ ይፈኑ ፤ ተፈነወ ፡ ብሎ ፡ ይትፌነው ፡ ይትፈነው ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ይትፌኖ ፡ ይትፈኖ ። ሐዊር ፡ ቀዊም ፡ ብሎ ፡ ሐወረ ፡ ቀወመ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሖረ ፡ ቆመ ፤ የሐውር ፡ ይቀውም ፡ ብሎ ፡ ሣልሳዩን ፡ ይሐውር ፡ ይቅውም ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ይሑር ፡ ይቁም ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። የወዲያኛው ፡ ትግሬም ፤ ቀርቡ ፡ መጽኡ ፡ ፈርሁ ፡ ደንግፁ ፡ ሲል ፤ ቀርበው ፡ መጽአው ፡ ፈርሀው ፡ ደንገፀው ፡ ይላል ። ዐማርኛም ፤ ግእዙ ፡ ባረኮ ፡ ቀደሶ ፡ አኃዞ ፡ ገሰሶ ፡ የሚለውን ፤ ባረከው ፡ ቀደሰው ፡ ያዘው ፡ ዳሰሰው ፡ እያለ ፡ በው ፡ ይዘረዝራል ። ይኸም ፡ የትግሬና ፡ ያማርኛ ፡ አካሄድ ፡ የጥንታዊው ፡ ያሮጌው ፡ ግእዝ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ፊደል ፡ ኹሉ ፡ ወ ፡ በፊቱ ፡ ከሌለ ፡ አለወ ፡ መሪነት ፡ ብቻውን ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ። የወ ፡ ጠባይ ፡ በዕብራይስጥም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፤ ዋ ፡ ደግሞ ፡ ብቻውን ፡ ለራብዕ ፡ ዲቃሎች ፡ ለ፳፫ቱ ፡ ዐመል ፡ ይኾናል ፤ ይህነን ፡ ኋላ ፡ በቦታው ፡ እናመጣዋለን ። የየ ፡ ጠባይ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፤ ራሱን ፡ እየጐረደ ፡ ሳድስና ፡ ግእዝ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ በካልአይና ፡ በሣልሳይ ፡ አንቀጽ ፡ ሣልስ ፤ በቀዳማይ ፡ ኃምስ ፡ ያደርጋል ። (ማስረጃ) ፤ ሠዪም ፡ ገዪሥ ፡ ብሎ ፡ ሠየመ ፡ ገየሠ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሤመ ፡ ጌሠ ፡ ይሢም ፡ ይጊሥ ። ሠነየ ፡ ብሎ ፡ ይሤንይ ፡ ይሠንይ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ይሤኒ ፡ ይሠኒ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ይሤኒ ፡ ባለውም ፡ የ ፡ አለበት ፤ ይሠየንይ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ፊደል ፡ ኹሉ ፡ የ ፡ በፊቱ ፡ ከሌለ ፡ አለየ ፡ መሪነት ፡ ብቻውን ፡ ሣልስና ፡ ኃምስ ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ። «በንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ግን ፡ ያውም ፡ በቀተለ ፡ ቤት ፡ ሣልስ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ሳድስ ፡ ያደርጋል ። (ማስረጃ) ፤ ሐቅይ ፡ ሰቅይ ፡ ወድይ ፡ ፈድይ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ» ። እና ፡ ሀ ፡ ደግሞ ፡ ጠባያቸው ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ኹለቱ ፡ ስላንድ ፡ ይቈጠራሉ ፤ ጠባያቸውም ፡ በቀዳማይና ፡ በሣልሳይ ፡ አንቀጽ ፡ ግእዝ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ሳድስ ፡ ማድረግ ፤ ሳድስ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ራብዕ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። (ማስረጃ) ፤ መጺእ ፡ ብሎ ፡ መጸአ ፡ ይምጽእ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መጽአ ፡ ይምጻእ ፤ በልዐ ፡ ይብላዕ ፤ ፈርሀ ፡ ይፍራህ ፤ ነጽሐ ፡ ይንጻሕ ፤ በዝኀ ፡ ይብዛኅ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ዐማርኛውንም ፡ መጣ ፡ በላ ፡ ፈራ ፡ ነጣ ፡ በዛ ፤ የሚያስኙት ፡ እና ፡ ሀ (ዐ ፡ ሐ ፡ ኀ) ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ አስተውል ። አ ፡ ከሀ ፡ ተለይቶ ፡ የማስደረግ ፡ ል

ማድ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፣ በትንቢት ፡ በዘንድ ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ ወና ፡ እንደ ፡ የ ፡ ይጐርዳል ። (ማ ስረጃ) ፣ **አቅተለ** ፡ ብሎ ፣ **የአ** ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ **ያቀትል ፡ ያቅትል** ። **አቅተልከ** ፡ ብሎ ፣ **ተአ** ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ **ታቀትል ፡ ታቅትል** ፣ የመሰለው ፡ ኹሉ ። «ባማርኛ ውም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፣ ዐዲሳበባ ፣ ባዲ ፣ ሳዲ ፣ ስላዲ ፣ ወዳዲ ፣ ዐዲሳበባን ። ባባት ፣ ካባት ፣ ላባት ፣ ወዳባት ፡ እያለ ፡ ዐመልነቱን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ጐራጅነቱን ፡ ያሳያል ። ፪ኛም ፡ ሳ ድስ ፡ ኹኖ ፡ አገባብ ፡ሲገኘው ፡ ተበዝብዞ ፡ ሳይጣፍና ፡ ሳይነገር ፡ ተውጦ ፡ ተጐርዶ ፡ ይቀ ራል ። እናት ፣ በናት ፣ ከናት ፣ ለናት ፣ ወደናት ። እግዜር ፣ በግዜር ፣ ከ ፡ ለ ፡ ስለ ፡ ወደግዜር ። እጅ ፣ በጅ ፡ ከ ፡ ለ ፡ ስለ ፡ ወደጅ ፣ የመሰለው ፡ ኹሉ» ። (፩) ፊደል ፡ ኹሉ ፡ እና ፡ ሀ ፡ በፊቱ ፡ ከሌሉ ፡ ብቻውን ፡ ሳድስና ፡ ራብዕ ፡ አይኾንም ። የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ አካሄድ ፡ ዐዋጁና ፡ ሕጉ ፡ እንዲህ ፡ ባራት ፡ ዐመል ፡ የቆመና ፡ የተወሰነ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፣ የወ ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ዉ ፡ ዎ ፣ የየ ፡ ሣልስና ፡ ኃምስ ፡ ዪ ፡ ዬ ፣ የአ ፡ ራብዕ ፡ ኣ ፣ የሀ ፡ ሳድስ ፡ ህ ፣ እነዚህ ፡ ፯ቱ ፡ ለየራሳቸው ፡ በመነሻና ፡ በመድረሻ ፡ በቁም ፡ ቀሪዎች ፡ እየኾኑ ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ ግእዝን ፡ ፊደል ፡ ኹሉ ፡ በጅ ፡ መኪና ፡ እንደርሳቸው ፡ ድምጥ ፡ ማስኬድ ፡ ይችላሉ ። ድም ጣቸውና ፡ ድምጥነታቸውም ፡ ከሮማይስጥ ፡ ዋየል ፡ ከ፯ቱ ፡ ኹሉ ፡ ይስማማል ። ዋየል ፡ የላቲን ፡ ቃል ፡ ነው ፣ የግእዝም ፡ ሊኾን ፡ ይቻላል ። መላው ፡ የአ ፡ ቤት ፡ ፊደል ፡ ፯ቱ ፡ ዐይ ነት ፡ ኹሉ ፡ በሮማይስጥ ፡ ዋየል ፡ ይባላል ። (ኹለቱ ፡ የና ፡ ኄ ፡ ናቸው) ። ፍችውንም ፡ ድ ምፅ ፡ ወሃቤ ፡ ድምፅ ፡ ይሉታል ፣ ድምፅ ፡ ለራሱ ፡ ወሃቢ ፡ ለሌላው ። እኛ ፡ ባገባብ ፡ ትም ርት ፡ ግእዝ ፡ ዐመል ፡ ደጊመ ፡ ቃል ፡ የምንላቸውን ፡ እሊህን ፡ ፫ቱን ፡ ያፈታውያን ፣ ኮንሶን ፡ ዋየል ፡ ዱብል ፡ ይሏቸዋል ። እሊሁም ፡ **ከነሰ ፣ ዋይ ፡ ወይል ፡ ወይለየ ፣ ደበለ** ፡ ከ ማለት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፣ በንባብ ፡ በምስጢር ፡ ይገጥማሉ ፣ እንዲያውም ፡ በዊራሽ ፡ ከነዚህ ፡ የወጡ ፡ ይመስላሉ ።

ዳግመኛም ፣ ያራቱ ፡ ዲቃሎች ፡ የነጐኈኰቈ ፡ ቅጥል ፡ ኹሉም ፡ መንታ ፡ መንታ ፡ ዐይነ ት ፡ መኾኑ ፣ ዋየሎቻቸው ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ነው ። የግእዛቸውም ፡ ቅጥል ፡ ቀለበቱ ፡ እንደ ፡ ሎ ፡ መኾኑ ፡ ፪ ፡ ወ ፡ ያሳያል ፣ ህየንተ ፡ ዉወ ፡ ነው ። ይህም ፡ **ገዉወ—ጐ ፣ ኀዉወ—ኈ ፣ ከዉወ—ኰ ፣ ቀዉወ—ቈ** ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። የሎም ፡ አጣጣፍ ፡ እንደ ፡ አቦዶና ፡ እንደ ፡ ዞሖጦ ፡ እንደ ፡ ኮጸጶሶ ፡ ዐንካሳ ፡ ቈራጣ ፡ ሊኾን ፡ እንጂ ፣ እንደ ፡ ጐኈኰቈ ፡ ቅጥላምና ፡ ቀለ በታም ፡ ሊኾን ፡ ባልተገባውም ፣ ድምጡና ፡ ቅጥሉ ፡ አልተስማማም ፣ ከሳቢዎች ፡ ሕግ ፡ ወ ጥቶ ፡ እንደነጐ ፡ ዲቃል ፡ ባለ፪ ፡ ዋየል ፡ ኹኗል ፣ ስለዚህ ፡ በዝርዝር ፡ ሲጣፍ ፡ **ሉወ ፡ ለዉወ** ፡ ያሰኛል ። መንታ ፡ ዐይነት ፡ ያልነውም ፣ **ገወዪ—ጒ ፣ ገዉአ—ጓ ፣ ገወዬ—ጔ ፣ ገወህ—ጕ** ፡ እያለ ፡ መንታውን ፡ ዋየል ፡ በመንታ ፡ ቅጥል ፡ ያሳያል ። ምንም ፡ የቅጥይን ፡ ጠባይ ፡ ለማስረዳት ፡ መንታ ፡ ዋየል ፡ ብንል ፣ በዚህ ፡ ፊደል ፡ ውስጥ ፡ ካንዳንድ ፡ በቀር ፡ ኹለት ፡ ዋየል ፡ የለም ፣ ወ ፡ በየቅጥላቸው ፡ ስላለ ፡ ተውጦና ፡ ተጐርዶ ፡ ይቀራል ። ድምጣቸው ፡ ግን ፡ ከታች ፡ አስቀድመን ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ (ክፍል ፡ ፯) ፡ በቅጥሉና ፡ በዋየሉ ፡ መጠን ፡ ዕጥፍ ፡ ድ ርብ ፡ ነው ፣ በግእዛቸው ፡ ላይ ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ እንደ ፡ ተደረቡ ፣ በቀሩትም ፡ ባራት ፡ ባራቱ ፡

---

(፩) የ ፡ ደግሞ ፡ በደፊንቱ ፡ አገባብ ፡ ሲገኘው ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በ ኢት ፡ ከኢት ፡ ለኢት ፡ ስለኢት ፡ ወደኢት ፡ እስከኢት ፡ ይላል ፡ እንጂ ፣ በየኢት ፡ ከየኢት ፡ ስለ የኢት ፡ ወደ ፡ የኢት ፡ እስከ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አይልም ፣ ቢልም ፡ ጸያፍ ፡ ነው ።

ላይ ፡ ካዕብ ፡ ተደርቧል ። የድምጣቸው ፡ ስልት ፡ እንደ ፡ በቅሎ ፡ እንደ ፡ ፈናፍንት፡ ዐጓጕል፡ ከ ኹሉ ፡ አለኹ ፡ የሚል ፡ ዲቃላ ፡ መኾኑ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ድምጥ ፡ በጽርእ ና ፡ በሮማይስጥም ፡ ዲፍቶንግ ፡ ይባላል ፤ ክዑብ ፡ ድምፅ ፡ ምንትወ ፡ ድምፅ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፫ኛም ፡ በጓጓኳቋ ፡ አንጻር ፡ ለሚገኙ ፡ ከቧ ፡ እስከ ፡ ቷና ፡ እስከ ፡ ሯ ፡ ላሉት ፡ እነጓጓኳቋ ም ፡ ሳይቀሩ ፡ ለመላው ፡ ለ፳፮ቱ ፡ ዲቃሎች ፡ ለራብዖች ፡ ብቻ ፡ ፍጹም ፡ ዐመላቸው ፡ ወይም ፡ ዋየላቸው ፡ ዋ ፡ ነው ፤ ቅጥላቸው ፡ ኹሉ ፡ ህየንተ ፡ ዋ ፡ ኹኖ ፡ በዋ ፡ ፈንታ ፡ ገብቷል ። ዋ ፡ ደ ግሞ ፡ ቅጥሉ ፡ የአ ፡ ምሳሌ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ዉአ ፡ ተብሎ ፡ ስለ ፡ ኹለት ፡ ዋየል ፡ ይቈጠራል ። ቅጥላቸው ፡ ቀርቶ ፡ በዝርዝር ፡ ፊደል ፡ ሲጣፉ ፡ ግን ፡ ቧቷቋ ፡ የነበሩት ፡ ቡአ ፡ ቱአ ፡ ቹአ ፡ ያሰኛሉ ፤ ይህነን ፡ ደግሞ፡ ዘርዝሮ፡ ሲጥፉት ፡ በዉአ ፡ ተዉአ ፡ ቸዉአ ፡ ያሰኛልና ፤ ቅጥ ላቸው ፡ እንደ ፡ ጓጓኳቋ ፡ በ፪ ፡ ወገን ፡ መኾኑ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። ልብ ፤ ልቧ ፡ ዐስቧል ፡ የተባ ለውም ፡ ቃል ፡ በዝርዝር ፡ ሲጣፍ ፤ ዐስቡ ፡ አል ፡ አለ ፡ ወይም ፡ ዐስበዎ ፡ አል ፡ ያሰኛል ፤ አል ፡ አለ ፡ ማለት ፡ ሀለወ ፡ ሀሎ ፡ ካለው ፡ የወጣ ፡ ነው ። አልና ፡ ዐሰበ ፡ በየራሳቸው ፡ የቆሙ ፡ ፪፡ ልዩ ፡ ቃሎች ፡ ሲኾኑ ፡ በመካከላቸው ፡ ኹለቱ ፡ ዋየሎች፡ (ዉአ)፡ ገጥመው ፡ ተባብረው ፡ ምን ታዌያቸውን ፡ ስላጠፉት ፡ ፩ ፡ ቃልና ፡ ፩ ፡ ንርመት ፡ ኹነው ፡ ዐስቧል ፡ ተብለው ፡ በተዋሕ ዶ ፡ ይጣፋሉ ፤ ምስጢራቸውም ፡ እንዳይለያይ ፡ እንዳይቀላቀል ፡ ቧ ፡ ዘበኛ ፡ ኹኖ ፡ ይጠብቃ ል ። በዚህ ፡ ባንዱ ፡ ራብዕ ፡ የኹሉ ፡ አካሄድ ፡ ይታወቃልና ፤ ኹሉን ፡ መናገር ፡ አያሻም ። (ተ ረት) ፤ አንድ ፡ ዐረግ ፡ ቢስቡ ፡ ዱር ፡ ይሰበስቡ ። የግእዝ ፡ ዐመል ፡ ከሮማይስጥ ፡ ዋየል ፡ መ ግጠሙና ፡ መተባበሩም፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ተጣፈው ፡ ነው ። ዉ—u ፤ ዪ—i ፤ አ—a ፤ ዬ—é ፤ ሀ—e ፤ ዎ—o ። የኤውሮፖች ፡ ፊደል ፡ ፳፮ ፡ ዘር ፡ እንደ፡ ኾነ ፡ የ ኛም ፡ በዚሁ ፡ ልክ ፡ ፳፮ ፡ ዘር ፡ ነውና ፤ ግእዝ ፡ ግእዙን ፡ ከነድርቦቹ ፡ በነዚህ ፡ በ፭ቱ ፡ ዋየል ፡ ሲያስኬዱት ፡ በዝርዝር ፡ አጣጣፍ ፡ ፪፻፸ ፡ ይኾን ፡ የነበረው ፡ ተጠቅልሎ ፡ ፴፯ ፡ ይኾናል ። ድርቦች ፡ ያልናቸው ፡ ፲፩ ፡ ናቸው ፤ ፩ቱ ፡ ዲቃሎችና ፡ ፯ቱ ፡ ዐማርኞች ። ፪፻፸ ፡ ካልነውም ፡ ፳፰ቱ ፡ ዐማርኛ ፡ ነው ። አኃዝ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ አካሄድ ፡ ለመቀልጠፍ ፡ ያው ፡ የተለመደው ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ የተቀበለው ፡ ባለዘሮው ፡ (1—10)፡ ህንዳዊው ፡ ቊጥር ፡ ይሻላል ። ይህነንም ፡ አኃዝ ፡ ዐረቦች ፡ ማእከል ፡ ኹነው ፡ ከህንድ ፡ ወደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ስላሳለፉት ፤ አካሄዱም ፡ እንዳ ረብ ፡ ፊደል ፡ ካቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ኤውሮፖች ፡ ዐረብ ፡ ይሉታል ፤ ገንዘብነቱ ፡ ግን ፡ የህንዶች ፡ ነው ፤ ያወጣውም ፡ አንድ ፡ ነጋዲ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ዳግመኛም ፡ በጅ ፡ መኪና ፡ የሚሰካው ፡ የኤውሮፖች ፡ ፊደል ፡ የፊደሉ ፡ እጅታ ፡ ጣቶች ፡ የሚያርፉበት ፡ ካስማ ውና ፡ እውታሩ ፡ ፵፪ና ፡ ፵፫ ፡ ሲኾን ፤ ፊደሉ ፡ ከናኃዙና ፡ ከንጓዙ ፡ ከነይዘቱ ፡ ከነምልክቱ ፡ ፹፬ ፡ ወይም ፡ ፹፮ ፡ ነውና ፤ የኛም ፡ አኃዝ ፡ ካንድ ፡ እስከ ፡ እልፍ ፡ (፩—፼) ያለው ፡ ኻያው ፡ ቅንጣት ፡ ፊደል ፡ በዚያ ፡ ባሥሩ ፡ በህንዳዊው ፡ ላይ ፡ ቢጨመር ፡ ቦታው ፡ ይተርፋል ፡ እንጂ ፡ አይጠበውም ። ይህም ፡ ኹሉ ፡ ኹኖ ፡ የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ ፊደል ፡ ከንጓዙና ፡ ከነጭፍራው ፡ ከነምልክቱ ፡ ኹሉን ፡ ባንዳይቅር ፡ ሰብስቦ ፡ ሲቈጥሩት ፡ ገና ፡ ፸፱ ፡ ነውና ፤ ፹፬ና ፡ ፹፮ ፡ ለማ ድረግ ፡ አስቀድመን ፡ በነጥብ ፡ አገባብ ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፤ ከፈረንጆቹ ፡ ምልክት ፡ አሻሽሎ ፡ መርጦ ፡ ፭ ፡ ወይም ፡ ፯ ፡ ያኽል ፡ ተውሶ ፡ መጨመርና ፡ ማግባት ፡ ያስፈልጋል ። የዚህ ፡ መ

ቅድም ፡ ሐሳብ ፡ ምኞቱና ፡ ጣሩ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፤ ከፊደላት ፡ በቀር ፡ የመኪናው ፡ ሕግ ፡ ሥርዐቱና ፡ ደንቡ ፡ ሳይለወጥ ፡ በዚያው ፡ በነሎቹ ፡ መኪና ፡ የኛን ፡ ፊደሎች ፡ ፴ ፡ ፴ቱን ፡ በያንዳንዱ ፡ ካስማ ፡ እያገቡ ፡ ለመጣፍና ፡ ለማተም ፡ ነው ። ይህን ፡ ጥሩ ፡ ሐሳብ ፡ ከባለመኪኖች ፡ ተስማምቶ ፡ በጥሩ ፡ ሥራ ፡ ቢከተሉት ፡ ከዚያው ፡ ከተቈረጠው ፡ ከመኪናው ፡ ዋጋ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ከሳራ ፡ የድካም ፡ ሥራ ፡ የለበትም ። የፊደሉም ፡ ትምርት ፡ የኤውሮፓን ፡ ፊደል ፡ ላዩ ፡ ልጆች ፡ ፊደሉን ፡ ብቻ ፡ መላልሶ ፡ በማየት ፡ ይፈጸማል ፤ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ፊደሉ ፡ ቅናት ፡ ምቀኝነት ፡ የሌለው ፡ መምርና ፡ መጣፍ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አያሻም ።

---

(፴፩)

## ፊደል ፡ ሣልስ ፤ ጸያሔ ፡ ፍኖት ፡ መብእስ ።

፫ኛ ፡ ፊደል ፤ ሐዲስ ፡ መንገድ ፡ በጥፊትና ፡ በጅ ፡ መኪና ፡ ግእዝ ፡ ካማርኛ ፡ የሚያስኬድ ።

| በመሎች ፡ ወይም ፡ ዋየሎች ። | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| (ግእዝ)፡ | (ካዕብ)፡ ዉ | (ሣልስ)፡ ዪ | (ራብዕ)፡ ኣ ፤ ዋ | (ኃምስ)፡ ዬ | (ሳድስ)፡ ህ | (ሳብዕ)፡ ዎ |
| አ | አዉ-ኡ | አዪ-ኢ | ኣ(ዋ) | አዬ-ኤ | አህ-እ | አዎ-ኦ |
| በ | በዉ-ቡ | በዪ-ቢ | በኣ-ባ<br>በዋ-ቧ | በዬ-ቤ | በህ-ብ | በዎ-ቦ |
| ገ | ገዉ-ጉ | ገዪ-ጊ | ገኣ-ጋ | ገዬ-ጌ | ገህ-ግ | ገዎ-ጎ |
| ጐ | — | ጐዪ-ጒ | ጐዋ-ጓ | ጐዬ-ጔ | ጐህ-ጕ | — |
| ደ | ደዉ-ዱ | ደዪ-ዲ | ደኣ-ዳ<br>ደዋ-ዷ | ደዬ-ዴ | ደህ-ድ | ደዎ-ዶ |
| ጀ | ጀዉ-ጁ | ጀዪ-ጂ | ጀኣ-ጃ<br>ጀዋ-ጇ | ጀዬ-ጄ | ጀህ-ጅ | ጀዎ-ጆ |
| ሀ | ሀዉ-ሁ | ሀዪ-ሂ | ሀኣ-ሃ | ሀዬ-ሄ | ህ | ሀዎ-ሆ |
| ወ | ዉ | ወዪ-ዊ | ወኣ-ዋ | ወዬ-ዌ | ወህ-ው | ዎ |
| ዘ | ዘዉ-ዙ | ዘዪ-ዚ | ዘኣ-ዛ<br>ዘዋ-ዟ | ዘዬ-ዜ | ዘህ-ዝ | ዘዎ-ዞ |
| ኘ | ኘዉ-ኙ | ኘዪ-ኚ | ኘኣ-ኛ<br>ኘዋ-ኟ | ኘዬ-ኜ | ኘህ-ኝ | ኘዎ-ኞ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሐ | ሐዉ-ሑ | ሐዪ-ሒ | ሐአ-ሓ | ሐዬ-ሔ | ሐህ-ሕ | ሐዎ-ሖ |
| ኀ | ኀዉ-ኁ | ኀዪ-ኂ | ኀአ-ኃ | ኀዬ-ኄ | ኀህ-ኅ | ኀዎ-ኆ |
| ኈ | — | ኈዪ-ኊ | ኈዋ-ኋ | ኈዬ-ኌ | ኈህ-ኍ | — |
| ጠ | ጠዉ-ጡ | ጠዪ-ጢ | ጠአ-ጣ<br>ጠዋ-ጧ | ጠዬ-ጤ | ጠህ-ጥ | ጠዎ-ጦ |
| ጨ | ጨ ዉ-ጩ | ጨ ዪ-ጪ | ጨ አ-ጫ<br>ጨ ዋ-ጯ | ጨ ዬ-ጬ | ጨ ህ-ጭ | ጨ ዎ-ጮ |
| የ | የዉ-ዩ | ዪ | የአ-ያ | ዬ | የህ-ይ | የዎ-ዮ |
| ከ | ከዉ-ኩ | ከዪ-ኪ | ከአ-ካ | ከዬ-ኬ | ከህ-ክ | ከዎ-ኮ |
| ኸ | ኸዉ-ኹ | ኸዪ-ኺ | ኸአ-ኻ<br>ኸዋ-ዃ | ኸዬ-ኼ | ኸህ-ኽ | ኸዎ-ኾ |
| ኰ | — | ኰዪ-ኲ | ኰዋ-ኳ | ኰዬ-ኴ | ኰህ-ኵ | — |
| ለ | ለዉ-ሉ | ለዪ-ሊ | ለአ-ላ<br>ለዋ-ሏ | ለዬ-ሌ | ለህ-ል | ለዎ-ሎ |
| መ | መዉ-ሙ | መዪ-ሚ | መአ-ማ<br>መዋ-ሟ | መዬ-ሜ | መህ-ም | መዎ-ሞ |
| ነ | ነዉ-ኑ | ነዪ-ኒ | ነአ-ና<br>ነዋ-ኗ | ነዬ-ኔ | ነህ-ን | ነዎ-ኖ |
| ኘ | ኘዉ-ኙ | ኘዪ-ኚ | ኘአ-ኛ<br>ኘዋ-ኟ | ኘዬ-ኜ | ኘህ-ኝ | ኘዎ-ኞ |
| ሠ | ሠዉ-ሡ | ሠዪ-ሢ | ሠአ-ሣ | ሠዬ-ሤ | ሠህ-ሥ | ሠዎ-ሦ |
| ዐ | ዐዉ-ዑ | ዐዪ-ዒ | ዐአ-ዓ | ዐዬ-ዔ | ዐህ-ዕ | ዐዎ-ዖ |
| ፈ | ፈዉ-ፉ | ፈዪ-ፊ | ፈአ-ፋ<br>ፈዋ-ፏ | ፈዬ-ፌ | ፈህ-ፍ | ፈዎ-ፎ |
| ጸ | ጸዉ-ጹ | ጸዪ-ጺ | ጸአ-ጻ<br>ጸዋ-ጿ | ጸዬ-ጼ | ጸህ-ጽ | ጸዎ-ጾ |
| ፀ | ፀዉ-ፁ | ፀዪ-ፂ | ፀአ-ፃ | ፀዬ-ፄ | ፀህ-ፅ | ፀዎ-ፆ |
| ቀ | ቀዉ-ቁ | ቀዪ-ቂ | ቀአ-ቃ | ቀዬ-ቄ | ቀህ-ቅ | ቀዎ-ቆ |
| ቈ | — | ቈዪ-ቊ | ቈዋ-ቋ | ቈዬ-ቌ | ቈህ-ቍ | — |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ረ | ረዉ-ሩ | ረዪ-ሪ | ረአ-ራ<br>ረዋ-ሯ | ረዬ-ሬ | ረህ-ር | ረዎ-ሮ |
| ሰ | ሰዉ-ሱ | ሰዪ-ሲ | ሰአ-ሳ<br>ሰዋ-ሷ | ሰዬ-ሴ | ሰህ-ስ | ሰዎ-ሶ |
| ሸ | ሸዉ-ሹ | ሸዪ-ሺ | ሸአ-ሻ<br>ሸዋ-ሿ | ሸዬ-ሼ | ሸህ-ሽ | ሸዎ-ሾ |
| ተ | ተዉ-ቱ | ተዪ-ቲ | ተአ-ታ<br>ተዋ-ቷ | ተዬ-ቴ | ተህ-ት | ተዎ-ቶ |
| ቸ | ቸዉ-ቹ | ቸዪ-ቺ | ቸአ-ቻ<br>ቸዋ-ቿ | ቸዬ-ቼ | ቸህ-ች | ቸዎ-ቾ |
| ጸ | ጸዉ-ጹ | ጸዪ-ጺ | ጸአ-ጻ | ጸዬ-ጼ | ጸህ-ጽ | ጸዎ-ጾ |
| ፐ | ፐዉ-ፑ | ፐዪ-ፒ | ፐአ-ፓ | ፐዬ-ፔ | ፐህ-ፕ | ፐዎ-ፖ |

(፴፪)

የመኪና ፡ ፊደል ፡ ከነጓዙ ።

አ በ ገ ደ ሀ ወ ዘ ሐ ኀ ጠ የ ከ ለ መ ነ ሠ ዐ ፈ ጸ ፀ ቀ ረ ሰ ተ ጸ ፐ ።

ዲቃሎች ።

ጐጀ ዠ ኈ ጨ ኰ ኸ ኘ ቈ ሸ ቸ ።

ዋየሎች ።

ዉ ዪ አ—ዋ ዬ ህ ዎ ።

ምልክቶች ።

፡ ፣ ፤ ፥ ። ’ ? ! ( ) - « » —

አኃዞች ።

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | ፯ | ፰ | ፱ | ፲ |
| ፳ | ፴ | ፵ | ፶ | ፷ | ፸ | ፹ | ፺ | ፻ | ፼ |

(፴፫)

የዋየል ፡ አነባብ ፡ ማሳያ ፡ ከመጽሐፉ ፡ ምሳሌ ፡ የመጡ ፡ ቃሎች ።

## ገህ አህ ዘህ=ግእዝ ።

(ምኛ ፡ ፮ ፡ ፱) ፡ መህበአለህየኣቱ ፡ ሰለዎመዎነህ ፡ ወለህደ ፡ ደኣወዩትህ ፡ ነህገዉሦ ፡ ኣህሰህረኣአዩሰህ ። ለአአህመህረዎ ፡ ጠህበበህ ፡ ወተገህሦኣጸህ=ምሳሌያት ፡ ሰሎሞን ፡ ወልደ ፡ ዳዊት ፡ ንጉሥ ፡ እስራኤል ። ለአእምሮ ፡ ጥበብ ፡ ወተግሣጽ ።

## ፀ መኣ ረህ ኘኣ=ፀማርኛ ።

(፱ ፡ ፲) ፡ አህሰኣነህተ ፡ ለህጆዎቸህ ፡ የኣበኣተህነህ ፡ ትገህሦኣጸህ ፡ ሰህመዉ ፡ ፀህወህቀተህነህመህ ፡ ቲኣሰህተወህለዉ ፡ ዘነህደህ ፡ አደህመህጠዉ=እናንተ ፡ ልጆች ፡ ያባትን ፡ ተግሣጽ ፡ ስሙ ፡ ዕውቀትንም ፡ ታስተውሉ ፡ ዘንድ ፡ አድምጡ ። (፪) ፡ መለህከኣመህ ፡ ተህመህረህተህ ፡ አህሰጠኣቸህኸዋለኸዉነኣ ፡ ተህመህረህተዩነህ ፡ አተህተወዉ=መልካም ፡ ትምርት ፡ እሰጣችኋለሁና ፡ ትምርቴን ፡ አትተዉ ። (፲፩ ፡ ፳፩) ፡ ለህበዉ ፡ በህለህንቶቸ ፡ ኣ ፡ የኸዎነ ፡ አሰህተወኣየህ ፡ ተበህለዎ ፡ የህጠረኣለህ ፡ በነገረዉመህ ፡ ጠኣፈኣጨህ ፡ የኸዎነ ፡ ተህመህረህተህ ፡ የኣበዘኣለህ=ልቡ ፡ ብልኅተኛ ፡ የኾነ ፡ አስተዋይ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ፡ በንገሩም ፡ ጣፋጭ ፡ የኾነ ፡ ትምርት ፡ ያበዛል ። (፳፪) ፡ ለገዘኣወህ ፡ ሰወህ ፡ መኣሰህተወኣለህ ፡ የሐህየህወተህ ፡ መህነህጨህ ፡ ነወህ ፡ የደነኣቂህረህተህ ፡ ተህመህረህተህ ፡ ገህነህ ፡ ሰህነህፈህነኣ ፡ ነወህ=ለገዛው ፡ ሰው ፡ ማስተዋል ፡ የሕይወት ፡ ምንጭ ፡ ነው ፡ የደናቆርት ፡ ትምርት ፡ ግን ፡ ስንፍና ፡ ነው ። (፳፫) ፡ የበህለህኄተ ፡ ኘኣ ፡ ለህበህ ፡ አፈዉነህ ፡ አሰህተወኣየህ ፡ የኣደረህገኣለህ ፡ ለከነህፈረዉመህ ፡ ተህመህረህተህ ፡ የህጨመህረኣለህ=የብልኅተኛ ፡ ልብ ፡ አፉን ፡ አስተዋይ ፡ ያደርጋል ፡ ለከንፈሩም ፡ ትምርት ፡ ይጨምራል ። (፲፮ ፡ ፲፯) ፡ በሰነፈህ ፡ አህጀህ ፡ የጠህበበህ ፡ መገህዘኣ ፡ ገነህዘበህ ፡ በዩነዎረህ ፡ ጠህበበህነህ ፡ የህገዘኣ ፡ ዘነህደህ ፡ አአህመህረዎ ፡ የለወህመህነኣ ፡ መህነህ ፡ የህጠቀህመወኣለህ=በሰነፍ ፡ እጅ ፡ የጥበብ ፡ መግዣ ፡ ገንዘብ ፡ ቢኖር ፡ ጥበብን ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ አእምሮ ፡ የለውምና ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ። (አስተውል) ፡ ዋየሎች ፡ ራሳቸውን ፡ መቻላቸው ፡ አስቀድመን ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ በመነሻና ፡ በመድረሻ ፡ ብቻ ፡ ብቻቸውን ፡ ሲኾኑ ፡ ነው ። (ምሳሌ ፡ (ዉ ፡ ዋ ፡ ዎ) ፡ ዉለዋለህ ፡ ውሏል ። ዉጠዋለህ ፡ ውጧል ። ዋጆ ፡ ዋሸ ፡ ዋና ፡ ዋለለ ። ደኣዋ ፡ ዳዋ ። መህጠህዋ ፡ ምጥዋ ። ለህጆህዎ ፡ ልጅዎ ። በዩተህዎ ፡ ቤትዎ ። በዩለአዎ ፡ ቢላዎ ። ግእዝ ፡ ሲቀድመው ፡ ግን ፡ ዋየል ፡ እንጂ ፡ (ኮንሶን) ፡ ባለቤት ፡ አይኾንም ። (ምሳሌ) ፡ ጨዉ ፡ ጬ ፡ ሰዉ ፡ ሱ ፡ ጨወዉ ፡ ሰወዉ ፡ ጬወ ፡ ሰወ ። ሸዋ ፡ ሿ ። ዐደዋ ፡ ዐዷ ። ነገዎ ፡ ነጎ ። ነገወዎ ፡ ነጎዎ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። (ዩ ፡ ዩ) ፡ ነዩ ፡ ኒ ። ነየዩ ፡ ነዩ ። ነየህ ፡ ነይ ። አህዩ ፡ እዩ ። ገዩተአዩ ፡ ጌታዩ ። አህመበዩተዩ ፡ እመቤቴ ። ሸወዩ ፡ ሸዊ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

(ኣ ፡ ሀ) ፡ ኣ ፡ ባማርኛ ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ ሲኾን ፡ እኔ ፡ በሚል ፡ ባስደራጊ ፡ ትንቢት ፡ አስመጣለኹ ፤ እስቀጣለኹ ፤ ይህን ፡ በመሰለ ። መድረሻ ፡ ሲኾን ፡ አፈሀአ ፤ አፍአ ። ሀወሀከሀ ፤ ሀውክ ፤ የወአሀ ፤ የዋሀ ፡ እያለ ፡ በነዚህ ፡ ብቻ ፡ ይገኛል ። ይህ ፡ ፊደል ፡ የወጣ ፡ በጅ ፡ መኪና ፡ ምክንያት ፡ ፊደላት ፡ በዙ ፡ ተብለው ፡ እንዳይከፈሉ ፡ ለመኪና ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለጅ ፡ ጥፈት ፡ አይቀናም ፤ ሥራው ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ነው ። «ያማርኛ ፡ ቃል ፡ ገቢር ፡ ሲኾን ፤ ካልዘረዘረ ፡ ወትሮ ፡ ን ፡ አያሰኝም ። ሚስት ፡ አገባ ፡ ልጅ ፡ ወለደ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ሚስትን ፡ ልጅን ፡ አይልም ፤ ሲዘረዝር ፡ ግን ፡ ሚስቱን ፡ ፈታ ፡ ልጁን ፡ መታ ፡ ያሰኛል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ግእዙ ፤ ልጅን ፡ መቅጣት ፤ ሚስትን ፡ መቈጣት ፡ እያሰኘ ፡ በሚያሻውና ፡ በሚያምርለት ፡ ቦታ ፡ አለዝርዝር ፡ ይነገራል» ።

---

## (፴፬)

(አርባዕቱ ፡ አዕዋዶ ፡ ኁልቈ) ፤ አራቱ ፡ የቍጥር ፡ ዐውዶች ፡ ወይም ፡ ሰንጠረዦች ፡ በየውስጣቸው ፡ ፲ ፡ ፲ ፡ መደብ ፡ የመደመርና ፡ የመቀነስ ፡ የማብዛትና ፡ የማካፈል ፡ ርባ ፡ ያላቸው ። በዘሮው ፡ ፈንታ ፡ ፲ኛ ፡ አኃዝ ፡ ስለ ፡ ገባባቸው ፡ መደባቸው ፡ በመሸጋሸግ ፡ ተጥፎ ፡ እንደ ፡ ጣት ፡ ታላቅና ፡ ታናሽ ፡ ኾኗል ። የአኃዙም ፡ ተራ ፡ አጣጣፍ ፡ በያንጻሩ ፡ በየመስሉ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከህንዳዊው ፡ ተራ ፡ ልዩ ፡ ነው ፤ ምንም ፡ ምስጢሩና ፡ ቍጥሩ ፡ ዙሮ ፡ ተጠምጥሞ ፡ ያው ፡ ቢኾን ፡ አካሄዱ ፡ አይገጥምም ። በግእዝ ፡ አኃዝ ፡ መጣፋችን ፡ ሕፃናት ፡ ቶሎ ፡ በቅርብ ፡ እንዲያገኙትና ፡ እንዲያጠኑት ፡ ነው ፤ ሥራው ፡ ግን ፡ በዚያው ፡ በበቀለበት ፡ በባለዘሮው ፡ በህንዳዊው ፡ አኃዝ ፡ ካልኾነ ፡ በዚህ ፡ አይመችም ፤ በ፩ ፡ የተወሰነውን ፡ ፀጋማይ ፡ መንገድ ፡ ፲ና ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ መሄድ ፡ ያፈርሱታል ። ከታች ፡ በ፫ኛው ፡ ክፍል ፡ ካ(1፩—10፲)ንድ ፡ እስካሥር ፡ የታጣነውን ፡ ቍጥር ፡ አኹን ፡ በዚህ ፡ ከአዕዋድ ፡ በፊት ፡ መቅድም ፡ አድርገን ፡ እስከ ፡ ምእልፊት ፡ እንጥፋለን ። ህንዳዊው ፡ አኃዝ ፡ ከቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ መሄዱን ፤ በዘሮ ፡ መብዛቱን ፤ ፱ ፡ ብቻ ፡ ኹኖ ፡ በ፫ ፡ በ፫ ፡ ቤት ፡ መከፈሉን ፡ የዘሮውን ፡ ጠባይ ፡ (0) ቅርጡን ፡ አቀማመጡን ፤ የአኃዞቹን ፡ ስም ፤ በቦታ ፡ ምክንያት ፡ መለዋወጡን ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ የሚያውቀው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ መልኩንና ፡ ግብሩን ፡ ዘርዝረን ፡ ሳንጥፍ ፡ አንድን ፡ (1) ብቻ ፡ በዘሮ ፡ (0) እያበዛን ፡ ከግእዝ ፡ ቍጥር ፡ እናስማማለን ፤ መስማማቱንም ፡ በያኳያው ፡ እይ ። (የህንድና ፡ የግእዝ ፡ አኃዝ) ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አ | — | ፩ ፤ | አንድ ። |
| 10 | የ | — | ፲ ፤ | ዐሥር ። |
| 100 | ቀ | — | ፻ ፤ | መቶ ። |
| 1. 000 | ቄ | — | ፲፻ ፤ | ሺሕ ። |
| 10. 000 | እ | — | ፼ ፤ | እልፍ ። |
| 100. 000 | የእ | — | ፲፼ ፤ | እእላፍ ። |
| 1. 000. 000 | ቀእ | — | ፻፼ ፤ | እእላፋት ። |
| 10. 000. 000 | ቄእ | — | ፲፻፼ ፤ | ትእልፌት ። |
| 100. 000. 000 | እእ | — | ፼፼ ፤ | ትእልፊታት ። |
| 1. 000. 000. 000 | ቄእእ | — | ፲፻፼፼ ፤ | ምእልፌት ። |
| 10. 000. 000. 000 | እእእ | — | ፼፼፼ ፤ | ምእልፊታት ። |

ይህነኑ ፡ ደግሞ ፡ ምእልፊታተ ፡ ምእልፊታት ፡ ብሎ ፡ ሲያዛርፋት ፡ ምእልፊታት ፡ ጊዜ ፡ ምእልፊታት ፡ ያሰኛል ። ይኸውም ፡ ሚልዮን ፡ ጊዜ ፡ ሚልዮን ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

## መደመር ።

የመደመር ፡ ሥርዐት ፤ በያንዳንዱ ፡ መደብ ፡ ከተጣፈው ፡ ከ፫ ፡ ከ፫ቱ ፡ ተራ ፡ አኃዝ ፡ ፪ ፡ ፪ቱን ፡ በማጣፈር ፡ እየደመሩ ፡ ፫ኛ ፡ ፫ኛውን ፡ ድሙር ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ፩ና ፡ ፩ ፡ ፪ ። ፩ና ፡ ፪ ፡ ፫ ፡ እያሰኘ ፡ ባሥሩ ፡ አኃዝ ፡ ኹሉ ፡ እስካሥር ፡ መደብ ፡ መዝመቱን ፡ ያሳያል ።

### ፩ኛ ፡ የመደመር ፡ ዐውድ ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ | ና | ፩ | ፪ |
| ፩ | » | ፪ | ፫ |
| ፩ | » | ፫ | ፬ |
| ፩ | » | ፬ | ፭ |
| ፩ | » | ፭ | ፮ |
| ፩ | » | ፮ | ፯ |
| ፩ | » | ፯ | ፰ |
| ፩ | » | ፰ | ፱ |
| ፩ | » | ፱ | ፲ |
| ፩ | » | ፲ | ፲፩ |
| ፪ | ና | ፪ | ፬ |
| ፪ | » | ፫ | ፭ |
| ፪ | » | ፬ | ፮ |
| ፪ | » | ፭ | ፯ |
| ፪ | » | ፮ | ፰ |
| ፪ | » | ፯ | ፱ |
| ፪ | » | ፰ | ፲ |
| ፪ | » | ፱ | ፲፩ |
| ፪ | » | ፲ | ፲፪ |
| ፫ | ና | ፫ | ፮ |
| ፫ | » | ፬ | ፯ |
| ፫ | » | ፭ | ፰ |
| ፫ | » | ፮ | ፱ |
| ፫ | ና | ፯ | ፲ |
| ፫ | » | ፰ | ፲፩ |
| ፫ | » | ፱ | ፲፪ |
| ፫ | » | ፲ | ፲፫ |
| ፬ | ና | ፬ | ፰ |
| ፬ | ና | ፭ | ፱ |
| ፬ | » | ፮ | ፲ |
| ፬ | » | ፯ | ፲፩ |
| ፬ | » | ፰ | ፲፪ |
| ፬ | » | ፱ | ፲፫ |
| ፬ | » | ፲ | ፲፬ |
| ፭ | ና | ፭ | ፲ |
| ፭ | » | ፮ | ፲፩ |
| ፭ | » | ፯ | ፲፪ |
| ፭ | » | ፰ | ፲፫ |
| ፭ | » | ፱ | ፲፬ |
| ፭ | » | ፲ | ፲፭ |
| ፮ | ና | ፮ | ፲፪ |
| ፮ | » | ፯ | ፲፫ |
| ፮ | » | ፰ | ፲፬ |
| ፮ | » | ፱ | ፲፭ |
| ፮ | » | ፲ | ፲፮ |
| ፯ | ና | ፯ | ፲፬ |
| ፯ | » | ፰ | ፲፭ |
| ፯ | » | ፱ | ፲፮ |
| ፯ | » | ፲ | ፲፯ |
| ፰ | ና | ፰ | ፲፮ |
| ፰ | ና | ፱ | ፲፯ |
| ፰ | » | ፲ | ፲፰ |
| ፱ | ና | ፱ | ፲፰ |
| ፱ | » | ፲ | ፲፱ |
| ፲ | ና | ፲ | ፳ |

## መቀነስ ።

የመቀነስ ፡ ሥርዐት ፤ ከ፫ቱ ፡ ተራ ፡ አኃዝ ፡ ብዙው ፡ አንደኛው ፡ ጕዳይ ፡ አናሽ ፤ ፪ኛው ፡ ተነሽ ፡ ተቀናሽ ፤ ፫ኛው ፡ ቀራ ፡ ትርፍ ፡ ይባላል ። ይህም ፡ ካ፩ ፡ ፩ ፡ ቢነሡ ፡ (0ዘሮ) ባዶ ፡ ይቀራል ። ካ፲ ፡ ፱ ፡ ቢነሡ ፡ ፩ ፡ ይቀራል ፡ እያለ ፡ እስካሥር ፡ መደብ ፡ መዝሙቱን ፡ ያሳያል ።

### ፩ኛ ፡ የ መ ቀ ነ ስ ፡ ዐ ው ድ ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ካ | ፩ | ፩ | ቢ | ባ | ይ |
| » | ፩ | ፪ | » | ፩ | » |
| » | ፩ | ፫ | » | ፪ | » |
| » | ፩ | ፬ | » | ፫ | » |
| » | ፩ | ፭ | » | ፬ | » |
| » | ፩ | ፮ | » | ፭ | » |
| » | ፩ | ፯ | » | ፮ | » |
| » | ፩ | ፰ | » | ፯ | » |
| » | ፩ | ፱ | » | ፰ | » |
| » | ፩ | ፲ | » | ፱ | » |
| ከ | ፪ | ፪ | ቢ | ባ | ይ |
| » | ፪ | ፫ | » | ፩ | » |
| » | ፪ | ፬ | » | ፪ | » |
| » | ፪ | ፭ | » | ፫ | » |
| » | ፪ | ፮ | » | ፬ | » |
| » | ፪ | ፯ | » | ፭ | » |
| » | ፪ | ፰ | » | ፮ | » |
| » | ፪ | ፱ | » | ፯ | » |
| » | ፪ | ፲ | » | ፰ | » |
| ከ | ፫ | ፫ | ቢ | ባ | ይ |
| » | ፫ | ፬ | » | ፩ | » |
| » | ፫ | ፭ | » | ፪ | » |
| » | ፫ | ፮ | » | ፫ | » |
| » | ፫ | ፯ | » | ፬ | » |
| » | ፫ | ፰ | » | ፭ | » |
| » | ፫ | ፱ | » | ፮ | » |
| » | ፫ | ፲ | » | ፯ | » |
| ከ | ፬ | ፬ | ቢ | ባ | ይ |
| ከ | ፬ | ፭ | ቢ | ፩ | ይ |
| » | ፬ | ፮ | » | ፪ | » |
| » | ፬ | ፯ | » | ፫ | » |
| » | ፬ | ፰ | » | ፬ | » |
| » | ፬ | ፱ | » | ፭ | » |
| » | ፬ | ፲ | » | ፮ | » |
| ከ | ፭ | ፭ | ቢ | ባ | ይ |
| » | ፭ | ፮ | » | ፩ | » |
| » | ፭ | ፯ | » | ፪ | » |
| » | ፭ | ፰ | » | ፫ | » |
| » | ፭ | ፱ | » | ፬ | » |
| » | ፭ | ፲ | » | ፭ | » |
| ካ | ፮ | ፮ | ቢ | ባ | ይ |
| » | ፮ | ፯ | » | ፩ | » |
| » | ፮ | ፰ | » | ፪ | » |
| » | ፮ | ፱ | » | ፫ | » |
| » | ፮ | ፲ | » | ፬ | » |
| ካ | ፯ | ፯ | ቢ | ባ | ይ |
| » | ፯ | ፰ | » | ፩ | » |
| » | ፯ | ፱ | » | ፪ | » |
| » | ፯ | ፲ | » | ፫ | » |
| ከ | ፰ | ፰ | ቢ | ባ | ይ |
| » | ፰ | ፱ | » | ፩ | » |
| ከ | ፰ | ፲ | » | ፪ | » |
| ከ | ፱ | ፱ | ቢ | ባ | ይ |
| » | ፱ | ፲ | » | ፩ | » |
| ካ | ፲ | ፲ | ቢ | ባ | ይ |

## ማብዛት ።

የማብዛት ፡ ሥርዐት ፡ ወይም ፡ አካሄድ ፤ ከ፫ቱ ፡ ተራ ፡ አኃዝ ፡ ፩ኛው ፡ በገር ፤ ፪ኛው ፡ ማብዣ ፤ ፫ኛው ፡ ብኻር ፡ ብዛት ፡ ውጤት ፡ ይባላል ። ይህም ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ፩ ፡ ጊዜ ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ እያለ ፡ እስካሥር ፡ መደብ ፡ መሄዱንና ፡ መዝመቱን ፡ ያሳያል ።

### ፫ኛ ፡ የማብዛት ፡ ዐውድ ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ | ጊ | ፩ | ፩ |
| ፩ | » | ፪ | ፪ |
| ፩ | » | ፫ | ፫ |
| ፩ | » | ፬ | ፬ |
| ፩ | » | ፭ | ፭ |
| ፩ | » | ፮ | ፮ |
| ፩ | » | ፯ | ፯ |
| ፩ | » | ፰ | ፰ |
| ፩ | » | ፱ | ፱ |
| ፩ | » | ፲ | ፲ |
| ፪ | ጊ | ፪ | ፬ |
| ፪ | » | ፫ | ፮ |
| ፪ | » | ፬ | ፰ |
| ፪ | » | ፭ | ፲ |
| ፪ | » | ፮ | ፲፪ |
| ፪ | » | ፯ | ፲፬ |
| ፪ | » | ፰ | ፲፮ |
| ፪ | » | ፱ | ፲፰ |
| ፪ | » | ፲ | ፳ |
| ፫ | ጊ | ፫ | ፱ |
| ፫ | » | ፬ | ፲፪ |
| ፫ | » | ፭ | ፲፭ |
| ፫ | » | ፮ | ፲፰ |
| ፫ | » | ፯ | ፳፩ |
| ፫ | » | ፰ | ፳፬ |
| ፫ | » | ፱ | ፳፯ |
| ፫ | » | ፲ | ፴ |
| ፬ | ጊ | ፬ | ፲፮ |
| ፬ | ጊ | ፭ | ፳ |
| ፬ | » | ፮ | ፳፬ |
| ፬ | » | ፯ | ፳፰ |
| ፬ | » | ፰ | ፴፪ |
| ፬ | » | ፱ | ፴፮ |
| ፬ | » | ፲ | ፵ |
| ፭ | ጊ | ፭ | ፳፭ |
| ፭ | » | ፮ | ፴ |
| ፭ | » | ፯ | ፴፭ |
| ፭ | » | ፰ | ፵ |
| ፭ | » | ፱ | ፵፭ |
| ፭ | » | ፲ | ፶ |
| ፮ | ጊ | ፮ | ፴፮ |
| ፮ | » | ፯ | ፵፪ |
| ፮ | » | ፰ | ፵፰ |
| ፮ | » | ፱ | ፶፬ |
| ፮ | » | ፲ | ፷ |
| ፯ | ጊ | ፯ | ፵፱ |
| ፯ | » | ፰ | ፶፮ |
| ፯ | » | ፱ | ፷፫ |
| ፯ | » | ፲ | ፸ |
| ፰ | ጊ | ፰ | ፷፬ |
| ፰ | » | ፱ | ፸፪ |
| ፰ | » | ፲ | ፹ |
| ፱ | ጊ | ፱ | ፹፩ |
| ፱ | » | ፲ | ፺ |
| ፲ | ጊ | ፲ | ፻ |

## መክፈል ።

የመክፈል ፡ ወይም ፡ የማካፈል ፡ ሥርዐት ፤ ከ፫ቱ ፡ ተራ ፡ አኃዝ ፡ ፩ኛው ፡ ተከፋይ ፤ ፪ኛው ፡ ከፋይ ፡ መክፈያ ፡ ወይም ፡ ተቀባይ ፤ ፫ኛው ፡ ክፍል ፡ ይባላል ። ይህም ፡ ፩ ፡ ባ፩ ፡ ቢከፈል ፡ ፩ ፡ ይኾናል ፤ ወይም ፡ ፩ን ፡ ላ፩ ፡ ቢሰጡት ፡ ፩ ፡ ይደርሰዋል ፡ እያለ ፡ እስካ፲ ፡ መደብ ፡ መዝመቱን ፡ ያሳያል ።

### ፬ኛ ፡ የማካፈል ፡ ዐውድ ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | ባ | ፩ | ቢ | ፩ | ይ |
| ፪ | » | ፩ | » | ፪ | » |
| ፫ | » | ፩ | » | ፫ | » |
| ፬ | » | ፩ | » | ፬ | » |
| ፭ | » | ፩ | » | ፭ | » |
| ፮ | » | ፩ | » | ፮ | » |
| ፯ | » | ፩ | » | ፯ | » |
| ፰ | » | ፩ | » | ፰ | » |
| ፱ | » | ፩ | » | ፱ | » |
| ፲ | » | ፩ | » | ፲ | » |
| ፬ | በ | ፪ | ቢ | ፪ | ይ |
| ፮ | » | ፪ | » | ፫ | » |
| ፰ | » | ፪ | » | ፬ | » |
| ፲ | » | ፪ | » | ፭ | » |
| ፲፪ | » | ፪ | » | ፮ | » |
| ፲፬ | » | ፪ | » | ፯ | » |
| ፲፮ | » | ፪ | » | ፰ | » |
| ፲፰ | » | ፪ | » | ፱ | » |
| ፳ | » | ፪ | » | ፲ | » |
| ፱ | በ | ፫ | ቢ | ፫ | ይ |
| ፲፪ | » | ፫ | » | ፬ | » |
| ፲፭ | » | ፫ | » | ፭ | » |
| ፲፰ | » | ፫ | » | ፮ | » |
| ፳፩ | » | ፫ | » | ፯ | » |
| ፳፬ | » | ፫ | » | ፰ | » |
| ፳፯ | » | ፫ | » | ፱ | » |
| ፴ | » | ፫ | » | ፲ | » |
| ፲፮ | ባ | ፬ | ቢ | ፬ | ይ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ፳ | ባ | ፬ | ቢ | ፭ | ይ |
| ፳፬ | » | ፬ | » | ፮ | » |
| ፳፰ | » | ፬ | » | ፯ | » |
| ፴፪ | » | ፬ | » | ፰ | » |
| ፴፮ | » | ፬ | » | ፱ | » |
| ፵ | » | ፬ | » | ፲ | » |
| ፳፭ | ባ | ፭ | ቢ | ፭ | ይ |
| ፴ | » | ፭ | » | ፮ | » |
| ፴፭ | » | ፭ | » | ፯ | » |
| ፵ | » | ፭ | » | ፰ | » |
| ፵፭ | » | ፭ | » | ፱ | » |
| ፶ | » | ፭ | » | ፲ | » |
| ፴፮ | በ | ፮ | ቢ | ፮ | ይ |
| ፵፪ | » | ፮ | » | ፯ | » |
| ፵፰ | » | ፮ | » | ፰ | » |
| ፶፬ | » | ፮ | » | ፱ | » |
| ፷ | » | ፮ | » | ፲ | » |
| ፵፱ | በ | ፯ | ቢ | ፯ | ይ |
| ፶፮ | » | ፯ | » | ፰ | » |
| ፷፫ | » | ፯ | » | ፱ | » |
| ፸ | » | ፯ | » | ፲ | » |
| ፷፬ | በ | ፰ | ቢ | ፰ | ይ |
| ፸፪ | » | ፰ | » | ፱ | » |
| ፹ | » | ፰ | » | ፲ | » |
| ፹፩ | በ | ፱ | ቢ | ፱ | ይ |
| ፺ | » | ፱ | » | ፲ | » |
| ፻ | ባ | ፲ | ቢ | ፲ | ይ |

(፴፰)

## ታሪክ ፤ —በእንተ ፡ ፍልጠተ ፡ ኊልቌ ፡ ዘመን ፡ ቀዳማዊ ፡ ወደኃራዊ ።

### ስለ ፡ ዘመን ፡ ቍጥር ፡ መለያየት ፡ የሚናገር ፡ ታሪክ ።

የብሉይና ፡ የቍጥር ፡ መምራን ፡ ዘመን ፡ አበውን ፡ እያሻሉና ፡ እየነሡ ፡ እያፋሰሱ ፡ ተርትረው ፡ ደምረው ፡ ሲቈጥሩ ፡ እንዳራቱ ፡ መደብ ፡ ባራት ፡ ዐቢይ ፡ ክፍል ፡ ይከፍሉና ፡ ድምሩን ፡ ፭ሺሕ ፡ ካ፭፻ ፡ ዓመት ፡ ይሉታል ። ቍጥሩና ፡ ክፍሉም ፡ አከፋፈሉም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፤ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ኖኅ ፡ ፳፪፻፶፮ ። —ከኖኅ ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ ፲፭፻፹፰ ። —ከሙሴ ፡ እስከ ፡ ሰሎሞን ፡ ፭፻፺፪ ። —ከሰሎሞን ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ፲፻፷፬ ። ድሙር ፡ ፶፭፻ ። የክፍሉም ፡ ምስጢራት ፡ መርከብና ፡ ድንኳን ፡ መቅደስና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናቸው ።



ዘከመ ፡ አውፅአሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአዳም ፡ ወሔዋን ፡ እምገነተ ፡ ትፍሥሕት ፡ ወአሰፈዎሙ ፡ ካዕበ ፡ ተስፋ ፡ መድኀኒት ፡ (ዘፍ፫ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ፡ ፳፩—፳፬) ። ወአመ ፡ በጽሐ ፡ ዕድሜሁ ፡ ፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልዶ ፡ ወተወልደ ፡ እምብእሲት ፡ ወገብረ ፡ በሕገ ፡ኦሪት ፡ ከመ ፡ ይሣየጦሙ ፡ ለእሊ ፡ ውስተ ፡ ኦሪት ፤ ከመ ፡ ንርከብ ፡ ትርሲተ ፡ ውሉድ ፡ (ገላ፬ ፡ ፬ ፡ ፭) ። እስመ ፡ ከመ ፡ ገ፣ ፡ አፍቀሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዓለም ፡ እስከ ፡ ወልዶ ፡ ዋሕደ ፡ መጠወ ፡ ወወሀበ ፡ ቤዛ ፡ (ዮሐ፫ ፡ ፲፮—፲፱ ። ሮሜ፭ ፡ ፰ ። ፰ ፡ ፴፪) ።

ከክርስቶስ ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ ዘመን ፡ ዓመተ ፡ ፍዳ ፡ ዓመተ ፡ ኵነኔ ፡ ዘመን ፡ ብሉይ ፡ ይባላል ። ከክርስቶስ ፡ ወዲህ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ዓመተ ፡ ሥጋዌ ፡ ዘመን ፡ ሐዲስ ፡ ይባላል ፡ ይኸውም ፡ ዘመነ ፡ መሲሕ ፡ ማለት ፡ ነው ። መላው ፡ ባንድነት ፡ ሲደመርና ፡ ሲጠቃለል ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ መዋዕለ ፡ ዓለም ፡ ይባላል ። ኢትዮጵያ ፡ ዘመን ፡ ብሉይን ፡ ፯ ፡ ሺሕ ፡ ከ፭፻ ፡ ወይም ፡ ፶፭፻ ፡ ማለቷ ፡ ከጥንታዊው ፡ ጽርእ ፡ የተቀዳ ፡ ከዮናኒ ፡ የተመለሰ ፡ መጽሐፈ ፡ ኦሪቷን ፡ ተከትላ ፡ ነው ። ኦሪት ፡ በዘመን ፡ ብሉይ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ተካክሎ ፡ ተጥፎ ፡ በ፫ ፡ ስሞች ፡ ተጠርቷል ፡ መጀመሪያ ፡ ሙሴ ፡ የጣፈው ፡ ኦሪተ ፡ ሌዋውያን ፡ ተብሏል ። ፪ኛ ፡ በስልምናሶር ፡ ዘመን ፡ ምናሴ ፡ ካህን ፡ ቤቴል ፡ ለሰማርያ ፡ ሕዝብ ፡ የጣፈው ፡ ኦሪተ ፡ ሳምራውያን ፡ ተብሏል ፡ እሊሁም ፡ አሕዛብ ፡ ናቸው ፡ (፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፳፬—፴) ። ፫ኛ ፡ በበጥሊሞስ ፡ ዘመን ፡ ሰብዓ ፡ ሊቃናት ፡ ከዕብራኒ ፡ ወደ ፡ ዮናኒ ፡ የመለሱት ፡ በስማቸው ፡ ኦሪተ ፡ ሊቃናት ፡ ተብሏል ፡ (ስንክ ፡ የካ፳) ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አይሁድ ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ ኦሪት ፡ ነቢያትን ፡ ለመቃወም ፡ በግዜርና ፡ በመሲሑ ፡ ላይ ፡ በጠላትነት ፡ ተነሥተዋል ። ኦሪት ፡ ነቢያት ፡ የሰበኩት ፡ ርግጡ ፡ የመሲሕ ፡ አመጣጥ ፡ ለማዳንና ፡ ለመፍረድ ፡ በትሕትናና ፡ በልዕልና ፡ በዕዋልና ፡ በደመና ፡ ፪ ፡ ጊዜ ፡ ሲኾን ፡ የትሕትናውን ፡ አመጣጥ ፡ ፊተኛውን ፡ ክደው ፡ ኋለኛውን ፡ ብቻ ፡ የልዕልናውን ፡ ስላመኑ ፡ ኋላም ፡ እንደዚሁ ፡ ስተው ፡ ተሳስተው ፡ ከመሲሕ ፡ በፊት ፡ በሚመጣው ፡ በሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ የሚያምኑ ፡ ሐሳውያን ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ የመሲሕን ፡ መንግሥት ፡ ሥጋዊ ፡ ምድራዊ ፡ አስመስለው ፡ መሲሑንም ፡ ሥጋው ፡ ቃል ፡ ያይዶሰ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ብለው ፡ ከውነተኛ ፡ አምላክ ፡ ከግዜር ፡ መንግሥት ፡ ከብርሃም ፡ በረከት ፡ ወጥተው ፡ በኦሪት ፡ መርገም ፡ ተጨልጠውና ፡ ተገርኝተው ፡ ወደ ፡ ሰይጣን ፡ መንግሥት ፡ ሂደዋል ፡ (ዮሐ፰ ፡ ፵፬ ። ራእ፪ ፡ ፱) ። የአዳም ፡ ኀጢአት ፡ እንደ ፡ ኰብሽና ፡ እንደ ፡ ቁጥኝ ፡ መርዕት ፡ በሔዋን ፡ እባብ ፡ መርዝ ፡ ተወግቶ ፡ ኹለንተናው ፡ ቈስሎ ፡ ተበላሽቶ ፡ ውሾች ፡ እጋንንት ፡ የሚልሱት ፡ ይህ ፡ በሽተኛ ፡ ዓለም ፡ ከጥንቱና ፡ ከመሠረቱ ፡ ከባቱ ፡ ከአዳም ፡ ከናቱ ፡ ከሔዋን ፡ ዠምሮ ፡ ፈጣሪው ፡ የሰጠው ፡ የመድኀኒት ፡ ተስፋ ፡ ስላለው ፡ ስሙ ፡ ከግብሩ ፡ ተባብሮለት ፡ የሱስ ፡ ዐማኑኤል ፡ ተብሎ ፡ በሙሴ ፡ እባብ ፡ አምሳል ፡ ተሰቅሎ ፡ ከሰማይ ፡ እባብ ፡ ከዲያብሎስ ፡ ሕምዝ ፡ ከሰራዊቱ ፡ መርዝ ፡ የሚያድን ፡ ሰማያዊ ፡ ንጉሥ ፡ ሐኪምና ፡ ፈውስ ፡ የማይሻ ፡ መስሏቸው ፡ የንቅፋትና ፡ የማእዝን ፡ ድንጊያ ፡ በተባለው ፡ በክርስቶስ ፡ ትሕትና ፡ በፍጹም ፡ ውርደቱ ፡ ጨርቅ ፡ አጠርቅሞ ፡ ማንደ ፡ ተሸክሞ ፡ በመታየቱ ፡ በመስቀሉ ፡ በመሰቀሉ ፡ ተሰናክለው ፡ ትንሣኤውንም ፡ አስተባብለው ፡ እውነተኛውን ፡ መሲሕና ፡ መድኅን ፡ የመሲሕን ፡ ዘመን ፡ ከዘመናቸው ፡ ለማራቅ ፡ መሲሑም ፡ ዘመኑም ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ዛሬ ፡ በኛ ፡ ዘመን ፡ ንጉሥ ፡ አይሁድ ፡ ተብሎ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ የተከተለው ፡ እኛ ፡ ግን ፡ ሰቅለን ፡ የገደልነው ፡ የናዝሬቱ ፡ የሱስ ፡ ምንም ፡ ከዳዊት ፡ ዘር ፡ ቢወለድ ፡ ለኛ ፡ ተገዛ ፡ እንጂ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ አልነገሠምና ፡ መሲሕ ፡ አይደለም ፡ ለማለት ፡ እግዜር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ ላባቶቻቸው ፡ ለሌዋውያን ፡ የሰጠውን ፡ ኦሪት ፡ በዘመን ፡ አበው ፡ ምክንያት ፡ ከኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ኹለቱን ፡ ምዕራፍ ፡ (፳ና ፡ ፲፩) ፡ ስላባጠሉት ፡ ስሙ ፡ ተለውጦ ፡ ኦሪተ ፡ አይሁድ ፡ ብጡል ፡ ተብሏል ። ይኸውም ፡ ብጡለ ፡ ፍቅድ ፡ ሙብጠሉ ፡ ትውልድ ፡ ዘአብጠልዎ ፡ አይሁድ ፡ ለእስሒቶ ፡ ደኅርት ፡ ውሉድ ፡ ማለት ፡ ነው ። ብጡልነቱም ፡ በነዚህ ፡ በኹለቱ ፡ ምዕራፍ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ የብሉይ ፡ መምራን ፡ እንደሚሉት ፡ መላው ፡ ፳፬ቱ ፡ ብሔር ፡ ወይም ፡ ፳፬ቱ ፡ የሙሴ ፡ መጽሐፍ ፡ ከሥር ፡ እስከ ፡ ጫፍ ፡ አይደለም ። ኢዮርብዓም ፡ ዐሥሩን ፡ ነገድ ፡ ከግዜርና ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ለማራቅ ፡ በዳንና ፡ በቤቴል ፡ ተራራ ፡ ፪ ፡ የወርቅ ፡ እንቦሶች ፡ አማልክት ፡ ብሎ ፡ እንዳቆመ ፡ አይሁድም ፡ ማብዛ ፡ ሕዝባቸውን ፡ ከውነተኛው ፡ መቅደስ ፡ ከክርስቶስና ፡ ከቤተ ፡

ክርስቲያኑ ፡ ለማራቅ ፡ በኦሪትና ፡ በነቢያት ፡ መጽሐፍ ፡ የንባብ ፡ ግልፎ ፡ የትርጓሜ ፡ ጣዖት ፡ እቁመዋል ፤ የትርጓሜውን ፡ ኋላ ፡ በቦታው ፡ እናመጣዋለን ፡ (ገጽ ፡ ፳፱) ። አለመስታዎት ፡ ዐይንን ፡ ባይን ፡ ማየት ፡ እንዳይቻል ፤ አለመሲሕም ፡ መምርነት ፡ የብሉይ ፡ ኪዳንን ፡ ትርጓሜ ፡ አካቶ ፡ ፈጽሞ ፡ ማወቅ ፡ መረዳት ፡ ርግጡን ፡ ማግኘት ፡ ለማንም ፡ ለማን ፡ አይቻልምና ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ የክርስቶስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ሐዋርያት ፡ አርድእት ፤ ይልቁንም ፡ የኦሪት ፡ ትምርት ፡ አበጋዞች ፡ የብሉይ ፡ የሐዲስ ፡ መሐንድሶች ፡ እነጳውሎስ ፡ እነእስጢፋኖስ ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ኹሉ ፡ ሱባዔ ፡ ትውልድ ፡ ከሔኖክ ፤ ሱባዔ ፡ ዘመን ፡ ከዳንኤል ፡ ሱባዔ ፡ ፅለት ፡ ከኤርምያስ ፡ በሰፍር ፡ በቍጥር ፡ እያመጡ ፤ ከኦሪትና ፡ ከነቢያት ፡ ብዙ ፡ ምስክር ፡ እየሰጡ ፤ ትውልዱን ፡ ከዘመን ፡ ትንቢቱን ፡ ከመድኀን ፡ እያስማሙና ፡ እየተረጐሙ ፤ ኦሪትን ፡ በፋና ፡ በአጋር ፡ በእመት ፤ ወንጌልን ፡ በፀሓይ ፡ በሳራ ፡ በመቤት ፤ የሱስን ፡ በይሥሐቅ ፡ በአብርሃም ፡ መሥዋዕት ፡ እየመሰሉ ፤ ወማኅለቅቱሰ ፡ ለጽድቀ ፡ ኦሪት ፡ አሚን ፡ በክርስቶስ ። እስመ ፡ ጽላሎታ ፡ ይእቲ ፡ ኦሪት ፡ ለእንተ ፡ ትመጽእ ፡ ሠናይት ። ኦሪትሰኬ ፡ መርሐ ፡ ኮነተነ ፡ ለኀበ ፡ ክርስቶስ ፡ እንከሰ ፡ ኢንፈቅድ ፡ መርሐ ፡ እያሉ ፤ በክርክርና ፡ በሙግት ፡ ወዲህም ፡ በአምላካዊ ፡ ኀይል ፡ በታምራት ፡ በ፪ ፡ ወገን ፡ የማይገፉ ፡ የማይሸነፉ ፡ የብሉይ ፡ ዝግኖች ፡ የሐዲስ ፡ ዐርበኞች ፡ ስለ ፡ ኽኑባቸው ፤ ካርባ ፡ የሚበዙ ፡ አይሁዶች ፡ እስጢፋኖስና ፡ ያዕቆብን ፡ ደብድበን ፡ እንደ ፡ ገደልነ ፡ ጳውሎስን ፡ ሳንገድል ፡ እኽል ፡ ውሃ ፡ እንዳንቀምስ ፡ ብለው ፡ ከተማማሉ ፡ በኋላ ፡ ርሱን ፡ ለብቻው ፡ ማግኘትና ፡ መግደል ፡ ቢሳናቸው ፡ ሥጋዊ ፡ ጦራቸው ፡ ጦርነታቸው ፤ የቍጣቸው ፡ አፍሬ ፡ የመሐላቸው ፡ ሰይፍ ፡ በስሉቱና ፡ ባንደበቱ ፡ ወደ ፡ መጻሕፍት ፡ ተመልሷል ። በሸንጎ ፡ ቢረታ ፡ ከቤት ፡ ሚስቱን ፡ መታ ፡ እንደሚሉት ፡ ኹሉ ፤ ከኀፍረትና ፡ ከብስጭት ፡ ከቍጣ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ወንጌልን ፡ ያጠፉ ፡ ኦሪትን ፡ ያሰፉ ፡ መስሏቸው ፤ ሐዋርያት ፡ የሚጠቅሷቸውን ፡ ደረቅ ፡ ትንቢትና ፡ ሱባዔ ፡ ራእይ ፡ ያላቸውን ፤ የክርስቶስን ፡ አምላክነትና ፡ ሰውነት ፤ ድካሙን ፡ ኀይሉን ፡ መከራ ፡ መስቀሉን ፡ በሕማሙና ፡ በሞቱ ፡ የዓለም ፡ መድኀኒት ፡ መኾኑን ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ገልጠው ፡ አፍርጠው ፡ የሚናገሩትን ፤ ቃላቸው ፡ ከብሉይ ፡ ንባብ ፡ የተለየ ፡ ፍጹም ፡ ደረቅ ፡ ሐዲስ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከቍጥር ፡ ከቀመር ፡ ሳይገቡ ፡ ለምስክርነት ፡ እንዳይን ፡ ብሌን ፡ እንዳደራ ፡ ምናን ፡ በፍጹም ፡ ጥንቃቄ ፡ ተጠብቀው ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩትን ፡ የብሉይን ፡ አዋልድ ፡ ኹሉ ፡ በሕዝቅኤል ፡ መቅድም ፡ እንደ ፡ ጣፍነው ፤ ጭራሽ ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ዕልም ፡ ድርግም ፡ አርገው ፡ አጠፉቸው ፤ ይኸውም ፡ በሐዋርያት ፡ ጥቅስ ፡ ይታወቃል ፡ (ማቴ ፳፯ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ይሁ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭) ። ያገራችን ፡ ሰዎች ፡ ዕብራይስጥ ፡ ጠፍቷል ፡ የሚሉት ፡ ይህን ፡ ምክንያት ፡ ይዘው ፡ ነው ፤ ወርቁ ፡ ደረቅ ፡ ትንቢት ፡ ጠፋ ፡ እንጂ ፡ ሚዛኑስ ፡ ቋንቋቸው ፡ አልጠፋም ፤ የሰነፍ ፡ ወሬ ፡ ነው ። ኋላ ፡ ግን ፡ በጽርኡ ፡ ምላሽ ፡ ተገኝተው ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ከተተረጐሙት ፡ አዋልድ ፡ ኩፋሌና ፡ ሔኖክ ፡ ተረፈ ፡ ኤርምያስ ፡ ዕርገተ ፡ ኢሳይያስ ፡ እሊህ ፡ አራቱ ፡ ከግእዝ ፡ በቀር ፡ በኹሉ ፡ ስላልተገኙ ፤ ሔኖክን ፡ ብቻ ፡ ከግእዝ ፡ ተርጕመው ፡ አይሁድ ፡ ሳይቀሩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ኹሉ ፡ ይዘውታል ። ከግእዝ ፡ ጋራ ፡ በዕብራይስጥ ፡ የታተመውን ፡ መጽሐፈ ፡ ሔኖክ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ደብረ ፡ ገነት ፡ ባለው ፡ በአይሁድ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ እኛ ፡ ባይናችን ፡ አይተናል ። ከኦሪቱም ፡ ኹለቱን ፡ ምዕራፍ ፡ (ዘፍ ፭ ፡ ፫—፴፪ ። ፲፩ ፡ ፲—፳፮) ፡ ለዋውጠው ፡ ገላብጠው ፡ ዘመኑ ፡ አበውን ፡ አፋለሱት ፤ አዳም ፡ ሴትን ፡ በ፪፻፴ ፡ ወለደ ፡ ያለውን ፡ በ፻፴ ፡ አሉት ። ሴት ፡ ሄኖስን ፡ በ፪፻፭ ፡ ያለውን ፡ በ፻፭ ፡ አሉት ። ሄኖስ ፡ ቃይናንን ፡ በ፻፺ ፡ ያለውን ፡ በ፺ ፡ አሉት ። እንዲህ ፡ እያሉ ፡ ፻፻ውን ፡ ሰርቀው ፡ ከፊት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እየዞሩ ፡ ከድኅኑና ፡ ከድምሩ ፡ ጋራ ፡ ጥፈውታል ፤ የፋቁትም ፡ ፫፻ ፡ ዓመት ፡ አለ ። ከትውልዱም ፡ አንዱን ፡ ኹለ

ተኛውን ፡ ቃይናን ፡ በጭ ራሽ ፡ ፍቀው ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ አብርሃም ፡ ፲፮፻፴፱ ፡ ዓመት ፡ አጐድለዋል ፤ በግእዙና ፡ ባማርኛው ፡ አሪት ፡ ተመልከት ። አሪት ፡ አይሁድን ፡ የተቀበሉ ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ፬ ፡ ሺሕ ፡ ያኽል ፡ የሚሉበት ፡ ምክንያቱ ፡ ይህ ፡ ነው ። አሪታችን ፡ ከሰብዓ ፡ ሊቃናት ፡ ትርጓሜ ፡ ከጥንታዊው ፡ ጽርእ ፡ መቀዳቱን ፡ አስቀድመን ፡ ተናግረናልና ፤ ስለዚህ ፡ እናትና ፡ ልጁን ፡ ፩ ፡ ወገን ፤ አሪተ ፡ አይሁድን ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ አድርገን ፡ ልዩነታቸውን ፡ እስከ ፡ ጫፍ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ዘርዝረን ፡ ደምረን ፡ እናሳያለን ። ፩ ፡ ወገን ፡ ለኾኑት ፡ ለናትና ፡ ልጁም ፡ ለጽርኡና ፡ ለግእዙ ፡ አሪት ፡ ካራት ፡ ላይ ፡ ጥቂት ፡ ልዩነት ፡ አላቸው ፤ ጽርኡ ፡ ከግእዙ ፡ ፳፮(26) ፡ ዓመት ፡ ያተርፋል ። የኋላ ፡ ዐራሚዎች ፡ ወይም ፡ የግእዝ ፡ ጣፎች ፡ በአኃዝ ፡ ሞክሼና ፡ በግድፈት ፡ የተሳሳቱበት ፡ ይመስላል ፤ ጽርኡ ፡ እንዳይታማ ፡ በንባብ ፡ ውስጥ ፡ ያለን ፡ ቍጥር ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ዕብራይስጥ ፡ በፊደላት ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ ግእዝ ፡ በአኃዝ ፡ አይጥፍም ። የግእዝ ፡ ጣፊ ፡ ግን ፡ ስንኳን ፡ ቍጥሩንና ፡ ቍጥር ፡ የሌለውን ፡ በፊደል ፡ ሲጣፍ ፡ የሚገባውን ፡ ስም ፤ የአምላክ ፡ ኀያ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ፳ኤል ፡ እያለ ፡ ይጽፋልና ፡ ሊገድፍና ፡ ሊስት ፡ ይችላል ፡ ጠባቂና ፡ ከልካይ ፡ የለውም ። ከዚህ ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፡ ባገራችን ፡ ጥፈትና ፡ ትምርት ፡ ተባብረው ፡ ተጣፍረው ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ አይገኙምና ፤ ሳይማሩና ፡ ሊቅ ፡ ሳይኾኑ ፡ ጥፈት ፡ ብቻ ፡ ማወቅ ፡ ከስሕተት ፡ ከግድፈት ፡ አያድንም ። ተምሮም ፡ ጥፈት ፡ አለማወቅ ፡ እንደ ፡ ሽባ ፡ እንዳይነ ፡ ስውር ፡ መኾን ፡ ነውና ፤ በትምርት ፡ ብቻ ፡ እንዲህም ፡ የሚል ፡ አብነት ፡ ይገኛል ፡ እያሉ ፡ ያነኑ ፡ የተጣፈውን ፡ ከመተርጐም ፡ በቀር ፤ መጻሕፍትን ፡ ማረም ፡ መጠንቀቅ ፡ አይቻልም ። መጻሕፍትንም ፡ ፈጽሞ ፡ ለማረም ፡ ለመጠንቀቅ ፤ ሐሳባቸውን ፡ ለማወቅ ፡ ከባሕረ ፡ ምስጢሩ ፡ ለመጥለቅ ፡ የተቀዱበትን ፡ ምንጫቸውን ፡ ማየት ፡ ያስፈልጋል ፤ ምንጫቸውና ፡ የምንጫቸውም ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ምንጭ ፡ ዕብራኒ ፤ የሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ምንጭ ፡ ዮናኒ ።

## አሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ ፭ ።

(አሪተ ፡ ሊቃ) ፡ (አሪተ ፡ አይ) ፡

ቍ ፫ — አዳም ፡ ሴትን ፡ በ፪፻፴ ። በ፻፴ ።
» ፮ — ሴት ፡ ሄኖስን ፡ በ፪፻፭ ። በ፻፭ ።
» ፱ — ሄኖስ ፡ ቃይናንን ፡ በ፻፺ ። በ፺ ።
» ፲፪ — ቃይናን ፡ መላልኤልን ፡ በ፻፸ ። በ፸ ።
» ፲፭ — መላልኤል ፡ ያሬድን ፡ በ፻፷፭ ። በ፷፭ ።
» ፲፰ — ያሬድ ፡ ሄኖክን ፡ በ፻፷፪ = በ፻፷፪ ።
» ፳፩ — ሄኖክ ፡ ማቱሳላን ፡ በ፻፷፭ ። በ፷፭ ።
» ፳፭ — ማቱሳላ ፡ ላሜሕን ፡ በ፻፹፯ = በ፻፹፯ ።
(ጽርኡ ፡ ግን ፡ በ፻፷፯ ፡ ይላል) ።
» ፳፰ — ላሜሕ ፡ ኖኅን ፡ በ፻፹፪ = በ፻፹፪ ።
(ጽርኡ ፡ ግን ፡ በ፻፹፰ ፡ ይላል) ።
» ፴፪ — ኖኅ ፡ ሴምን ፡ ባ፭፻ ፡ ዓ ፡ ወ = ባ፭፻ ።
(ምዕራፍ ፡ ፲፩) ።
ቍ ፲ — ሴም ፡ አርፋክስድን ፡ በ፻ = በ፻ ።

(አሪተ ፡ ሊቃ) ፡ (አሪተ ፡ አይ) ፡

ቍ ፲፪-አርፋክስ ፡ ቃይናንን ፡ በ፻፴፭ ። (ፍሉቅ) ፡
» ፲፫ — ቃይናን (አርፋ) ሳላሕን ፡ በ፻፴ ። በ፴፭ ።
» ፲፬ — ሳላሕ ፡ ዔቦርን ፡ በ፻፴ ። በ፴ ።
» ፲፮ — ዔቦር ፡ ፋሌግን ፡ በ፻፴፬ ። በ፴፬ ።
» ፲፰ — ፋሌግ ፡ ራግውን ፡ በ፻፴ ። በ፴ ።
» ፳ — ራግው ፡ ሴሩግን ፡ በ፻፴፪ ። በ፴፪ ።
» ፳፪ — ሴሩግ ፡ ናኮርን ፡ በ፻፴ ። በ፴ ።
» ፳፬ — ናኮር ፡ ታራን ፡ በ፻፱ (በ፸፱) ። በ፳፱ ።
(ጽርኡ ፡ ግን ፡ ፻፸፱ ፡ ይላል) ።
» ፳፮ — ታራ ፡ አብርሃምን ፡ በ፻ ፡ ዓ ። በ፸ ፡ ዓ ።
(ጽርኡ ፡ ግን ፡ በ፸ ፡ ይላል) ።
ድምር ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ አብ ፡ ርሃም ፡ ፫ ፡ ሺ ፡ ከ፫፻፹፮ ፡ (3386) ፤ ድ ፡ ፲፮፻፴፯ ፡ (1637) ።

ጽርኡ ፡ ከግእዙ ፡ ፳፯ ፡ ዓመት ፡ ያተርፋልና ፤ ፳፯ን ፡ ከ፹፯ ፡ ቢጨምሩ ፡ ፫ ፡ ሺ ፡ ካ፬፻፲፫ ፡ ዓመት ፡ ይኾናል ። አሪተ ፡ አይሁድ ፡ ያጐደለው ፡ እንደ ፡ ግእዙ ፡ ሺ ፡ ፯፻፵፱ ፡ (1749) ። እንደ

ጽርኡ ፡ ግን ፡ ሺ. ፡ ፲፯፻፷፰ ፡ (1775) ነው ። እግዜር ፡ አስቀድሞ ፡ መጻሕፍቱን ፡ ወደ ፡ ጽርእ ፡
ቋንቋ ፡ ባያሸሽ ፡ የአይሁድ ፡ ክፋት ፡ የአሪታቸው ፡ ብጡልነት ፡ እንዲህ ፡ ፈጽሞ ፡ ባልታወ
ቀም ፡ ነበር ። (ተረት ፤ ስለ ፡ በቅሎ ፡ ክፋት) ፤ እግዜር ፡ ባወቀ ፡ ሰማዩን ፡ አራቀ ። አይሁድ ፡
ግን ፡ በሕይወታቸው ፡ አበጋዝ ፡ በክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ፡ ለመቃብሩ ፡ ጠባቆች ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡
ደፍተው ፡ ሐዋርያት ፡ አርድእት ፡ የተባሉትን ፡ ፻፲፱ቱን ፡ አንቅጸተ ፡ ሕግና ፡ ፹፩ዱን ፡ የወንጌል ፡
በቀልት ፡ እንዳስተባበሉ ፤ በዚህ ፡ ደግሞ ፡ ፸፪ ፡ ሊቃናትን ፡ ያስተባብላሉ ፡ (ማቴ፳፰፡፲፩—፲፮) ።
የሳምራውያንም ፡ ኦሪት ፡ በዘመን ፡ አበው ፡ ቍጥር ፡ ከሰብዓ ፡ ሊቃናት ፡ ትርጓሜ ፡ ከኦሪተ
ጽርእ ፡ እንጂ ፤ ብጡል ፡ ከተባለው ፡ ከኦሪተ ፡ አይሁድ ፡ አይገጥምም ። ይህም ፡ ሐተታና ፡
ቍጥር ፡ ኦሪተ ፡ አይሁድን ፡ ብጡል ፡ ማለት ፡ የሊቁ ፡ የባለታሪኩ ፡ ያቡሻህር ፡ ቃል ፡ ነው ፤
ርሱ ፡ ዘመን ፡ አበውን ፡ ሲጥፍ ፤ ይቤ ፡ መጽሐፈ ፡ ኦሪቶሙ ፡ ለሰብዓ ፡ መተርጕማን ፡ ብሎ ፡
ይገምርና ፡ በመጨረሻው ፡ ይህን ፡ አይሁድ ፡ የፋቁትን ፡ ይናገራል ። ዜና ፡ አይሁድን ፡
የጣፈ ፡ እውነተኛው ፡ ካህን ፡ ዮሴፍ ፡ ወልደ ፡ ኮርዮንም ፡ ዘመን ፡ አበውን ፡ እንዳቡሻህር ፡
እንደ ፡ ኦሪተ ፡ ጽርእ ፡ ጥፏል ፤ ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ አይሁድ ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ጥጦስ ፡
፩ሺሕ ፡ ከ፭፻፷፰ ፡ የሚሉትን ፡ ዓመተ ፡ ፀሐይ ፡ ርሱ ፡ በጨረቃ ፡ ፩ ፡ ሺሕ ፡ ከ፭፻፶፰ ፡ ይላል ።
«አይሁድም ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ሌላም ፡ ርሳቸውን ፡ የሚያሳፍርና ፡ አባቶቻቸውን ፡ የሚያስነ
ውር ፡ ብዙ ፡ ድንቅ ፡ ታሪክ ፡ አምላካዊ ፡ ሥራ ፡ ስላለበት ፡ የዮሴፍን ፡ መጣፍ ፡ አይወዱትም ፤
ይልቁንም ፡ ክርስቲያኖች ፡ ስለ ፡ ተቀበሉት ፡ ታሪኩንም ፡ ታምራቱንም ፡ ተረት ፡ ነው ፡ እያሉ ፡
እንደ ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ሐዲሳት ፡ ይንቅፉታል» ። በጥንተዮን ፡ ቍጥር ፡ ፭ቱ ፡ ሺሕ ፡ ከ፭፻ ፡
ዓመተ ፡ ወርኅ ፡ ካ፲፱ ፡ ጨረቃ ፡ እስከ ፡ ጌታ ፡ ስቅለት ፡ ልክ ፡ ይኾናል ፤ ፴፭ቱም ፡ ከስቅለት ፡
እስከየፋሳሴም ፡ ጥፋት ፡ ነው ። የጨረቃ ፡ ቍጥር ፡ ከፀሐይ ፡ ቍጥር ፡ መብዛቱ ፡ ግን ፡
ፀውደ ፡ ዓመቷ ፡ ፫፻፶፬ ፡ ዕለት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ። በኋላ ፡ ዘመንም ፡ የተነሡ ፡ ፪ቱ ፡ ባለታሪ
ኮች ፡ ኦሪተ ፡ አይሁድን ፡ ንቀፈው ፡ አጸይፈው ፡ ዘመን ፡ አበውን ፡ እንደ ፡ ጽርእና ፡ እንደ ፡
ሳምር ፡ ኦሪት ፡ ጥፈዋል ፤ እሊሁም ፡ ስዒድ ፡ ወልደ ፡ በጥሪቅ ፤ መሕቡብ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘመን
በግ ፤ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፤ ኤጲፋንዮስ ፡ ዘቆጵሮስ ፤ ጽዒዳውያን ፡ ናቸው ። (ኤጲፋንዮስ ፡
እንደነጳውሎስ ፡ ምሁረ ፡ ኦሪት ፡ የነበረ ፡ አይሁዳዊ ፡ ሊቅ ፡ ነው ፤ ጌታ ፡ በታምራት ፡ ማር
ኮታል) ። አቡሻህር ፡ ባ፴፫ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ምስክር ፡ አድርጎ ፡ ኹሉንም ፡ ባንድነት ፡ ጠቅሷ
ቸዋል ፤ ቍጥራቸውንም ፡ ከሰንጠረዡ ፡ ውስጥ ፡ አግብቶታል ፤ ፪ኛው ፡ ባለታሪክ ፡ ግን ፡
ርሱው ፡ ራሱ ፡ ነው ። ፫ኛም ፡ ሉቃስ ፡ ወንጌላዊ ፡ በ፫ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ (ቍ፴፮ ፡ ፴፯) ፡ የክርስ
ቶስን ፡ ትውልድ ፡ አሻቅቦ ፡ ከርሱ ፡ ከዳግማይ ፡ አዳም ፡ ተነሥቶ ፡ እስካሮጌው ፡ አዳም ፡ ሲቈ
ጥር ፤ ዔቦርን ፡ ወልደ ፡ ሳላሕ ፤ ሳላሕን ፡ ወልደ ፡ ቃይናን ፤ ቃይናንን ፡ ወልደ ፡ አርፋክስድ ፡
ብሎ ፡ ኦሪተ ፡ አይሁድን ፡ አበጥልሎ ፡ እንደ ፡ ኩፋሌና ፡ እንደ ፡ ኦሪተ ፡ ጽርእ ፡ ፪ ፡ ቃይናን ፡
ይጥፋል ። ኢትዮጵያ ፡ ዘመን ፡ ብሉይን ፡ እንዲህ ፡ አስተካክላ ፡ ፭ ፡ ሺሕ ፡ ካ፭፻ ፡ ብላ ፡
ስትቈጥር ፤ ዘመን ፡ ሐዲሷ ፡ ልዩ ፡ ኹኖ ፡ ከግብጽ ፡ በቀር ፡ ከማንም ፡ ቍጥር ፡ አይገጥምም ፤
ከሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከምሥራቆችም ፡ ከምዕራቦችም ፡ ወትሮ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡
ታጕድላለች ። ምክንያቱም ፡ ባለታሪኮችን ፡ ትታ ፡ ወንጌል ፡ ተርጓሚችን ፡ ስለ ፡ ተከተለች ፡
ይመስላል ። በምሥራቅም ፡ በምዕራብም ፡ ያሉ ፡ መተርጕማን ፡ (ማቴ፳፩ ፡ ፪) ፡ ኢይትኀደግ ፡
ዝየ፡ እብን፡ ዲበ፡ እብን ፡ ያለውን ፡ ሲተረጕሙ ፡ በዘመን ፡ ቍጥር ፡ አልተስማሙም ፤ እኩሌ
ቶች ፡ ከዕርገት ፡ በኋላ ፡ በ፴፯ ፤ ከልደት ፡ በኋላ ፡ በ፸ ፡ ይላሉ ፤ እኩሌቶች ፡ በ፸፯ ፡ ይላሉ ፤

ኢትዮጵያም ፡ ሕጹጽ ፡ ትታ ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ በ፸ ፤ ከዕርገት ፡ በኋላ ፡ ባ፵ ፡ ትላለች ። ባለታሪኮች ፡ ግን ፡ እንዳንድ ፡ ልብ ፡ መከራ ፡ እንዳንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ ኹነው ፡ ሰዓት ፡ ደቂቃ ፡ ሳይተዉ ፡ የነገሥታቱን ፡ ዘመን ፡ በወርኅ ፡ በዕለት ፡ ዘርዝረው ፡ ደምረው ፡ ከዕርገት ፡ በኋላ ፡ ባ፵፬ ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ በ፸፯ ፡ ጠፋች ፡ ብለው ፡ ጥፈዋል ። የባለታሪኮች ፡ አባት ፡ (ዩሲፉስ) ፡ ዮሴፍ ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ አስቀድመን ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ ከፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ እስከ ፡ ጥጦስ ፡ ፭ ፡ ሺሕ ፡ ከ፺፪፻፴፫ ፡ ዓመተ ፡ ወርኅ ፡ ብሏል ። አቡሻህርም ፡ ባ፲፱ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ከዮሴፍ ፡ መጽሐፍ ፡ ከ፫ኛው ፡ ክፍል ፡ ጠቅሶ ፤ ወኮነ ፡ ሙዕየታ ፡ ለቀድስ ፡ በኀምሳ ፡ ወኀምስቱ ፡ ምእት ፡ ሰብዓ ፡ ወሰብዐቱ ፡ (፶፰፻፸፯) ፡ ዓመት ፡ ፀሓያዊት ፡ እምፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ እመ ፡ ዐሡሩ ፡ ለኃምስ ፡ ወርኅ ፡ ወእመ ፡ ተሱዑ ፡ ለሠርቀ ፡ ረዠብ ፡ በኀምሳ ፡ ወሰብዐቱ ፡ ምእት ፡ አርብዓ ፡ ወሰመንቱ ፡ (፶፯፻፵፰) ፡ ዓመት ፡ ወርኃዊት ፡ ይላል ፤ ኃምስ ፡ ወርኅ ፡ ረዠብ ፡ ያለውም ፡ ነሐሴን ፡ ነው ። ፫ኛም ፡ ሮብራክ ፡ የሚባል ፡ ባለታሪክ ፡ በክርስቲያን ፡ ቍጥር ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ በ፸፯ ፡ ጠፋች ፡ ይላል ። ፬ኛም ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ የተነሣ ፡ ግሬጽ ፡ የሚባል ፡ አይሁዳዊ ፡ በታሪኩ ፡ እንደዚሁ ፡ ይላል ። ከአይሁድና ፡ ካገራቸው ፡ ጥፋት ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ሌላ ፡ ፩ኛ ፡ የማያሳስት ፡ ቍጥር ፡ ስለሌለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ የምታጐድለው ፡ ያ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ይህ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በግልጥ ፡ ይታወቃል ። ከዕርገት ፡ በኋላ ፡ ያለውን ፡ ፵፬ቱን ፡ ዓመት ፡ ፬ቱን ፡ ትታ ፡ ፵ ፡ እንዳለችው ፡ ፸፯ቱንም ፡ ፯ቱን ፡ ትታ ፡ ፸ ፡ ብላዋለች ። ይህም ፡ ልማድ ፡ ዓመቱን ፡ በወር ፡ ስንቈጥር ፡ ጳጉሜን ፡ ስለ ፡ ሕጸጺ ፡ በናሴ ፡ ላይ ፡ ትተን ፡ ፲፪ ፡ ወር ፡ እንደምንለው ፡ ነው ፤ ሊቃውንትም ፡ እንቅዱስ ፡ ኤፍሬም ፡ ፳ቱን ፡ ቀን ፡ ትተው ፡ ተጸውረ ፡ በከርሣ ፡ ተሰዐተ ፡ አውራኀ ፡ የሚሉት ፡ ይህነን ፡ ይመስላል ። ሕጹጽ ፡ ትቶና ፡ ሕጹጽ ፡ መልቶ ፡ መቍጠር ፡ ከሰውና ፡ ከግዜር ፡ የተገኘ ፡ የመጽሐፍ ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ (ዘፍ፲፭ ፡ ፲፫ ። ዘፀ፲፪ ፡ ፵ ። ጥበ፯ ፡ ፪) ። እንዳንድ ፡ የኤውሮፓ ፡ ሰዎች ፡ ድሜጥሮስ ፡ ዓመተ ፡ ዓለምን ፡ ባ፳፪ ፡ ቍና ፡ ሲሰፍር ፡ ሲቈጥር ፡ ዘመን ፡ ብሉይ ፡ ፭ሺ ፡ ከ፬፻፺፪ ፡ ቢኾንበት ፡ ፭፻ ፡ እንዲመስለት ፡ ፰ቱን ፡ ዓመት ፡ ከላይ ፡ ከዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ አውርዶ ፡ ለታችኛው ፡ ተውሳክ ፡ አድርጎታል ፡ ብለው ፡ ያወራሉ ፤ የመላ ፡ የግምት ፡ አነጋገር ፡ ነው ፤ የተሣልቆም ፡ ይመስላል ፤ እውነትስ ፡ ቢኾን ፡ ባቡሻህር ፡ በመርሐ ፡ ዕዉር ፡ ይጣፍ ፡ ነበር ። ካገራችንም ፡ ሰዎች ፤ የምሥራቅ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እርቶዶክሳውያን ፡ ሶርያና ፡ እርመን ፡ ግሪክ ፡ ሌሎቹም ፡ ኹሉ ፡ እንደኛና ፡ እንደ ፡ ግብጥ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ያጐድላሉ ፡ ብለው ፡ የሚተርኩ ፡ አሉ ፤ ምሥራቃውያን ፡ ግን ፡ ስንኳን ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ፯ ፡ ወር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ አያጐድሉም ፤ ከበዓላትም ፡ በቀር ፡ በዘመን ፡ ቍጥር ፡ ከምዕራብ ፡ እንጂ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አይገጥሙም ። ምሥራቆች ፡ ከምዕራቦች ፡ የሚለዩ ፡ በ፩ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ በወር ፡ ብተትና ፡ በበዓላት ፡ ብቻ ፡ ይህነኑም ፡ ባለቤታቸው ፡ በቃል ፡ በስንክሳር ፡ ይመሰክራሉ ። ዛሬም ፡ በጭራሽ ፡ በብተትና ፡ በበዓላት ፡ ከምዕራቦች ፡ ተስማምተው ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኹነዋል ፤ መቼም ፡ መች ፡ ቢኾን ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ የብተትና ፡ የቍጥር ፡ አንድነት ፡ የላቸውም ። የግብጦችም ፡ ታሪክ ፡ ፪ ፡ ነው ፤ ዓመተ ፡ ሥጋዌና ፡ ዓመተ ፡ ሰማዕታት ፤ ከሥጋዌም ፡ ይልቅ ፡ የሚጥፉና ፡ የሚቈጥሩ ፡ በሰማዕታት ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ፯ቱን ፡ ዓመቶች ፡ ማጕደልንና ፡ መጨመርን ፡ ኹለቱንም ፡ ስለ ፡ ነቀፉ ፡ ነው ፡ ይባላል ፤ ይህ ፡ ባይኾን ፡ ግን ፡ ጕንዱን ፡ ትተው ፡ ወዳጆቁ ፡ ባልሄዱም ። ከክርስቶስ ፡ እስከ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ እንደኛና ፡ እንደ ፡ ግብጦች ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፸፯ ፡ ነው ፤ እንደሌሎቹ ፡ ግን ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ሲጨመርበት ፡ ፪፻፹፬ ፡ ወይም ፡ ፹፬ ።

ይኸናል ። በዘንዚከር ፡ ሐሳበ ፡ ጸሐፍት ፡ ወፈሪሳውያን ። ይቤሉ ፡ አኀው ፡ አይሁድ ፡ ወፈላስያን ፤ እምፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ እስከ ፡ ዮም ፤ ኀምሳ ፡ ወስድስቱ ፡ ምእት ፡ ተስዓ ፡ ወአርባዕቱ ፡ (፶፮፻፺፬) ፡ ዓመት ። ይኸውም ፡ ፭ ፡ ሺሕ ፡ ከ፮፻፺፬ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ እኼን ፡ ዛሬ ፡ ይህ ፡ መጣፍ ፡ በታተመበት ፡ በዘመነ ፡ ማርቆስ ፡ ወንጌላዊ ፤ አመ ፡ ሳድስ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኬንያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ። ዳግመኛም ፡ ይህ ፡ ፶፬ቱ ፡ ፮ ፡ ዓመት ፡ ተጨም ሮበት ፡ ፭፻ ፡ ከመላ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ፭ሺ ፡ ያለው ፡ ፲፫፻ው ፡ ዘመነ ፡ መሲሕ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፤ ይኸውም ፡ በዕፀ ፡ በለስ ፡ የተመሰሉ ፡ አይሁድ ፡ ከአሕዛብ ፡ እጅ ፡ ወጥተው ፡ አገራቸው ፡ ገብተው ፡ እንደ ፡ ቀድሞቻቸው ፡ ንጉሥ ፡ ቀብተው ፡ የሚያነግሡበት ፡ ባለቃቸው ፡ የሚታዘዙበት ፡ የነጻነት ፡ ወራት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ጌታችንና ፡ ጳውሎስ ፡ ዮሐንስ ፡ ሌሎችም ፡ ነቢያት ፡ የተናገሩት ፡ (፪ተሰ ፡ ፪ ፡ ፫—፲፪ ። ራእ ፲፱ ፡ ፲፩ ፡ ፳) ፡ ሥጋዊውና ፡ ምድራዊው ፡ ሐሳዊው ፡ መሲሓቸው ፡ ግን ፡ የሚገለጥና ፡ የሚሰወር ፡ ባ፴ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ይባላል ። ፪ኛ ፡ ደግሞ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ሲነግሥ ፡ በጭራሽ ፡ ይመጣል ፡ ይላሉ ። የጎግ ፡ ማጎግም ፡ ጦርነት ፡ ወትከውን ፡ ሀገር ፡ ዐባይ ፡ ሠለስተ ፡ መክፈልተ ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ (ራእ፲፮ ፡ ፲፱) ፤ በ፫ቱ ፡ ነገድ ፡ ስም ፡ በሴምና ፡ በካም ፡ በያፌት ፤ ወይም ፡ ነቢዩ ፡ ስማቸውን ፡ ጠርቶ ፡ በተናገራቸው ፡ በ፫ቱ ፡ ደቂቀ ፡ ያፌት ፡ በማጎግ ፡ በቱባል ፡ በሞሳሕ ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፩ ፡ ፪ ። ሕዝ፴፰ ፡ ፪) ፡ ከሦስት ፡ ተከፍሎ ፡ በቍርስ ፡ በምሳ ፡ በራት ፡ ተመስሎ ፡ የቍርሱ ፡ ምሳሌ ፡ ተፈጽሟል ፡ (ማቴ፳፬ ፡ ፯—፳) ። የምሳውና ፡ የራቱም ፡ ተራና ፡ ጊዜ ፡ ይጠብቃል ። ከምሳ ፡ እስከ ፡ ራት ፡ ያለው ፡ ጊዜም ፡ ሐሳዌ ፡ መሲሕ ፡ እስኪነግሥ ፡ ከምሳው ፡ ግብግቦ ፡ ለቀሩት ፡ ዕረፍትና ፡ ተድላ ፡ ያሳያል ። ከራት ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ተኝቶ ፡ ተነሥቶ ፡ በክርስቶስ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ ነው ፡ (ማቴ፳፭ ፡ ፴፩—፴፫ ። ሮሜ፲፬ ፡ ፲) ። ሺሕ ፡ ዓመትና ፡ መዠመሪያ ፡ ሕይወት ፡ (ትንሣኤ) ፡ የተባለውም ፡ (ራእ፳ ፡ ፩—፯) ፡ በቅዱሳን ፡ አበው ፡ ትርጓሜ ፡ ሺሑ ፡ ዓመት ፡ ዘመነ ፡ ሥጋዌ ፤ ትንሣኤውም ፡ ትንሣኤ ፡ ልቡና ፡ ተብሏል ። ጻድቃን ፡ ምእመናን ፡ በጥምቀት ፡ በቍርባን ፡ የክርስቶስ ፡ ሕዋሳት ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በትንሣኤውና ፡ በርገቱ ፡ ምስጢረ ፡ መንግሥቱን ፡ ተሳትፈው ፡ ዛሬውኑ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አሉና ፤ ሕያዋን ፡ እንጂ ፡ ሙታን ፡ አይባሉም ፡ (ማቴ፳፪ ፡ ፴፪ ። ኤፌ፪ ፡ ፩—፯) ። ሺሑም ፡ ዓመት ፡ ዘመነ ፡ ሥጋዌ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ወሰበ ፡ ኀልቀ ፡ ዐሠርቱ ፡ ምእት ፡ ዓመት ፡ ይትፈታሕ ፡ ሰይጣን ፡ እምነ ፡ ሞቅሑ ፡ ተብሎ ፡ ከ፯ ፡ እስካ፲ ፡ የተጣፈው ፡ ቃል ፡ ያስረዳል ። አይሁድ ፡ ግን ፡ ፊተኛውን ፡ ትንሣኤና ፡ ምጽአት ፡ ዘመነ ፡ ሥጋዌን ፡ ስለ ፡ ካዱ ፡ ዘመነ ፡ አበውን ፡ ሲከፍሉ ፡ ፫ ፡ ፫ውን ፡ ከፊት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዳዞሩት ፡ ሺሑን ፡ ዓመት ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ አዙረው ፡ ለትንሣኤና ፡ ለሐሳዌ ፡ መሲሕ ፡ ይሰጡታል ። ፯ኛው ፡ ሺ ፡ እንደ ፡ ቅዳሜ ፡ ነው ፤ መሲሓችን ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ዐልቆ ፡ እስራኤል ፡ ብቻ ፡ ይነሡና ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነግሠው ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ ሌሎቹ ፡ ሙታን ፡ ይነሣሉ ፡ ብለው ፡ ሌላም ፡ ብዙ ፡ ተረት ፡ ጨምረው ፡ ግልብጦ ፡ ወሬ ፡ ያወራሉ ። (ሙሾ ፤ መነኵሲት ፡ አርግዛ ፡ በምጥ ፡ ስለ ፡ ሞተች) ፤ እንቺ ፡ ሞኝ ፡ እንቺ ፡ ሞኝ ፡ እንቺ ፡ ሞኝ ፡ ተላላ ፤ የኋላውን ፡ በፊት ፡ የፊቱን ፡ በኋላ ።

(፴፪)

ውዳሴ ፡ አምላክ ፡ ወአርጋኖነ ፡ ስም ፡ ቡሩክ ፤ አው ፡ መዝሙር ፡ ወቅዳሴ ፤ ወእመ ፡ አኮ ፡ ድርሳን ፡ (ዲስኩር) ፡ በእንተ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ እምቃለ ፡ ነቢያት ፡ ወሙሴ ። ነቢያትሰ ፡ እሙንቱ ፡ ስኩራነ ፡ መንፈስ ፤ ምሉኣነ ፡ ሞገስ ፤ አቅርንተ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፤ በከመ ፡ ይቤ ፡ ብፁዕ ፡ አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ሠራዒ ፡ መዋዕል ፡ ወአዝማን ፡ በምዙናኑ ፡ ባሕቲቱ ፤ አኮቴት ፡ ለወልድ ፡ የማኑ ፡ ወመዝራዕቱ ፤ ዕበይ ፡ ወክብር ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሕይወቱ ፤ እስመ ፡ ብሂለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ሥሉስ ፡ ዕሩይ ፤ ዘከመ ፡ ፀሓይ ፡ ወብርሃን ፡ ወዋዕይ ፤ ኅቡረ ፡ ህላዌ ፡ ወባሕርይ ፤ ዘኢይትከፈል ፡ ወዘኢይትሌለይ ፤ በከመ ፡ ይቤ ፡ ሙሴ ፡ ነቢይ ፤ ወባዕዳንሂ ፡ ነቢያት ፡ በቃለ ፡ ግናይ ፤ ስማዕ ፡ እስራኤል ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዋሕድ ፡ (ዘዳ፮ ፡ ፬ ። ማር፲፪ ፡ ፳፱ ፡ ፴፪ ። ዮሐ፲፯ ፡ ፫ ። ፩ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፬ ፡ ፮) ። ወበዕብራይስጢ ፡ ይሰመይ ፡ ኤሎሂም ፡ ወአዶናይ ፤ ይሆዋ ፡ ወሻዳይ ፡ (ዳን ፡ አጥብ) ፤ ኤሎሂምሰ ፡ ወአዶናይ ፡ አምላክ ፡ ሐዲስ ፡ ወብሉይ ፤ ይተረጐም ፡ በክልኤ ፡ ፍና ፤ በትሥልስት ፡ ወበዋሕድና ። ቀዳሚ ፤ አምላክ ፡ ወእግዚእ ፡ ዘከመ ፡ ዋሕድና ፡ መለኮቱ ፡ ወሥልጣኑ ፡ ወጠባይዑ ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፮) ። ዝኒ ፡ በተሊወ ፡ አንቀጽ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወአኮ ፡ በተሊወ ፡ አካል ፡ ሠለስቱ ፤ እስመ ፡ እንዘ ፡ ዋሕድ ፡ ሥሉስ ፡ እንበለ ፡ ሕጸጽ ፤ ወእንዘ ፡ ሥሉስ ፡ ዋሕድ ፡ ዘእንበለ ፡ ቢጽ ፤ አንቀጽኒ ፡ ይተሉ ፡ ህላዌ ፡ ወአኮ ፡ አካለ ፤ ዘውእቱ ፡ ብሂል ፡ መለከ ፡ ፈጠረ ፡ ነበበ ፤ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ። ወካዕበ ፡ ይተረጐም ፡ አማልክተ ፡ ወአጋዕዝተ ፡ ዘከመ ፡ ትሥልስተ ፡ አካሉ ፡ ወገጹ ፡ ወመልክኡ ፤ ዝኒ ፡ በተሊወ ፡ አካል ፡ ወገጽ ፡ ተወካፌ ፡ አንቀጽ ፡ ወአኮ ፡ በተሊወ ፡ ባሕርይ ፡ ወአንቀጽ ፤ እስመ ፡ ትርጓሜሁ ፡ ለኤሎሂም ፡ በሕገ ፡ ረበናት ፡ ወሰዋስው ፡ አማልክት ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ዘብዙኃን ፡ ዕደው ፡ (ዘፀ፳፩ ፡ ፮ ። መዝ፹፩ ፡ ፩ ። ፹፩ ፡ ፮) ። ወመብዝኂቱኒ ፡ ይእቲ ፡ የድ ፡ ዘኵሎ ፡ ታበዝኅ ፡ ወታፌድፍድ ፤ ወታብህለነ ፡ ለነሂ ፡ መላኪ ፡ መላክያን ፤ ፈጣሪ ፡ ፈጣርያን ፤ ነባቢ ፡ ነባብያን ፤ በእንተ ፡ ዘተሰውጠት ፡ ቦቱ ፡ ምስለ ፡ ሚም ፡ (ይም) ። ባሕቱ ፡ ትትወነጥ ፡ ወኢትትነከይ ፡ በንባብ ፤ ዘውእቱ ፡ ኤሎሂም ፡ በከመ ፡ ጸሐፍነ ፡ ዝየ ፤ ወአኮ ፡ ኤሎሂይም ። ወአሐዱሰ ፡ ውእቱ ፡ ኤል ፡ አው ፡ ኤሎሀ ፤ ወናሁ ፡ ሎቱ ፡ ስምዕ ፡ ጽድቅ ፤ ዐማኑኤል ፡ (ዒማኑኤል) ፡ ሚካኤል ፡ ወገብርኤል ፤ (ኤሊ) ፡ ኤሎሄ ። ወፍካሬሁኒ ፡ ለአዶናይ ፡ አጋዕዝትየ ፡ ብሂል ፡ ከመ ፡ ዘሠለስቱ ፡ አካል ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ፲፱ ፡ ፪ ። ኢሳ፮ ፡ ፫ ፡ ፰) ። ዝኒ ፡ ዘከመ ፡ ንባቡ ፡ ወቃሉ ፡ ገጸ ፡ በገጽ ። ወአሐዱሰ ፡ አዶን ፡ አዶኒ ፤ ወአኮ ፡ አዶኒም ፡ ወአዶናይ ፤ እስመ ፡ ብሂለ ፡ አዶን ፡ ወአዶኒም ፡ ከመ ፡ ብሂለ ፡ ኤል ፡ ወኤሎሂም ፡ ዘውእቱ ፡ እግዚእ ፡ ወአጋዕዝት ፤ ወአዶኒሰ ፡ ውእቱ ፡ እግዚእየ ፡ ብሂል ። ይሆዋኒ ፡ እግዚእ ፡ ፍጹም ፡ ፍሉጥ ፡ ስም ፤ እግዚአ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፤ ዘውእቱ ፡ ብሂል ፡ እግዚአብሔር ፡ ገባሬ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ። ወሻዳይኒ ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ፡ ወከሃሊ ፡ ኵሉ ፤ ወሥሉጥ ፡ ባዕለ ፡ ኵሉ ። ኤሎሂምኬ ፡ በአማን ፡ አምላክ ፡ ፀሓይ ፡ ዘአስተርአየ ፡ ሥሉስ ፡ ለአብርሃም ፡ በቀትረ ፡ መዓልት ፤ ወተናገሮ ፡ ዋሕደ ፡ ለሙሴ ፡ በነደ ፡ እሳት ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፪ ። ዘፀ፫ ፡ ፪—፮) ። እስመ ፡ አኮ ፡ ከዱን ፡ ወስዉር ፡ ዘኢይትአመር ፡ ሥላሴ ፡ በመጽሐፈ ፡ ሙሴ ፤ ዳእሙ ፡ ጥዩቀ ፡ አእመርናሁ ፡ በኦሪት ፡ ወበነቢያት ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ሥላሴ ፡ ውእቱ ፡ ኤሎሂም ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፤ ዋሕደ ፡ መለኮት ፡ ወኀይል ፡

ወሥሉስ ፡ አካል ። ኤሎሂምኬ ፡ ውእቱ ፡ ዘበቃሉ ፡ ሰቀሎ ፡ ለሰማይ ፤ ወአጽንዖ ፡ ለምድር ፡ ዲበ ፡ ማይ ፤ ወበመንፈሱ ፡ ኮነ ፡ ይጼልል ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ፤ ለቀድሶተ ፡ ባሕር ፡ ቀዲሙ ፡ ከመ ፡ ንጠመቅ ፡ በስሙ ፡ (ዘፍጥ ፩ ፡ ፩ ፡ ፪ ። ማቴ፳፰ ፡ ፲፱) ። ዘውእቱ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ ወአሐቲ ፡ መንግሥት ፡ ወአሐቲ ፡ ሥልጣን ፡ ወአሐቲ ፡ ምኵናን ፡ በከመ ፡ ይቤሉ ፡ አበዊነ ፡ (ዘፍጥ ፩ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯ ። ፫ ፡ ፳፪ ። ፲፩ ፡ ፯ ። ዘኊ ፳ ፡ ፳፬—፳፮ ። ኢሳ ፮ ፡ ፫ ። ማቴ ፲፯ ። ፳፬ ፡ ፩ ። መዝሙር ፵፱ ፡ ፩ ፡ ፯) ። ኢኮነ ፡ ክልኤተ ፡ ወኢሠለስተ ፡ በመለኮቱ ፡ ወንድሉ ፡ ወኢይትዌከፍ ፡ ተውሳከ ፡ ወኢሕጸተ ፡ ትሥልስተ ፡ አካሉ ፤ አላ ፡ ዘከመ ፡ ፀሓይ ፡ ወእሳት ፡ ወዘከመ ፡ ቀላይ ፡ አምሳሉ ፤ ቅዱስ ፡ ሥሉስ ፡ ይሆዋ ፡ እግዚአ ፡ ኵሉ ፡ ዘሀሎ ፡ ወይሄሉ ። ይሆዋኬ ፡ ወሻዳይ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዶናይ ፤ ወጣኔ ፡ ኪዳን ፡ ብሉይ ፡ ዘአይበሊ ፡ ወፈጻሜ ፡ ኪዳን ፡ ሐዲስ ፡ ገባሬ ፡ ወከሃሊ ፤ ዘአክሀለነ ፡ በከሂሎቱ ፡ ወረድአነ ፡ በረድኤቱ ፡ ኊልቈ ፡ ሥነ ፡ ፊደል ፡ ፍጥረቱ ፡ ወጤነ ፡ ወፈጸሞ ፡ በጽሒፍ ፡ ወበተርጕሞ ፤ አሜን ፡ (ዘፀ ፲፱ ፡ ፳ ። ፳ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ኤር ፴፩ ፡ ፴፩—፴፱ ። ዘካ ፱ ፡ ፲፩ ። ማቴ፳፮ ፡ ፳፰) ።

ዝኬ ፡ ውእቱ ፡ ዘተነግረ ፡ በመጻሕፍት ፡ አምላካውያት ፤ ወዘተብህለሂ ፡ እምሊቃውንት ፤ ሥዙራብ ፡ አነሙት ፡ ፀምረ ፡ ወቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተዐጽፈት ፤ አሕዛብ ፡ አስተጋብኡ ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፤ ወሦኩብ ፡ ተርፈ ፡ ኀበ ፡ አይሁድ ። እንከሰ ፡ ብሉርና ፡ ለነ ፡ ወአኮ ፡ ለአይሁድ ፤ እስመ ፡ ተስፋሆሙ ፡ ወብሉርናሆሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ናሁ ፡ ኮነ ፡ ለአሕዛብ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ አብ ፤ ከመ ፡ ብሉርና ፡ ዔሳው ፡ ለያዕቆብ ፤ ወቅድምና ፡ ግሩም ፡ ኤልያብ ፡ ለዳዊት ፡ ንጹሐ ፡ ልብ ። ያዕቆብሰ ፡ ወዳዊት ፡ ዐማኑኤል ፡ ሰባኬ ፡ ወንጌል ፤ አምላክ ፡ ሥግው ፡ ፍጹመ ፡ ትስብእት ፡ ወፈጻሜ ፡ ትንቢት ፤ ሰማያዊ ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ዋሕድ ፡ ወናዝራዊ ፡ ንጉሠ ፡ አይሁድ ፤ ለበ ፡ አበው ፡ ወበዙረ ፡ ብዙኃን ፡ አኀው ።

ወሥሴነሂ ፡ ቅድስት ፡ ወንጽሕት ፡ እምግብረ ፡ ምንታዌ ፡ ወትርብዕት ፡ ትጼዋዕ ፡ በብእሲ ፡ ከመ ፡ አብ ፤ ወከመ ፡ እምሂ ፡ በብእሲት ፤ የማና ፡ ስፉሕ ፡ ለጸግዎ ፡ ጸጋ ፡ ሲሳየ ፤ ወፀጋማኒ ፡ ድልው ፡ ለሐቂፈ ፡ ውሉደ ፡ ፍጥረት ። ይእቲኬ ፡ ኤሎሂም ፡ አምጻኢተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፤ ፈጣሪት ፡ በኢዳምዎ ፤ ወጸጋዊት ፡ በኢይንጽዎ ። ለአብናሃ ፡ ስብሐተ ፡ አብ ፤ ወለእምናሃ ፡ ውዳሴ ፡ እም ፤ ከመ ፡ ውዳሴሃ ፡ ለማርያም ፡ ይደልዎ ፡ ይደልዎ ፡ ወይሰናአዎ ፡ በርትዐ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ወበኵሉ ፡ ሳዕ ፤ እምአፈ ፡ ውሉዳ ፡ መላእክት ፡ ወሰብእ ፤ አሜን ።

(ማስረጃ) ፤ በግእዝም ፡ የአምላክ ፡ ዘይቤ ፡ እንደ ፡ ኤሎሂም ፡ ነው ፤ ምንም ፡ በልማድ ፡ አፈታት ፡ አንድ ፡ ቢባል ፡ የመለክ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፤ በሰዋስው ፡ ሕግ ፡ ብዛትንና ፡ ውስጠ ፡ ብዙነትን ፡ ያሳያል ። ዘሩና ፡ አንቀጹ ፡ መሊክ ፡ መለከ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ጥሬውን ፡ መልክ ፡ መለክ ፡ ብሎ ፡ «መልከ ፡ ጼዴቅ ፤ መለክ ፡ ሰገድ» ፡ ብዝርውን ፡ አምላክ ፤ አማልክት ፡ (ወይም ፡ መለካን) ፡ ያበኛል ፤ ይህም ፡ ደብር ፡ ፈለግ ፡ ብሎ ፡ አድባር ፡ አድባራት ፤ አፍላግ ፡ አፍላጋት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ መለክ ፡ አንድ ፤ አምላክ ፡ ብዙ ፡ አማልክት ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ይባላል ። ደብርና ፡ ፈለግም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። ዐረቡ ፡ መለክን ፡ ሲያበዛ ፡ ሙሉክ ፤ ዕብራይስጡ ፡ ምላኪም ፡ ይላል ።

ያንድነትና ፡ የሦስትነት ፡ ምስጢር ፡ ፍሬው ፡ ባሕርይና ፡ አካል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ባሕርይና ፡ አካልም ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ እንደ ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ ሕንጻ ፤ እንደ ፡ ሥርና ፡ እንጻጽቅ ፡ የተዋሐደ ፡ የተገናዘበ ፡ ኅብርና ፡ ዕሙር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ፩ነት ፡ ያለሦስትነት ፡ ፫ነትም ፡ ያላንድነት ፡ ብቻ ፡ ብቻውን ፡ ሊጣፍ ፡ ሊነገር ፡ አይቻልምና ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ የነቢያት ፡ ቋንቋ ፡ ዕብራይስጥ ፡ የፈጣሪን ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ የቃሉን ፡ ማሰሪያ ፡ አንቀጹን ፡ ያንድ ፡ ወንድ ፤ ስሚውንና ፡ ባለቤቱን ፡ አንቀጽ ፡ ተቀባዩን ፡ ብዙ ፡ ወንድ ፡ አድርጎ ፤ ባራእ ፡ ኤሎሂም ፡ (ፈጠረ ፡ አምላክ) ። አማር ፡ (ይቤ) ፡ አዶናይ ፡ እያለ ፡

ባንድና ፡ በብዙ ፡ ይናገራል ። ባራእና ፡ አማር ፡ አንድነቱን ፤ ኤሎሄም ፡ አዶናይ ፡ ሦስትነቱን ፡
ገልጠው ፡ አኰልተው ፡ ያስረዳሉ ። ፩ነት ፡ የባሕርይ ፡ ምስጢር ፤ ሦስትነት ፡ የአካል ፡ ምስጢ
ር ፡ ይባላል ፤ ይህም ፡ ዕብራይስጣዊ ፡ ቃል ፡ ሥላሴ ፡ ይሄሉ ፡ ዘልፈ ፡ በሥላሴሁ ። ንባርኮ ፡ ለአ
ብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ካለው ፡ ከሊቃውንት ፡ ቃል ፡ ይስማማል ፤ በብሉያትም ፡ ውስጥ ፡
በብዙ ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ሊቅና ፡ እንደ ፡ ሐዲስ ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ የሚል ፡ ስም ፡ ይገኛል።
ለሰው ፡ ለመላእክት ፡ ሲነገር ፡ ግን ፡ አንቀጹ ፡ ያንድ ፡ የነበረው ፡ ተለውጦ ፤ ኤሎሂም ፡ እቴዎ ፡
(አማልክት ፡ አንትሙ) ። አዶናይ ፡ ሱሩና ፡ (አጋዕዝትየ ፡ ንሕሡ) ፡ እያለ ፡ የብዙ ፡ ይኾናል ።
ብዛቱን ፡ ሳይለቅ ፡ በአንቀጽ ፡ ብቻ ፡ መለየቱም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ የሚሉ ፡ አይሁድን ፡ በጣም ፡ ያሳፍ
ራል ። ርሳቸው ፡ ግን ፡ ፩ነትን ፡ ዐቅፈው ፡ ፫ነትን ፡ ነቅፈው ፡ አንዱን ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ባሕርይ
ና ፡ አንቀጽን ፡ ተከትለው ፤ ኤሎሂም ፡ ማለት ፡ ስላንቱታ ፡ ስለ ፡ ከበረታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡
፫ነት ፡ አይዶለም ፡ ብለው ፡ ፈራሽ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ያልተገባ ፡ ምላሽ ፡ ይሰጣሉ ፤ ኤሎሂም ፡
ማለት ፡ ቃለ ፡ አክብሮ ፡ ከኾነ ፤ ፈጠረም ፡ ማለት ፡ አንቱ ፡ ብሎ ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው
ና ፤ በግድ ፡ ቃለ ፡ አጎስሮ ፡ ይኾናል ። ወይም ፡ የግእዝ ፡ መዝሙር ፡ ዘእንበለ ፡ ይቁም ፡ አድ
ባር ፡ እንደሚለው ፡ ንባብ ፡ ስሕተትና ፡ ጸያፍ ፡ ይባላል ። ዳግመኛም ፤ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአር
አያን ፡ ወበአምሳሊነ ። ናሁ ፡ አዳም ፡ ኮነ ፡ ከመ ፡ አሐዱ ፡ እምኔነ ። ንዑ ፡ ንረድ ፡ ወንክበው ፡
ያላቸው ፡ መላእክትን ፡ ነው ፡ ይሉና ፤ ወዲያው ፡ ደግሞ ፡ ገድሎ ፡ እንደ ፡ ማዳን ፡ ሰብሮ ፡ እንደ፡
መጠገን ፤ የአዳም ፡ ተፈጥሮ ፡ በመላእክት ፡ አርአያና ፡ አምሳል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ምንም ፡ ራሱን ፡
ከመላእክት ፡ ውስጥ ፡ አግብቶ ፡ ንግበር ፡ ቢል ፤ ከዚያው ፡ አያይዞ ፡ ወገብሮ ፡ ለአዳም ፡ ይላል ፡
እንጂ ፤ ወገብርዎ ፡ አይልምና ፤ መፍጠር ፡ የግዜር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አሉታና ፡ ጽድቅ ፡
ያትታሉ ፤ ባ፩ ፡ ራስ ፡ ፪ ፡ ምላስ ። ስለ ፡ መሲሕም ፡ መከራ ፡ ስለ ፡ ቢዛነቱ ፡ (ኢሳ፶፫ ፡ ፩-፲
፪) ፡ ነሥአ ፡ ደዌነ ፡ ወጾረ ፡ ሕማመነ ፡ ወበእንቲአነ ፡ ሐመ ፤ ቀነወኒ ፡ እደውየ ፡ ወእገርየ ፡
ያለውን ፤ ሌላውንም ፡ ኹሉ ፡ የክርስቶስን ፡ ሥራና ፡ መከራ ፡ ለእስራኤል ፡ ሰጥተው ፡ ይፈታ
ሉ ። ይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ለእግዚእየ ፡ ንበር ፡ በየማንየ ፤ አንተ ፡ ካህኑ ፡ ለዓለም ፡ በከመ ፡ ሢመ
ቱ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ያለውም ፤ አብርሃምን ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ዳንኤልም ፡ ስለ ፡ መሲሕና ፡ ስ
ለ ፡ ሞቱ ፡ ሱባዔውን ፡ ቈጥሮ ፡ ትንቢቱን ፡ ሲናገር ፡ ወእምድኅረ ፡ ስሳ ፡ ወክልኤቱ ፡ ሰንበት ፡
ይትቀተል ፡ መሲሕ ፤ ወአኮ ፡ ለርእሱ ፡ ያለውን ፤ ይጥሉበት ፡ ቢያጡ ፡ ለአግሪጳስ ፡ ሰጥተው ፡
ይፈታሉ ። መላእክትን ፡ እንደ ፡ ወልድና ፡ እንደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የአብ ፡ ተባባሮች ፡ የአ
ዳም ፡ ፈጣሮች ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ እስራኤልን ፡ አለስሙና ፡ አለመልኩ ፡ የዓለም ፡ ቤዛ ፡ የአ
ሕዛብ ፡ መድኅን ፤ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ አብርሃምን ፡ በአብ ፡ ቀኝ ፡ ተቀማጭ ፡ የዘላለም ፡ ካህን ፤
ተቀብዖ ፡ የሌለው ፡ አግሪጳስን ፡ ቅቡዕና ፡ መሲሕ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ማለት ፡ በውነቱኞቹ ፡
ዕብራውያን ፡ በንጹውሎስ ፡ ዘንድ ፡ ከጥርስ ፡ ዐልፎ ፡ ዐይን ፡ የሚያሥቅ ፡ ምፀትና ፡ ሥላቅ ፡
ቢባል ፡ እንጂ ፡ ቁም ፡ ነገርና ፡ ጽድቅ ፡ አይባልም ፤ ምፀትነቱም ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፤
ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ ሰማዕታት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከመ ፡ ገዘሰ ፡ ግፍዕ ፡ እመ ፡ ተገብረ ፤ አዕይ
ንት ፡ ይስምዑ ፡ ሆሎ ፡ ነገረ ፤ ወአእዛን ፡ ይርአዩ ፡ አድባረ ፡ (ቅኔ) ። ለብሉይና ፡ ለዕብራይስጥ ፡
ምንም ፡ ባላባቶች ፡ ቢኾኑ ፡ ሌላውን ፡ ትርጓሜ ፡ ያስጊጡትና ፡ ያስረግጡት ፡ እንጂ ፤ የሥላሴ
ንና ፡ የሥጋዌን ፡ ምስጢር ፡ የመሲሕን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ በንባቡና ፡ ባገባቡ ፡ ፊት ፡
ለፊት ፡ አቅንተው ፡ መተርጐም ፡ መፍታት ፡ ማየትና ፡ መስማት ፡ ማስተዋል ፡ መመልከት ፡
አልቻሉም ፤ ዐይኑ ፡ ልባቸውን ፡ ሰይጣንና ፡ ርግማን ፡ ስላወረው ፡ ቋንቋቸውና ፡ መጣፋቸው ፡
የቅርብ ፡ ሩቅ ፡ ሰውርና ፡ ድብቅ ፡ ኾኖባቸዋል ። (ምሳሌ) ፤ ቀራንብት ፡ ኀቤሁ ፡ ለዐይን ፡
እንዘ ፡ ቅሩባን ፤ ቀራንብተ ፡ ኢይኔጽር ፡ ዐይን ፡ (ኢሳ፷ ፡ ፱ ፡ ፲) ። የፈጣሪን ፡ ሥራ ፡ ለፍጡ
ራን ፡ ሰጥቶ ፡ መተርጐም ፡ አባቶቻቸው ፡ እነኢዮርብዓም ፡ ሰው ፡ ሠራሹን ፡ ጣዖት ፤ እሉ ፡

እሙንቱ ፡ አማልክቲከ ፡ እስራኤል ፡ ዘአውፅኡከ ፡ እምድረ ፡ ግብጽ ፡ እያሉ ፡ ይሰቱበትና ፡ ያስቱበት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ከዚህ ፡ ልዩ ፡ አይደለም ። ባህላቸውና ፡ ትርጓሜያቸው ፡ ኹሉ ፡ ብሉይን ፡ ከሐዲስ ፡ ሙሴን ፡ ከክርስቶስ ፡ የሚለይና ፡ የሚያጣላ ፡ የን ባብ ፡ የምስጢር ፡ ደዌ ፡ ነው ፤ ካወንታና ፡ ከዝምታ ፡ በቀር ፡ ማስረጃ ፡ መድኀኒት ፡ የለውም ፡ (ኢሳ፳ ፡ ፳) ። በሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ሥላሴና ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ የተባለው ፤ ያው ፡ በብ ሉይ ፡ ኪዳን ፡ ኤሎሂም ፡ አዶናይ ፡ ይሆዋ ፡ ሻዳይ ፡ ይባል ፡ የነበረው ፡ የአብርሃምና ፡ የይሥ ሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ብሉይ ፡ ኪዳንና ፡ ሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ካንድ ፡ ጕንደ ፡ ሕይወት ፡ የተገኙ ፡ ጽጌና ፡ ፍሬ ፡ እንደ ፡ መኾናቸው ፤ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ካህን ፡ ወበግዕ ፡ በተባለው ፡ በመሲሑ ፡ በዐማኑኤል ፡ ደም ፡ ታርቀው ፡ ተለቃልቀው ፤ እንደ ፡ ነፍስና ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አምሳል ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ኹነው ፡ ከርሱ ፡ ከባለቤቱ ፡ በሐዋርያት ፡ እጅ ፡ ለእስራኤል ፡ ዘነፍስ ፡ (ለቤተ ፡ ክርስቲያን) ፡ ተሰጥተ ዋል ። እስራኤል ፡ ዘሥጋ ፡ የተባለች ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ ከጥንትም ፡ ከኋላም ፡ ከሙሴና ፡ ከክርስቶስ ፡ ዝምር ፡ ኦሪት ፡ ሲኗት ፡ ጣዖት ፡ ወንጌል ፡ ሲኗት ፡ ኦሪት ፡ እያለች ፡ የኦሪት ፡ የወንጌል ፡ ጠበኛ ፤ የሙሴ ፡ የክርስቶስ ፡ ጎረኛ ፤ የነቢያት ፡ የሐዋርያት ፡ ደመኛ ፡ ገፋዒተ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ኾነች ፤ መታረቃቸውን ፡ እንዳታይና ፡ እንዳትሰማ ፡ ዐይኗን ፡ ጨፍና ፡ ጆሮዋን ፡ ደ ፍና ፡ በሕልክ ፡ በንቢታ ፡ በሽፍጥ ፡ ባሉታ ፡ ትኖራለች ፡ (ማቴ፳፫ ፡ ፴—፴፯ ። ዮሐ፳ ፡ ፵፩—፵ ፯ ። ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፯—፲ ። ግብ፯ ፡ ፶፩—፶፫ ። ፳፰ ፡ ፳፫—፳፰) ። ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ የብሉይ ፡ ሐተታ ፡ በስማዕ ፡ እስራኤል ፡ ተመልከት ፤ ስማዕ ፡ እስራኤልም ፡ የተባለ ፡ እንግሊዛዊው ፡ ሊቅ ፡ ማርቲን ፡ ፍላድ ፡ በጌዴዎንና ፡ በልጁ ፡ በጕዲት ፡ ስለሚመኩ ፡ ስለ ፡ ስሜንና ፡ ስለ ፡ ጐንደር ፡ ስላገራችን ፡ ፈላሾች ፡ ከኦሪትና ፡ ከነቢያት ፡ እንደ ፡ ንሀብ ፡ ቀሥሞ ፤ እንደ ፡ ወጥ ፡ ቀምሞ ፤ አጣፍጦ ፡ ተርጕሞ ፤ ባማርኛ ፡ ዐትሞ ፡ ያወጣው ፡ ታናሽ ፡ ምእላድ ፡ ነው ፤ ታናሽነ ቱም ፡ እንደ ፡ ሰናፍጭ ፡ እንደ ፡ ሲርባ ፡ (ሚጥሚጣ) ፡ የኾነው ፡ ፍሬ ፡ ነው ። የጌዴዎንና ፡ የጕ ዲት ፡ ዜና ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በዋዜማ ፡ ታሪክ ፡ ተመልከት ፡ (ገጽ ፡ ፳፰—፴) ።

(ማስታወቂያ) ፤ ጕልቈ ፡ ዘመንና ፡ ውዳሴ ፡ አምላክ ፡ ከነማስረጃቸው ፡ የተጣፉበት ፡ ምክ ንያት ። ቀድሞ ፡ ባገራችን ፡ ከግእዝ ፡ በቀር ፡ የዕብራይስጥ ፡ ወሬ ፡ አልነበረም ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ በዘመናችን ፡ አይሁድ ፡ ለወገኖቻቸው ፡ ለፈላሾች ፡ መምህራን ፡ (ረበናት) ፡ ሰደው ፡ የተማሪ ፡ ቤት ፡ ስላቆሙ ፤ በወዲያ ፡ በጐንደር ፡ ፈላሾቹ ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋና ፡ የብሉይ ፡ ትርጓሜ ፡ ከክርስቲ ያኖች ፡ እንዲማሩ ፤ በዚህም ፡ በሺዋ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ወደዚያ ፡ እየገቡ ፡ ከፈላሾችና ፡ ከረበናት ፡ ዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ሲማሩ ፡ አይተን ፤ የተማሩትም ፡ ኦሪተ ፡ አይሁድን ፡ በዘመን ፡ ቍጥር ፡ ሲያጸድቁና ፡ ሲያገሎሳምሱ ፡ ኦሪተ ፡ ማእዝን ፡ ሲያከስሱ ፡ ሰምተን ፤ ቋንቋቸውን ፡ ከመሳተፋ ችን ፡ የተነሣ ፡ እነዚህን ፡ ክፍሎች ፡ ባጭር ፡ ቃል ፡ ጥፎ ፡ ላንባቦችና ፡ ለተማሮች ፡ መስጠት ፡ የሚገባን ፡ ኾኖ ፡ አገኘነው ። ኹለቱንም ፡ ነገድ ፡ ፊደልና ፡ ቋንቋ ፡ የተማሪ ፡ ቤት ፡ የሚያገና ኛቸው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የዘመን ፡ ቍጥር ፡ የኤሎሂም ፡ ምስጢር ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ መስሎት ፡ በፈላሻ ፡ ባህል ፡ እንዳይታለል ፡ እንዳይሸነገል ፤ ፈላሻውም ፡ ኦሪት ፡ ነቢያት ፡ ከወ ንጌል ፡ የሚጣሉና ፡ ትርጓሜያቸው ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ዐሳብ ፡ መስሎት ፡ ከክርስቲያን ፡ ትምርት ፡ እንዳይርቅና ፡ እንዳይከለከል ፤ ለኹለቱም ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ዳኛ ፡ የወል ፡ እንደ ፡ ምሰሶ ፡ የመካ ከል ፡ ኾኖ ፡ የዘመንን ፡ ታሪክ ፡ የሃይማኖትን ፡ መልክ ፡ የሚያሳይና ፡ የሚያስረዳ ፡ ጥሩ ፡ መስ ታዮት ፡ ይኾንላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለጊዜው ፡ የሚያሻ ፡ መኾኑን ፡ ዐውቀን ፡ ስለ ፡ ፈላሻና ፡ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ጥቅም ፡ ከፊደል ፡ ጋራ ፡ ጥፈንዋል ። (ተረት ፤ ስለ ፡ ተማሪና ፡ ስላንባቢ) ፤ ከዳቦ ፡ የተገኘን ፡ ወጥ ፤ ዐብረኽ ፡ ግመጥ ። በሰጡኽ ፡ አትስነፍ ፤ ከሰጡኽ ፡ አትለፍ ። ከበላ ፡ ብላ ፤ ከሰው ፡ አትጣላ ።

## መክደኛ ፡ ግጥም ።

የምድረ ፡ ከነዓን ፡ ወተትና ፡ ማር ፡
ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ እግዚአብሔር ፤
፷ቱን ፡ ክፍል ፡ ባሕር ፡ ፳ቱን ፡ ክፍል፡ የብስ፡
ከምረት ፡ ከይብሰት ፡ ሊያድን ፡ ሊፈውስ ፡
የጕርፉ ፡ አወራረድ ፡ ግሥገሣ ፡ ዘመቻ ፡
ከኢየሩሳሌም ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ።
ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፡ የሰማይ ፡ ወተት ፡
መዝመሪያ ፡ ትምርት ፡ ምግበ ፡ ሕፃናት ፤
ካርባዕቱ ፡ እንስሳ ፡ ከሱራፌል ፡ ጡት ፡
እነኢሳይያስ ፡ ዐልበው ፡ የጠጡት ።
የተረፈውንም ፡ ውሉደ ፡ ጥምቀት ፡
ሐዋርያት ፡ አርድእት ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡
በልባቸው ፡ ቋጀ ፡ መልተው ፡ ቢያረጉት ፡
እንደ ፡ ቅቤ ፡ እንዳይብ ፡ እንደ ፡ ወገሜት ፡
የማይለየውን ፡ ለመለያየት ፡
አርዮስ ፡ የናጠው ፡ አይሁድ ፡ የገፉት ።
ምንም፡ባንዱ፡አካል፡ላይ፡ቢጨመር፡ሰብእና፡
ጣዕሙ ፡ አይለወጥም ፡ እንደ ፡ ማየ ፡ ቃና ፤
በተዋሕዶው ፡ ውስጥ ፡ ባሕርይ ፡ የሚያጸና ፡
ተፀቅቦ ፡ የሚሉት ፡ መድኀኒት ፡ አለና ።
የመድኀኒቱም ፡ ኀይል ፡ የሚፈውሰው ፡
ኢየሱስ ፡ ናዝራዊ ፡ አምላክና ፡ ሰው ፤
አንድ፡ አካል ፡ አንድ፡ ልጅ ፡ ምንትው፡ልደት፡
የባሕርይ ፡ ተፀቅቦ ፡ የማይፈርስበት ።
ኹሉን ፡ የሚያቈራኝ ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡
አንዱ ፡ አካል ፡ ሰንሰለት ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
በኹለት ፡ ፍንጆቹ ፡ በትእዛዛት ፡
የተሰቀሉበት ፡ኦሪት ፡ ነቢያት ።

---

### ዐዌ ር ፡ የሊቃውንት ፡ ዐዋጅ ።

ምስጢረ ፡ ሥላሴን ፡ ምስጢር ፡ ያሰኘት ፡
የባሕርይ ፡ እንድነት ፡ ያካል ፡ ሦስትነት ፤
ምንታዌ ፡ ርባዔ ፡ ስለሌለበት ።
ምስጢረ ፡ ሥጋዌን ፡ ምስጢር ፡ ያሰኛት ፡
የባሕርይ ፡ ምንታዌ ፡ ያካል ፡ አንድነት ፤
ቱሳሔ ፡ ቡዓዴ ፡ ስለሌለበት ።
በሥላሴ ፡ ምስጢር ፡ እንዳንላላት ፡
በሥጋዌም ፡ ምስጢር ፡ እንዳንሳሳት ፡
ለዶቶ ፡ ጠንቅቆ ፡ ይህን ፡ ኹለት ፡ ስልት ፡
ማስተዋል ፡ ይገባል ፡ መላልሶ ፡ ማየት ፡
በሐዲስ ፡ ትርጓሜ ፡ በሊቅ ፡ አፈታት ፡
ብሉይ ፡ እንደንጀራ ፡ በሚፈተፍት ።

---

### ምክር ፡ ሠናይት ፡ ለኵሉ ፡ ዘይገብራ ።

የተዋሕዶን ፡ ባህል ፡ የኦርቶዶክስን ፡
በሦስቱ ፡ ጉባኤ ፡ የተባለውን ፡
አስተውሎ ፡ ጠንቅቆ ፡ ያልሰማ ፡ ጕርሽ ፡
ከጎረ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ እንዳያጣላሽ ፤
ምስጢረ ፡ ሥላሴን ፡ ሳታደላድል ፡
ምስጢረ ፡ ሥጋዌን ፡ ዐውቃለኹ ፡ አትበል ።
ዐውቃለኹም ፡ ብለኽ ፡ ብትከራከር ፡
ይፈርሳል ፡ ነገርኽ ፡ ጥቅመ ፡ ሰናፆር ፤
ቋንቋኽም ፡ ይለያል ፡ ከቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡
እንዳወጣኪ ፡ እንደበት ፡ እንዳርዮስ ፡ አፍ ።
አፍኽ ፡ እንዳመጣም ፡ ነገር ፡ ብትተች ፡
ውርድ ፡ ይነዙብኻል ፡ የጉባኤ ፡ አፎች ፡
እናባ ፡ አትናቴዎስ ፡ እነቄርሎስ ፡
የማርቆስ ፡ ልጆች ፡ የአባ ፡ አንበስ ፤
ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እስራኤል ፡ ዘነፍስ ፡
እግዜር ፡ ያበቀለው ፡ በወንጌሉ ፡ ራስ ፡
የድርሳናቸው ፡ ቀንድ ፡ ሰማይ ፡ የሚጠቅስ ፡
ሣ ራውም ፡ ትርጓሜ ፡ ምድር ፡ የሚያብስ ።
ከዚህ ፡ ዐልፎ ፡ ተርፎ ፡ እንዳይገነፍል ፡
የቀረው ፡ ሐተታ ፡ ተከድኖ ፡ ይብሰል ።

## ማርያም ፡ ድንግል ፡

ነቀዐ ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፤



ወርግብ ፡ ጸዐዳ ።

ምስለ ፡ ፍቁር ፡ ወልዳ ።